# ምዕራፍ ዐሥራ ስምንት

*ዐፄ ቴዎድሮስ የቤተ መንግሥትንና የቤተ ክህነትን ሕግ እንዳቀሙ ሸዋ በአቤቶ ሰይፉ መሪነት እንደ ሸፈተባቸው*

ዐፄ ቴዎድሮስ ጐጃምን ፣ ቤገምድርን ፣ ትግሬን ፣ ወሎንና ሸዋን በመላው በኃይልና በመሣሪያ ድል አድርገው ፣ ኢትዮጵያን እንደ ጥንቷ አንድ የንጉሠ ነገሥት አገር ለማድረግ ብዙ ከታገሉ በኋላ ፣ ሕዝቡ የሚተዳደርበትን የቤተ ክህነትንና የቤተ መንግ ሥትን ደንብና ሕግ ለማቆም አሰቡ ። በቤተ ክህነት በኩል ከዚህ ቀደም ከአባ ሰላማ ጋር የተስማሙበትን የተዋሕዶ ሃይማኖት ከአጸኑ በኋላ ፣ ክርስቲያንም የሆነ ሁሉ ካንድ ሚስት በቀር ሌላ እንዳያገባ ሲሉ ለዚሁ በመዠመሪያ ለሕዝብ አብነት ለመሆን ራሳቸው እቴጌ ተዋበችን በቊርባን አድሰው አገቡ ።

በኢትዮጵያ የቤተ ክርስቲያን ባህል ፣ ባንድ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚቀድሱ ቀሳውስት ፣ ማኅሌት የሚቆሙ ደብተሮች ከአለቃው ፣ ከቀኝ ጌታው ፣ ከግራ ጌታው ፣ ከርዕሰ ደብሩ ፣ ካጋፋሪው ፣ ከመጨኔው ፣ ከቄሰ ገበዙ ፣ ከጐዝጓዥ ጋር ብዙ ነው ። እነዚህ ደግሞ የሚተዳደሩበት በጥሬ ብር የሚከፈል የወር ደመወዝ ስለሌለ በዚህ ፈንታ የቅስና ፣ የዲቁና ፣ የግብዝና ፣ የመሪጌትነት ፣ የእልቅና መሬት እየተባለ በቤተ ክህነት አገል ጋዮች ዘንድ ስለ ተያዘ ፣ ዐፄ ቴዎድሮስ እነዚህ ሁሉ ለመንግሥት አገልግሎት ስለማይሰጡ ነገሩ ጸጽቷቸው ስለነበረ ፣ «ዝቅ ቢል አንድ ቤተ ክርስቲያን5 ሰሞነኞች ፣ ከፍ ቢል 7 ቀዳሾች ይበቃሉ ። የቀረው መሬት ወደ መንግሥት ይግባ ወይም ደብተራው ለመ ንግሥት እንደሌላው ሁሉ ይገብር ፤ አልገብርም ያለ መሬቱን ይልቀቅና ዐሥራት ፣ በኵራት ፣ ምጽዋት እየተቀበላችሁ ኑሩ» የሚል ዐዋጅ አወጡ ። ካህናቱ ጳጳሱን ይዘው ፣ «እንዴት አድርጎ ይሆናል ?» የሚል ክርክር አንሥተው ፣ በዚህ ምክንያት መጽሐፍ ቀርቦ ፣ በካህናቱ በኩል ፣ «ለቤተ ክርስቲያን አንድ

ጊዜ የተመደበው ይረጋል» የሚል ጥቅስ በማቅረብ አንዱ እያ ነበበ ፣ ሌላው እየተረጐመ ክርክር ስላበዙባቸው ንጉሡ ተናደው ደብተሮቹን ፣

«እንድሽ አንባቢ
እንድሽ ተርጓሚ»

ብለው በቁጣ ከጉባኤው ተነሥተው እስከ መሔድ ደርሰዋል ።(1) ስማቸው ያልታወቀው ጸሐፊ የዚህን ጉዳይ እንደዚህ ሲሉ አብ ራርተውታል ፡ «ዐጤ ቴዎድሮስ ደብተራና መነኩሴ አይወዱም ነበር ። ይልቁንም ደብተራ አይወዱም ነበርና ደብተራን ሲሰ ድቡ ድጉን (ሻሹን) በራሱ ላይ እየታጠቀ (እየጠመጠመ) አይ ዋጋ ፣ አይገብር ፣ ከከተማ ሆኖ የሰው ምሽትና ጋለሞታ እየመ ለመለ (እያማገጠ) ነው ኑሮው ። ስለዚህ ሪሙን ሁሉ ነቅለው በደብር 5 ልዑካን (ቄስና ዲያቆን) ይበቃሉ ፤ ከፍ ላለ ደብርም 7 ቄስ (ቀሳውስት) ይበቃል ብለው ሠርተውት ነበር ። ስለዚህ ካህን ሁሉ አይወዳቸውም ነበር ።»(2) በሌላ ቦታ ላይ ደግሞ፣ አንድ የዳሞት ደብተራ፣ አንድ የእስላም ንጉሥ ያደረገውን ምሳሌ ጠቅሶ፣ «አስተማሪ (ደብተራ ሊቅ) ይገብር፣ ሰሞነኛ ይዳን ማለ ትዎ ትምህርት ሲቀር ቁርባን እንደቀረ ፣ እኛን አስተማሪዎችን ገብሩ ማለት ቁርባን ይቅር ፣ ቤተ ክርስቲያን ይዘጋ ማለትዎ መሰለ» ቢላቸው ፣ «እንዳንተ የሚያስተምር ይገብር አላልሁም ። ዘንጉን እየጐተተ መንደር ለመንደር የሚዞር አረግራጊውን ነው እንጂ ። አሁንም አንተን የመሰለ ሁሉ ከግብር ይዳን» ብለው ማወጃቸው ተጽፏል ።(3)

በቤተ መንግሥትም ወገን ፣ ሰው ሁሉ በዕለት ተግባሩና በደመወዙ እንዲያድር እንጂ ባሪያ መሸጥ ወይም መሸፈት እን ዳይኖር በጠቅላላው በነገሡበት ቀን ፣ ከዚህ በፊት እንዳወጁት ገበሬም ወደ ርሻው ፣ ነጋዴም ወደ ንግዱ የቀረውም ሰው በየሥ ራው እንዲመለስ ባዋጅ አስታወቁ ። በዚህ ጊዜ የቴዝባ አገር ሰዎች ቀርበው «ጃንሆይ ፣ ሰዉን ሁሉ በየሥራህ ግባ ካሉት

1 እሌታ ዘነብ........ገጽ 27—28 ፣ — የሕይወት ታሪክ—ብላታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ ገጽ 38
2 ተዘለ........ገጽ 23
3 እሌታ ወልደ ማርያም ገጽ 27—28



እኛም ከሌብነትና ከሽፍትነት በቀር ሌላ ሥራ የለንምና ይኸንኑ ሥራችንን ይፍቀዱልን» ሲሉ ጥቂት ሆነው አመለከቷቸው ። ርሳቸውም በኋላ በነዚህ ሰዎች ላይ የሚፈርዱትን በልባቸው ይዘው ፣» እኔም ለራሴ ታማኝ ዘበኛ ለመቅጠር የምፈልገው እንደናንተ የዚህ ልማድ ያለውን ጠንካራ ሰው ነው ። ይሁን እንጂ ፣ አሁን ያላችሁት ጥቂቶች ናችሁና ሌላ ባዕድ ሳትጨምሩ የዚህ ልማድ ያላቸውን ብቻ አጣርታችሁ ይዛችሁልኝ ኑ» ብለው አሰናበቷቸው ።

በዚህ ጊዜ ፣ መኳንንቱ እንደዚህ ያሉትን ሌቦች መግረፍ ነበር እንጂ ፣ ማሰናበት እንዴት ይገባል እያሉ ሲያስቡ ፣ በተባ ለው ቀን ሌቦቹ ተሰብስበው በፊታቸው ቆሙ ። ዐፄ ቴዎድሮስም እነሱ ብቻ መሆናቸውን ጠይቀው የእምነታ ምላሽ እንዳገኙ ፣ በዙሪያቸው የቆሙትን ወታደሮች አዘው በጥይት አንድ ሳይቀር አስደበደቧቸው ። ከዚያ ቀን አንሥቶ በንጉሡ ፊት የሣቅና የቀልድ ንግግር በፍጹም ቀረ ይባላል ። በእንደዚህም ያለ ቅጣት ጥቂት ዘመን ሰው እንደ ልቡ ወዲያና ወዲህ እያለ ኖረ ። በዚያ ጊዜ የነበሩትም የውጭ አገር ሰዎች ፣ እስከ ሩቅ አገር ለአደንም ለሌላም ጉዳይ እስከ ምሽት ድረስ ወዲያና ወዲህ ሲሉ ማንም ይነካቸው እንዳልነበረ ይነገራል ። መሬትም የመንግሥት ነው በማለት መኳንንቱንም ፣ ወታደሩንም ነቅለው በደመወዝ ብቻ እንዲተዳደር ሞክረው ነበር ።

ከዚህም ጋር ጉልተኛ መሳፍንትን እየነቀሉ ፣ በየአውራ ጃው መንግሥትን የሚያገለግሉና ለርሳቸው የሚታመኑትን እየሾሙ ለመደልደልና ማዕከላዊው መንግሥት እንዲጸና ምኞት ነበራቸው ። ለምሳሌ ፣ በጐጃም የሸፈቱትን መስፍኑን ደጃች ተድላ ጓሉን ሽረው ፣ ምስፍንና የሌላቸውን የራሳቸውን ታማኝ ራስ እንግዳን ለጐጃም ፣ የሸዋውንም መስፍን መርድ አዝማች ኃይሌን ፣ ወደፊት እንደምናነበው ፣ አስረው ከነጋሢው ከሣህለ ሥላሴ የማይወለዱትን አቶ በዛብህን ሾመው ነበር ። (1)

ዳሩ ግን ፣ በድል የያዙት አገር ጊዜ እየፈለገና እያንሰራራ የርሳቸውን መራቅ ምክንያት እያደረገ ይሸፍትባቸው ዠመር ።

1 Hist. Rol. J.B. Coulbeaux Vol. II pp. 425 - 424
የሕይወት ታሪክ ብላታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ ገጽ 27 ፣ 38

ከነዚሁም በወሎ እነ በሺር አህመድ ፣ በሸዋ የንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ልጅ ፣ የኃይለመለኮት ወንድም አቤቶ ሰይፉ (ሰይፈ ሥላሴ) ባማራ አገር የደጃች ክንፉ ልጅ ጋረድና ግንባሮ ካሣ ፣ በጐጃም ተድላ ጓሉና እነ ብሩ ኃይሉ ፣ በትግሬ የደጃች ውቤ ዘመድ ደጃች ንጉሤ ናቸው ። የነዚህም በየሥፍራው መነሣት ከካህናቱ ቅሬታ ጋር እየተሳሰረ ፣ እርሳቸው ላቀዱት የአንድነትና አዲስ የመሻሻል አስተዳደር ታላቅ እንቅፋት ሆኖ ነበር ። አሁን የአቤቶ ሰይፉን አነሣሥና በርሳቸው ላይ የተደረገውን ዘመቻ በዚህ ምዕራፍ ላይ እናነባለን ።

መርድ አዝማች ኃይሌ ካቤቶ ሰይፉ ጋራ ወንድማማች ቢሆኑም ፣ ከፍተኛ የሥልጣን ባላንጣነት ስለ ነበራቸው አስረዋቸው ነበር ። በኋላ ግን ፣ ሰይፉ ከሚስታቸው በስውር ከመብል ጋር በተላከላቸው ሞረድ እግር ብረታቸውን ሰብረው አመለጡ ። መርድ አዝማች ኃይሌም ፣ ከ1848 ዓ. ም. ዠምሮ እስከ 1851 ዓ. ም. ድረስ ሸዋን ሲያስተዳድሩ እንደቆዩ ፣ በዚሁ ዓመት ላፄ ቴዎድሮስ የሚሰጥ ያመት ግብርና ገጸ በረከት 1,000 ፈረስ 788 በቅሎ ፣ 1,000 ጥሬ ብር ፣ ብዙ ሠንጋ በሬ ፣ በሺ የሚቆጠር ልዩ ልዩ ሸማና (ልብስ) ዕቃ አምጥተው ለንጉሡ አቅርበዋል ። ንጉሡም በዚሁ ተደስተው ከፍ ያለ ግብር (ግብዣ) ለመርድ አዝማች ክብር ካደረጉ በኋላ ፣ አቶ ሥራህ ብዙ የሚባል የሸዋ ሰው ፣ «የንጉሡን ጠላት የዐመዴ በሽርን መልክተኛ በምስጢር ተቀብለህ አነጋግረህ ሸልመህ አሰናብተሃል» ብሎ ባደባባይ ከንጉሡ ላይ ከሰሳቸው ። ለዚህ መልስ መርድ አዝማች ፣ «መልክተኛው መምጣቱ እርግጥ ነው ። ነገር ግን አይሆንልኝም (ካንተ ጋር አላድምም) ብዬ መልሼዋለሁ» አሉ ። በዚህ ጊዜ ዐፄ ቴዎድሮስ ፣ «እንደዚህ ያደረገን ሰው ምን ያደርጉታል ?» የሚል ጥያቄ ለጉባኤው ቢያቀርቡ ፣ «ከጠላት ከተላላከ ይቀጣ» ብለው ፈረዱና ወዲያው በፍቅር የተገናኙት መርድ አዝማች ኃይሌ ከንጉሡ ጋር በጠብ ተለያይተው ፣ ያ ሁሉ ያቀረቡት ገጸ በረከት ዋጋ ቢስ ሆኖ ፣ እርሳቸውም ወደ ኮላሽ አምባ ተግዘው ታሰሩ ።(1)

ከዚህ በኋላ ፣ «ለሸዋ ማንን ብንሾምለት ይሻል ይመስልሃል ?» ብለው ንጉሡ ከሳሹን ሥራህ ብዙን ቢያማክሩት ፣

---

1 አለቃ ዘነበ ገጽ 37—38



«አቶ ዳርጌን ቢሾሙለት ሸዋ ደስ ይለዋል» ስለአለ ዳርጌ ተሾሙ ። በዚህ ጊዜ ሌላ ከሳሽ አሁንም የሸዋው አቶ ጃራ ብቅ ብሎ ፣ «ሥራህ ብዙ ከዳርጌ ጋር ውስጥ ለውስጥ ተማምለው ብርም ሰጥቶታል» ሲል ከሰሳቸው ። ዳርጌ «ገንዘብ ከሥራህ ብዙ ተቀብለሃልን ?» ተብለው በንጉሡ ተጠይቀው «አዎን» ብለው ስለ መለሱ ፣ ይኸው እንደ ጥፋት ሆኖ ታሰሩና ሥራህ ብዙ በተግሣፅ ታለፈ ።

በመጨረሻ ተመክሮ ፣ ተዘክሮ ለሸዋ ከነጋሢው ከሣህለ ሥላሴ የማይወለድ ጉበዝ ሰው ይሾም ተብሎ ስለ ተወሰነ ፣ በፊተኛው ጦርነት ቆስለው የተማረኩት አቶ በዛብህ ለአበጋዝነት ፣ አቶ አቦዬ ለአፈንጉሥነት ተሾሙ ። «ከርስዎ ሹማምንት መካከል አንድ ሰው እንደ ታዛቢ ይሰጠን» ብለው እነ አቶ በዛብህ ቢያመለክቱ ፣ «አሳላፊ ኪዳኑ ይመልከታችሁ» ብለው ሰጥተዋቸው ሦስቱም ጉዟቸውን ወደሸዋ ቀጠሉ ። የዚህን ወሬ አቤቶ ሰይፉ ከመርድ አዝማች ኃይሌ እስራት እንዳመለጡ በየቦታው ወዲያና ወዲህ እያሉ ጦር በማሳበር ላይ እንደ ነበሩ ሰሙ ። ገና አስቀድሞ እኔ ከደንበኛ ሚስት ከወይዘሮ በዛብሽ የተወለድሁት እያለሁ ፣ ከዕቁባቷ ከወይዘሮ ይመኙሻል ቡንኝ የተወለደው ኃይሌ መርድ አዝማች ተብሎ ለምን ተሾመ የሚል ቅሬታና ጠብ ነበራቸው ። መርድ አዝማች ኃይሌም ቀድሞውኑ አስረው ያስቀመጧቸውና ከሚስታቸው በተላከላቸው ሞረድ እግር ብረታቸውን ፈትተው ያመለጡት ሰበቡ ይኸው ነው ።

አሁን ደግሞ ፣ የባሰውን ከሣህለ ሥላሴ ምንም ዘር የሌላቸው አቶ በዛብህ ፣ ምንም እንኳን የመርድ አዝማችነት ማዕረግ ባይጨመር ፣ ተሾመው ወደ ሸዋ መምጣታቸውን ሲሰሙ ባይሆን የወንድሜን የኃይለ መለኮትን ልጅ ፣ ምኒልክን መልሰው እንደ ማስቀመጥ እንዴት ለበዛብህ ሰጡት ብለው ከምንጃር እስከ ኤፍራታ ያለውን ምሥራቅ ምሥራቁን እያሳበሩ አንኮበር ገብተው ተቀመጡ ። ብዙም የሸዋ ጦር በዙሪያቸው ተሰበሰበ ። እነ አቶ በዛብህ በራሳቸው ኃይል መስፍኑን ሰይፉን ለመመለስ እንደማይችሉ ተገንዝበው ይድረሱልን ብለው ወደ ዐፄ ቴዎድሮስ ላኩ ።

በዚህ ጊዜ ፣ ዐፄ ቴዎድሮስ በአማራ ሳይንት እነ ደጃች ትኩን ለማስገበር ከዚያም በወሎ ከዐመዴ በሽር ጋር የሚዋጉበት

ጊዜ ስለ ነበረ፣ ዐመዴ በሽርም ንጉሡ ሲመጡበት በፍርሃት ከወሎ ወደ በረሃማው ክፍል የተሰደደበት ወቅት ስለ ነበረ፣ እዚያው ወሎ ውስጥ እንዳሉ የነበዛብህ መልእክት ሲደርሳቸው በቶሎ ገሥግሠው በሰላ ድንጋይ በኩል ዐልፈው በ1852 ዓ.ም. አንኮበር ደርሰው፣ የርሳቸውና የሰይፉ ጦር በኃይል ተደበላልቆ ይዋጋ ዠመር። አቶ ሰይፉ ከቤጌምድር አንድ የጦር አለቃ መጥቶ የሚያዋጋ መስሏቸው ነበር እንጂ፣ የንጉሡ ነገሥቱን መኖር አልጠረጠሩም ነበር። በዚሁ ዓመት በጥቅምት 2 ቀን በተደረገው ጦርነት አንድ ከንጉሡ ጦር ውስጥ የተማረከ ወታደር ከፊታቸው ቀርቦ፣ «አዝማቹ ማን የሚባል ነው» ብለው ቢጠይቁት፣ «ጃንሆይ፣ ዐፄ ቴዎድሮስ ራሳቸው ናቸው» ብሎ በተናገረ ጊዜ፣ «ደንግጠው ጦራቸው ሳይሰማ እርሳቸው ከአንኮበር ቅጥር ወጥተው ሸሹ። ጦራቸው ግን፣ ውድቅት እስቲገላገለው ድረስ በርትቶ ተዋጋ» በማለት አለቃ ዘነብ ሲያስገነዝቡ፣ በበኩላቸው አለቃ ወልደ ማርያም ስለዚሁ ጦርነት እንደዚህ ሲሉ በራሳቸው አባባል መዝግበው ይገኛል።

«አቤቶ ሰይፉ፣ ከቅጽሩ ውስጥ ሙቅ ምድር ከሚባለው ነፍጠኛዎን (ነፍጠኞቸውን) ይዘው ጦርነት ዠመሩ ወደ ንጉሡ (ከንጉሡ ጋራ)። በዚህ ጊዜ በሚካኤል አራዳ አቀበቱ ላይ በታችኛው በነፍጥ እጅግ ሰው አለቀ . . . ንጉሡም የዚህን ጦርነት በአቤቶ ሰይፉ ቢያዩ እንደነዚህ ያሉት በፊት (1848) ተገኝተው ቢሆን ሸዋን አላያትም ነበር። የወታደርም ሙያ በአንኮበር ብቻ ይቆጠር አሉ። ነገር ግን፣ የእግዚአብሔር ፈቃድ አልቀረምና አቤቶ ሰይፉ የቴዎድሮስን ወሬ (መኖር) ሲሰሙ ሰዌን አላስጨርስም ብለው ከተማውን ለቀው ወደታች ወረዱ» ካሉ በኋላ፣ የንጉሡ ጦር ካሸነፈና ሰይፉ ከሸሹ በኋላ ስለ ተደረገው እንደዚህ ብለዋል። « . . . ይህን ጊዜ የንጉሡ ጦር በከተማው ገብቶ ዘረፈ። ይህ ከተደረገ በኋላ 'ምርኮኛ የያዝህ አምጣ' ብለው ዐዋጅ ነገሩ። እየተሰበሰበ በመጣ ጊዜ አቶ በዛብህ ተነሥቶ፣ 'ይህ የከዳ ነው፤ ይህ የኛ ነው' ብሎ በሁለት ወገን አቆመ። በዚህ ጊዜ ባለወግ(*) እየተጠራ መጥቶ ያንን የከዳ ሰውን ሁሉ ቀኝ እጁን፣ ግራ እግሩን እየቆረጠ ጨረሰ። ይኸን ጊዜ አልቃሽ፣

* ባለወግ ማለት ከንጉሣዊው ፍርድ በኋላ፣ እጅና እግር ለመቁረጥ ወይም ለመግደል ተግባሩ ሆኖ የተመደበ ያንድ ክፍል ጭፍራ ነው።



'ዐፄ ቴዎድሮስ እጅግ ተዋረዱ
የሸዋን ሰው ሁሉ እጅ ነሥተውት ሔዱ'

አለች ።» (¹)

ከሁለቱም ወገን የሞተውን በመገምገም፣ ዘነብና ወልደ ማርያም ይለያያሉ። ዘነብ «ሠራዊትዎን ግባበት አሉ ብዙ ነፍጥ፣ አራት መድፍ፣ ብዙ ዕቃ ተገኘ። ከንጉሡ ጋላ ብሩ የሺ ነፍጥ አለቃ (ሻምበል) የመቶ አለቆች ሁለት ሞቱ። ከጭፍራም አንድ(*) የሚሆን ሞተ። የቆሰለውም በነፍጥ በጦርም ሁለት መቶ የሚሆን ሆነ። ንጉሥ ቴዎድሮስም ከአቶ ሰይፉ የተያዘውን ሰው ሰባት መቶ የሚሆን እጁንና እግሩን ቆረጡት። ያቶ ሰይፉም እናትና እኅት ልጃቸውም ተያዙ» ብለው ያለፉትን ወልደማርያም አጠር አድርገው፣ ከአቶ ሰይፉ ወገን በጦርነት የሞተውን ሳይጠቅሱ ከንጉሡ ወገን በጦርነቱ ላይ አምስት መቶ፣ በጠቅላላው በጦርነትም፣ በመንገድም በማናቸውም የሞተው አንድ ሺ ከሰባት መቶ መድረሱን ያመለክታሉ። ሁለቱም ጸሐፊዎች ከምርኮ በኋላ ተይዘው እጅና እግራቸውን የተቆረጡትን (700) ከመጥቀስ በቀር ካቶ ሰይፉ ወገን በውጊያው ጊዜ በንጉሣዊው ጦር እየተጠቃ ያለቀውን አልጻፉትም። በዚያን ጊዜ እንደ ንጉሡ ወገን በሰይፉ በኩል ያለው ስለማይመዘገብ፣ መጻፉም አስቸጋሪ ይሆን ይሆናል።

በዚሁ ጊዜ ከጦርነቱ በኋላ፣ ከሸዋ ሊቃውንት በጸጋ ልጅነታቸው የጸኑት ተያዙ። የወታደሩ ክፍል በአቶ በዛብህ አስተናባሪነት እየቀረበ ቅጣቱን ሲቀበል፣ ከሊቃውንቱም ወገን እነ አለቃ እገሌ በጸጋነታቸው ጸንተው የጳጳሱንና የንጉሣችንን ትእዛዝ አፍርሰዋል፣ እነ አለቃ እገሌ ከሰይፉ ጋር ተመሣጥረዋል በመባል እንጉሡና እጳጳሱ ጉባዔ ፊት እየቀረቡ ከተፈረደባቸው በኋላ፣ እነ አለቃ አሥራት፣ እነ አለቃ ወልደ ሥላሴ ተቀጡ። (²) እንደዚሁም አቶ ሰሙ ንጉሥ የሚባሉ ያቶ ሰይፉ ባለቤት የወይዘሮ ገበያነሽ አባት እጅና እግራቸው በተቆረጠበት በዚያው ሰዓት ሞቱ። ያንኮበር አብያተ ክርስቲያናት በፊተኛው ዘመቻ ጊዜ የዳኑት ባሁኑ ጊዜ እየተበዘበዙ ተዘረፉ።

1 አለቃ ወልደ ማርያም ገጽ 20—21
* አንድ ያሉት አንድ መቶ ለማለት ይሆን?
2 የብላቴን ጌታ ኅሩይ ጽሑፍ ገጽ 77—78

እንደዚህ አድርገው ንጉሡና ጳጳሱ በኅብረት በወታደርነትም ፣ በሃይማኖትም የተነሣ ብዙ ሰው በመፍጀታቸው እንደዚህ ተብሎ በሁለቱም ላይ ተገጠመባቸው ።

«ባለድባብ ንጉሥ ፣ ባለጥና አቡን
እየዞሩ ፈቷት ኢትዮጵያን» (*)

በዚህ ዐይነት ፣ አቶ ሰይፉ የንጉሥ ኃይለ መለኮት ታናሽ ወንድም ፣ እንደ ወንድማቸው ላጭር ጊዜም ቢሆን በሸዋ የመንገሥ ዕድል ሳይገጥማቸው በወንድማቸው በመርድ አዝማች ኃይሌ ጊዜ እስራት ፣ ባቶ በዛብህ ጊዜ ጦርነትና ስደት ዕድላቸው ሆኖ ፣ አሁን ደግሞ በንጉሡ መኖር ተደናግጠው ከአንኮበር ከተማ ሸሽተው በረሃ ለበረሃ እየተንከራተቱ ጨርጨር ገቡ ። ወደ ሐረርጌም ለመሔድ አስበው ሳለ ፣ አሚሩ እንደማይቀበላቸው ወይም ተቀብሎ እንደሚያጉላላቸው በመጠራጠር ከጨርጨር ወደ እናታቸው ወደ ወይዘሮ በዛብሽ አገር ወደ መራቤቴ ተመለሱ ። ከመራቤቴም ወደ ቦረና(**) ሔደው ከባላባቱ ከአመሮ ዐሊ ጋር ተነጋግረው ወደ መርሐቤቴ (መራቤቴ) ሲመለሱ፣ ለመራቤቴ በፊተኛው ጊዜ እንደ እንደራሴ አድርገው ራሳቸው የሾሙት አቶ ክብረት የሚባል በዚህ በቀውጢው ቀን እምነቱን ክዶ ሜዳ ላይ ተዋግቶ ገደላቸውና ከሁሉም የሥልጣን ውዝዋዜ ተገላገሉ ። ከቴዎድሮስም ፣ ከበዛብህም አገዛዝ እንድናለን ብሎ በርሳቸው ተስፋ ያደረገው ሁሉ ተስፋ ቆረጠ ። አልቃሽም እንደዚህ ብላ የለቅሶ ግጥም ገጠመች ።

«የሸዋ መኳንንት እንግዲህ አትልፉ
ተመዞ የነበር ተከተተ ሰይፉ ።(1)»

- * ድባብ ለወግ ማዕረግ ከንጉሥ ጭንቅላት በላይ አሸከር ከኋላ ቆሞ የሚይዘው ትልቅ ጃንጥላ ዐይነት ነው ። ጥና ዐጠን ከሚለው ግስ የወጣ የዕጣን ማጠኛ ጳጳስም ቄስም በእጁ እያወዛወዘ ዕጣን የሚያጥንበት የቤተ ክርስቲያን መሣሪያ ነው ።
- ** ቦረና በወሎ ውስጥ ያለው እንጂ የሲዳሞው አይደለም ።

1 አለቃ ወልደ ማርያም ገጽ 21



# ምዕራፍ ዐሥራ ዘጠኝ

## የግብጽና የኢትዮጵያ ግንኙነት ባፄ ቴዎድሮስ ዘመን ፤ የአቡነ ቄርሎስ ጉብኝት በኢትዮጵያ

ኢትዮጵያና ግብጽ በአፍሪካ አህጉር በመልክዓ ምድር አቀማመጥ ተቀራራቢ ፣ ባንድ የአባይ ወንዝ ተጠቃሚ እንደ መሆናቸው መጠን፣በሁለት የጐረቤት አገሮች ላይ የሚደርሰው የመልካምና የመጥፎ የግንኙነት ውዝግብ በነርሱም ላይ በየጊዜው ደርሷል ። በኢትዮጵያና በግብጽ መካከል ከክርስትና በፊት የነበራቸውን ግንኙነት ወደጐን እንተወውና በክርስትና ዘመን ሁለቱም ከምዕራባውያንም፣ከምሥራቃውያንም አብያተ ክርስቲያናት ተለይተው በተዋሕዶ ሃይማኖት ስለ ተሣሠሩ ፣ በሁለቱ አገሮች መካከል የወዳጅነት ግንኙነት እንጂ ምንም የሚያጣላቸው ምክንያት አልነበረም ። እንዲያውም የግብጽ ፣ የኑብያና (ሱዳን) የኢትዮጵያ ሃይማኖት አባት ያው በእስክንድርያ መንበር የሚቀመጠው ሊቀ ጳጳስ ስለ ነበረ ፣ በነዚህ ሦስት አፍሪካውያን አገሮች ዘንድ ኅብረትና መተሳሰብ ነበር ።

በስድስተኛው መቶ ዓመተ ምሕረት በመካ መዲና መሐመድ ተወልዶ በክርስትና ጐን አዲስ የእስልምና ሃይማኖት ከመሠረተ ወዲህ ፣ በሰባተኛው መቶ ዓ. ም. ላይ በአሚሩ የሚመራው እስላማዊ ጦር ግብፅን በ640 ዓ. ም. እ. አው. አቆ. ሲይዝ ፣ ከዚህ ወዲህ ግብጽን የሚገዙት ሡልጣኖች በቀን ብዛት ቁራንን በሼኮቹ አማካይነት እያስተማሩ ቁጥሩ 12 ሚሊዮን የነበረው የግብጽ ክርስቲያናዊ ሕዝብ አብዛኛው እስላም ሆነ ።(1)ኢትዮጵያ ግን ፣ ከዐረቦች ወረራ ነጻ ሆና አርቶዶክሳዊ ሃይማኖት እንደ ያዘች የሃይማኖት ልዩነት በሚፈጥረው ቅራኔ በሁለቱ የቀድሞ ወዳጆች መካከል ዐልፎ ፣ ዐልፎ ጠብ እየተፈጠረ ይሔድ ዠመር ።

1 Coup d'Ceil sur la Chronologie de la Nation Egyp. J. Cataui pp. 183 - 189.

ቢሆንም ባንድ ወገን በሡልጣኖቹ ታጋሽነት ፣ በክርስቲያኖቹ ግብጻውያን ሃይማኖት አጥባቂነት በቁጥር ከጠቅላላው እስላማዊ ሕዝብ ቢያንሱም፣ ተዋሕዶ ሃይማኖትን የሚያዘወትሩት የግብጽ ወገኖችና የኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ግንኙነታቸውን እንደ ያዙ ብዙ ዘመናት ማሳለፋቸውን ፣ ለኢትዮጵያ የሚመጣው ጳጳስም ከግብጽ መሆኑን ባለፈው አመልክተናል ። በየዘመኑ ቅራኔው ሲከር የኢትዮጵያ ማስፈራሪያ አባይን እዘጋለሁ ፣ የሡልጣኑ መሣሪያ ደግሞ ጳጳሳችሁን አልሰድም የሚል ነበር ።

በዚህ ዐይነት ውዝግብ የሁለቱ አገር መሪዎች ሲጣሉ ፣ ሲዛዛቱ ፣ ሲታረቁ ፣ ገጸ በረከት ሲለዋወጡ ረዥም ዘመን (12—18ኛው መቶ ዓ. ም.) አሳልፈዋል ። የኢትዮጵያ በነጻነት መኖርና የግብጽ በዐረቦችና በቱርኮች በየፈረቃ መያዝ ለጉዳዩ መፍትሔ አላገኘለትም ። ከዐረብም ፣ ከቱርክም የመጣ ቢሆንም የግብጹ ገዥ እስላም በመሆኑ ፣ ለክርስቲያኑ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት የጐረቤት ባላንጣው ከመሆን አልዘለለም ።

በነራስ ዐሊ ፣ በነደጃዝማች ክንፉ ዘመን ከቱርክ ሡልጣን ተሾሞ መጥቶ ፣ መሐመድ ዐሊ በግብጽ ሥልጣኑን ደህና አድርጎ ከመሠረተና ግዛቱንም እስከ ሱዳን ከዘረጋ በኋላ ይኸው መሐመድ ዐሊ ዘለዓለማዊ አጨቃጫቂ የሆነውን ፣ ለግብጽና ለሱዳን ከነጭ አባይ የበለጠ ሕይወት የሚሰጠው ጥቁር አባይ የሚመነጭበትን የኢትዮጵያን አገር እይዛለሁ ብሎ ወረራውን እስከ ጐንደር አቅራቢያ ካፋጠነው ወዲህ ፣ ባለፈው እንዳመለከት ነው ፣ የግብጽን አጥቂነት ለመመከት በዘመኑ መሳፍንት የነበረው የኢትዮጵያ ደካማ ኃይል በራሱ ሊቋቋም ስለ አልቻለ ፣ ወረራው የተገታው በመሳፍንቱ አቤቱታ ፣ በእንግሊዞቹና በፈረንሳዮቹ ሃይታ መሆኑ አይጠረጠርም ።

መሐመድ ዐሊ፣ ራሱ ከቱርክ የበላይ ገዥነት ለመገላገል በሚመኝበት ሰዓት «ዋና መቀመጫ ከተማውን ፋዞግልንና ስናርን (ሱዳን) አድርጎ ፣ «ፈረንጆቹ ባይከላከሉኝ ኖሮ አበሻን ይገዜ በደንብ ለመከላከል እችል ነበር ። በቱርክ ብሸነፍም ይኸው ክፍለ ሀገር (ኑብያና ኢትዮጵያ) ደህና መሸሸጊያዬ ይሆን ነበር» ሲል ተናግሮ ነበር ። ([1])

1 Mili Trenta Cinque Anni-G. Massaya - Vol. I. pp. 72 - 73.



የሆነ ሆኖ ፣ መሐመድ ዐሊ በሱዳን አገር ላይ አገዛዙን በማጠንከር የግብጽን አቅዋም ከቱርክ ሡልጣን ቀንበር በመጠኑ ተቃውሞ ለማቅለል በአውሮፓውያን ኃያላን ዘንድ ድጋፍ በማግኘት ፣ ግብጽን ከርሱ በፊት ከነበሩት መሪዎች የበለጠ አሻሽሎ በደንበኛ መንግሥትነት እንድትታወቅ ስለ አደረገ ፣ በሕዝብ ዘንድ ሙን ኪድ ምስር (የግብጽ ገንቢ) እየተባለ ለመጠራት በቃ። በ1952 ዓ. ም. እ. ኤ. አ. በኮሎኔል ናስር መሪነት የቆመው ሬፑብሊክ እስኪሽራቸው ድረስ ግብጽን እየተከታተሉ በንጉሥነት ያስተዳድሩ የነበሩት እነ ፉአድ ፣ እነ ፋሩክ የርሱ ዘሮች ናቸው ።

መሐመድ ዐሊ ፣ በሽምግልና ዘመኑ ለሥልጣን ሳይሳሳ የጉልበቱን መድከም ፣ የአዕምሮውን መፍዘዝ ፣ የዐይኑን መደንገዝ ተገንዝቦ ልጁ ኢብራሂም በሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ሆኖ እንዲያስተዳድር ፈቀደለት ። ነገር ግን ፣ ኢብራሂም ሥልጣን ካወረሰው ከአባቱ ከመሐመድ ዐሊ በፊት እንደ አው. ቁ. በ1848 ዓ. ም. ሞተ ። መሐመድ ዐሊም ግብጽን 43 ዓመት (1805—1848) እ. አው. አቆ. ካስተዳደረ በኋላ ፣ ሞተና የልጅ ልጁ አባስ ሥልጣን ያዘ ።

አባስም የአያቱን የመገንባት አርአያ በመከተል ፈንታ አፍራሽ ሆነ ። ሥልጣን ከጨበጠ ጊዜ ዠምሮ የሃይማኖት መሪዎችን ለማስደሰት ፣ ራሱም ለመደሰት ሲል ወደ ሃይማኖት ጉዳይ በማዘንበል፣ የሥልጣኔውን ውጥን ሁሉ እንዲቆም በማድረግ ለመምህርነት የመጡትን ፈረንጆች ሁሉ አሰናበተ ። አባቱ ያቃለለውን የቱርክን የገዥነት ቀንበር እንዲመለስ አደረገ ። በዚህም የግብጽን በሥልጣኔ አለማደግ ምሁሩና ወጣቱ እያዘነበት ቆይቶ ፣ በቤተ መንግሥቱ እንዳለ ሳያስበው በስድብ እያዋረደ ያጉላላቸው የነበሩት የራሱ ዘበኞች አንቀው ገደሉት ።([1])

አባስ ሲሞት በሥልጣን የተተካው ሰይድ ባሻ የሚባለው አራተኛው የመሐመድ ልጅ ነው ። ሰይድ የሹመት አባቱን የአባስን ወደኋላ ጉታች አያያዝ በመንቀፍና ያያቱን የመሐመድ

1 Coup d'Ceil sur la Chronologie Egyp. J. Cataui pp, 363 - 375

ዐሊን አርአያ በመከተል፣ የተባረሩትን ፈረንጆች መልሶ የተቋረጠውን የሥልጣኔ ሥራ በአዲስ ኃይል እንዲንቀሳቀስ አደረገ ።

ግዛት በማስፋፋት ረገድ ፣ መሐመድ ዐሊ በኢትዮጵያ ላይ ሰንዝሮት የነበረውንና በእንግሊዝና በፈረንሣይ ተግሣጽ የቆመውን አጥቂነት ማስወገድ ብቻ ሳይሆን፣ ሰይድ ባሼ ቴዎድሮስ ከምትመራው ኢትዮጵያ ጋር መልካም የጉርብትና ወዳጅነት እንዲወጠን አመቺ ሁኔታ ለመፍጠር ይጣጣር ዠመር ። ማናቸውም ነገር ያለምክንያት አይደረግምና ምናልባት አባቱን መሐመድ ዐሊን ኢትዮጵያን ለመውረር የገፋፋው በመሳፍንቱ ዘመን የራስ ይማምና የደጃች ማሩ ፣ የራስ ዐሊና የደጃች ውቤ የርስ በርስ ጦርነት ፣ በጠቅላላ የመንግሥቱ ደካማነት ሲሆን ፣ አሁን አዲሱን መሪ ሰይድ ባሻን መንፈሱን አለስልሶ ከኢትዮጵያ ጋር ወዳጅነት ለመፍጠር ያስገደደው ያፄ ቴዎድሮስ የጉብዝናቸው ዝና በሱዳን በኩል ዘምቶ ካይሮ ላይ ተሰምቶ ስለ ነበረ ነው ።([1]) በዚህም ላይ ጦርነትና የልማት ፕላን ባንድነት ስለማይራመዱ ፣ ማናቸውም ብሩህ መሪ ባገሩ ውስጥ የልማት ፕላን ለመዘርጋት ሲያስብ በቅድሚያ ባገርና በጐረቤት ዘንድ ሰላም ማግኘት ፣ ለጦርነት የሚውለውንም ሀብት ለልማት ማዋል አስፈላጊነቱ ግልጽ ስለሆነ ፣ የሰይድ ሰላማዊነት ከዚህ ሁሉ ጋር የተያያዘ ሊሆን ይችላል ።

በዚህ ምክንያት ፣ ሰይድ ባሻ በወጠነው አዲስ የወዳጅነት ግንኙነት መሠረት ከዚያ በፊት የእስክንድርያ ፓትርያርክ ኢትዮጵያን ጐብኝቶ የማያውቀውን አሁን በርሱ ጊዜ ንግግር ተደርጎ የግብጥው ጥሪ ካፄ ቴዎድሮስም ፣ ከአቡነ ሰላማም ስለ ተላለፈለት ፣ ሊቀ ጳጳሱ አቡነ ቄርሎስ ኢትዮጵያን ለመጐብኘት መጡ ። ለአሁኑ ግንኙነት አመቺ ሁኔታን የፈጠሩት እንደኛ ቀብተው ዐፄ ቴዎድሮስን ያነገሡዋቸው አቡነ ሰላማ ናቸው። ከጠቡ በፊት ባሁኑ ወቅት አቡነ ሰላማና ዐፄ ቴዎድሮስ ፣ «እግዚአብሔር የሰጠኝ የሃይማኖት ልጄ ፣ ክርስቶስ የሰጠኝ የሃይማኖት አባቴ» እየተባባሉ በኅብረት ሥጋዊውንና መንፈሳዊውን ሥራ አብረው የሚያከናውኑበት ጊዜ ነው ። ሁለተኛም

1 የእስራት ዘመን በሐበሻ አገር ዶክተር ብላንክ እንደ ጻፈው ፣ ዳኘው ወልደ ሥላሴ እንደ ተረጐመው ገጽ 54—55



በንጉሡና በጳጳሱ ግብጥ የተጠሩት ፓትርያርክ ፣ የሃይማኖት ልጃቸው ቴዎድሮስና ገዥያቸው ሰይድ ባሻ እንዲወዳጁላቸው ከልብ ፈቅደዋል ።

ስለዚህ ፣ ሰይድ ባሻ ባገሩ ውስጥ የዠመረውን የሥልጣኔ ሥራ ወደ ፍጻሜ ለማድረስ ፣ ባገሩም ውስጥ ከጐረቤቶችም ጋር በሰላም ለመኖር የሚከተለው መንገድ ከነዚህ ከሃይማኖት አባቶች ፍላጐት ጋር ስለ ገጠመ ፣ ዐፄ ቴዎድሮስና ሰይድ ባሻ በወዳጅነት ለመቀራረብ እላይ እንዳልነው ያፄ ቴዎድሮስ የጋባዥነት ጥሪ ለፓትርያርኩ ተላከ ።

ፓትርያርኩም ጥሪውን በደስታ ተቀብለው ፣ በጉዳዩም ከግብጹ መሪ ከሰይድ ባሻ ጋር ተነጋግረው ከተስማሙበት በኋላ ፣ ለንጉሠ ነገሥቱ የሚቀርብ ብዙ የጦር መሣሪያና ሌላም ዕቃ ፣ እንደዚሁም እንደ አው. አቆ. በ1856 ዓ. ም. (1271 የሂጅራ ዓመት) የተጻፈ ደብዳቤ ይዘው ወደ ኢትዮጵያ መጡ ። ከመጣው ስጦታ ውስጥ በአልማዝ የተጌጠ መስቀል ይገኝበታል ።([1])

ዐፄ ቴዎድሮስም ለፓትርያርኩ ደንበኛ አቀባበል አደረጉላቸውና ንጉሠ ነገሥቱና ፓትርያርኩ ለአጭር ጊዜ በፍቅር ሰንብተው ሳለ ፣ በውይይቱ ጊዜ የሁለቱ አሳብ በጣም ከመራራቁ የተነሣ ወዲያው በወዳጅነቱ ፈንታ ጠቡ ተተካ ።

አቡነ ሰላማና አቡነ ቄርሎስ ፣ ሁለቱም ክርስቲያን በመሆናቸውና ሰይድ ባሻ እስላም በመሆኑ በሃይማኖት ይለያያሉ እንጂ፣ በሌላው ረገድ ሁለቱም ጳጳሳት በአካልም ፣ በመንፈስም ግብጻውያን መሆናቸውንና ዜግነታቸውም የግብጽ መንግሥት መሆኑን ዐፄ ቴዎድሮስ በደንብ አላጤኑትም ። በርሳቸው አስተያየት ሁለቱም በአሳብም ፣ በተግባርም ከርሳቸው ጐን ተሰልፈው ፣ እስላሙን የግብጽ መንግሥት ተቃውመው ጥያቄያቸውን እንዲያሟሉላቸው ነው ።

1 የእስራት ዘመን በአበሻ አገር ገጽ 55

በዚያ ሰዓት ፣ ያፄ ቴዎድሮስ አንገብጋቢ ጥያቄ ከመሐመድ ዐሊ ዠምሮ የግብጽ መንግሥት የሚያስተዳድራቸውንና በሰናር ወሰን ያሉትን ቀበሌዎች ፣ እንደዚሁም ቦጐስን ፣ መንሳን ፣ ሐልሃልንና ሐባብን ፣ ከ1517 ዓ. ም. ዠምሮ የቱርክ መንግሥት የያዛቸውን የምጥዋን ወደብና አካባቢውን ወደ ኢትዮጵያ ለማስመለስ ነው ። እንደዚሁም ከግብጽ ቁጥራቸው በርከት ያሉ እንደ ኢትዮጵያ በተዋሕዶ ሃይማኖት የሚያምኑት የግብጽ ተወላጆች ወደ ኢትዮጵያ መጥተው አገሪቱን እንዲያሠለጥኑ ፣ በነርሱም እየተተኩ በኢትዮጵያ የተስፋፉት የካቶሊክና የፕሮቴስታንትን ሃይማኖት የሚሰብኩት ጀርመኖችም ፣ እንግሊዞችም ፣ ሌሎቹም ካገር እንዲወጡ የሚል ሰፋ ያለ ዓላማ የያዘ ነው ።

ይኸ ዓላማ ባጠገባቸው ያሉትን ፣ እንደ ወዳጅም እንደ አሽከርም ሆነው የሚያገለግሏቸውን እንግሊዞቹን እነ ፕሎውዴንን ፣ ጀርመኖቹን እነ ማርቲን ፍላድን አስደንግጧል ። ፓትርያርኩን አቡነ ቄርሎስን ፣ ጳጳሱን አቡነ ሰላማን ዓላማው በግላቸው የሚያስደስታቸው ቢሆንም ፣ አሳቡን በተለይ የግዛቱን መልቀቅ ጉዳይ ፣ በፍጹም የግብጹ መሪና ባለሥልጣኖቹ እንደማይቀበሉት ስለሚያምኑና የነርሱንም የዜግነት አቀዋም የሚያበላሽባቸው መሆኑን በመረዳት በልስላሴ መቃወም ግዴታቸው ሆነ ። በዚህም ሰዓት ራሱ ሰይድ ባሻ ግዛቱን ሱዳንን ለመጐብኘት በካርቱም ስለ ነበረ ፣ ሁኔታውን በቅርብ ሆኖ እየተከታተለ ከፓትርያርኩም ጋር ይጻጻፍ ነበር ። ሊቀ ጳጳሱ ጉብኝታቸው እንደ ተከናወነ ወደ ኢትዮጵያ አሠልጣኝና ሠራተኛ እንዲልክ ጽፈውለት ነበር ።

በዚህ ምክንያት ዐፄ ቴዎድሮስ የነዚያንም ፣ የራሳቸውንም ጉልበት ከሚዛን ውስጥ ሳያገቡ በዚህ ጊዜ እንደ መሠረታዊ ዓላማ አድርገው የያዙት የግብጽንና የቱርክን ኃይል ከኢትዮጵያ ዙሪያ ለማስወጣት ፣ ከዚያም ዐልፈው ኢየሩሳሌምን ጭምር ለማስለቀቅ ስለሆነ ፣ የፓትርያርኩንና የሰይድ ባሻን መጻጻፍና መላላክ ሲሰሙ ተቆጥተው ፣ ፓትርያርኩንና ጳጳሱን በየድንኳናቸው እንደ እስረኛ አድርገው ፣ በዙሪያቸው አጥር አሳጥረው በዘበኛ ያስጠብቁዋቸው ዠመር ። የንጉሡና የጳጳሱ ጠብ ሁኔታው እንግሊዙን ፕሎውዴንን ፣ ጀርመናዊውን ፍላድን ሳያስደስት አልቀረም ። ምናልባትም ቴዎድሮስ ይኸን ዐይነቱን



እርምጃ እንዲወስዱ በቀጥታ ቢቀር በጐን ሳይገፋፉ አይቀርም ። ይሁን እንጂ ፣ በመጨረሻ ገላጋይ ያገር ሊቃውንትና ሽማግሌዎች በነገሩ ገብተውበት ሁለቱንም ወገኖች አዋቅሰውና አወያይተው በማስታረቅ አስማሟቸው ።

ይህን ጉዳይ አለቃ ዘነብ በሚከተለው ዐይነት አስፍረውት ይገኛል ። «..........በታኅሣሥ (1849)..........ጀን ሜዳ ሰፍረው ሳሉ (ቴዎድሮስ) ከምስር (ከግብጽ) ሊቀ ጳጳስ አባ ቄርሎስ መጡ ። ንጉሥ ቴዎድሮስም በሥርዓተ ንግሥ ተቀበሏቸው ። ሰንብተው ሳሉ ያለ ንጉሥ ፈቃድ ደብዳቤ ጥፈው ተገኙ ። ብዙ ዕቃ ፣ ብዙ ሠራተኛ ስደድ የሚል፣ ከምስሩ ጌታ ከሰይድ ባሻ ዘንድ ። ንጉሥ ቴዎድሮስም አባ ቄርሎስንና አባ ሰላማን ተቆጥተው ፣ ቤቱን አሳጥረው ፣(*) በውስጥ አግብተው ዙሪያውን ነፍጠኛ (ባለጠመንጃ) አስጠበቋቸው ። የአፈረዋናት (**) ካህናት ሔደው ከአደባባይ ቆሙ ። ንጉሥ ቴዎድሮስም «ምነው ፣ ምን ሆናችኋል?» ብለው ቢጠይቋቸው ፣ «ከሊቀ ጳጳስ አባ ቄርሎስና ከአባ ሰላማ ይታረቁልን ብለን ነው ። እኛ ንጉሥና ሊቀ ጳጳስ ማስታረቅ የሚቻለን ሁነን አይደለም ። ዳሩ ግን ፣ ዕርቅ የወደደን ንጉሥ ገበሬ ያስታርቀዋል ብለን ነው እንጂ» አሉ ። ([1])

ከካህናቱ ይኸን የመሰለ የዕርቅ አሳብ ሲቀርብላቸው ንጉሡ የዕርቁን ጉዳይ አልጠሉትም ። ምናልባትም መካርም ገብቶ የተከበሩትን እንግዳ በማሰራቸው ተጸጽተው ፣ ደግሞ እንደዚሁ መፍታትን ጠልተው የሚያስታርቃቸውን ከጐን ገፋፍተው ይሆናል ። በዚህ ምክንያት ከካህናቱ የዕርቁ አሳብ ሲቀርብላቸው ፣ እልኸኛው ቴዎድሮስ አሻፈረኝ በማለት ፈንታ «..........የአድባራቱን ካህን ሁሉ ጨምራችሁ አስታርቁኝ» ብለው ሌሎቹም ካህናት ተጨምረው አስታረቋቸውና ሰላም ሆነ ።

ከዚህ በኋላ ፣ ሊቀ ጳጳሱ በኢትዮጵያ ከታኅሣሥ እስከ ኅዳር (1856—57) እ.አው.አቆ. 11 ወራት ቆይተው ፣ ዐፄ ቴዎድሮስም የቀድሞ ጥያቄያቸውን ወደ ጐን ተወት አድርገው የሊቀ ጳጳሱ

---

* ወልደ ማርያም ድንኳን ብለውታል ።

** አፈረዋናት በደብረ ታቦርና በደራ ውስጥ የቅዱስ ገላውዴዎስና የሺሚ ማርያም አብያተ ክርስቲያናት ስለአሉ ፣ የነዚህ ካህናት ናቸው ።

1 አለቃ ዘነብ ገጽ 28—29

ጉብኝት እንዳስደሰታቸው ፣ በኢትዮጵያና በግብጽ የወዳጅነቱ ግንኙነት እንደሚቀጥል እምነታቸው መሆኑን ከመግለጽ ጋራ የተረፈውን ምኞታቸውን ሊቀ ጳጳሱና መልክተኞቻቸው በቃል እንዲያስረዱላቸው የሚገልጠውን ደብዳቤ አስይዘው ሊቀ ጳጳሱን አሰናበቱዋቸው ። በዚሁ ጊዜ 7 ፈረሶችና ልዩ ልዩ የኢትዮጵያ የጦር መሣሪያ ለሰይድ ባሻ የሚሰጥ ገጸ በረከት ይዘው ፣ አንድ መኰንንና ምሁሩ አለቃ ገብረየስ ተልከው ከሊቀ ጳጳሱ ጋር አብረው ወደ ግብጽ ሔዱ ።[1]

መሐመድ ሰይድ ባሻም ፣ ካፄ ቴዎድሮስ ዘንድ የተላከውን ደብዳቤውንም ፣ ገጸ በረከቱንም ሁሉንም ከተመለከካተ በኋላ በጉዳዩም ከአቡነ ቄርሎስ ጋር አሳብ ለአሳብ ተለዋውጠ እርሱም በበኩሉ ደብዳቤ ጽፎ ለመልክተኞቹ ለመስጠት በሚዘጋጅበት ጊዜ እንደ አለቃ ዘነብ አባባል ፣ «ንጉሣችሁ ምን ይወዳል?» ብሎ መልክተኞቹን ቢጠይቃቸው ፣ «የኛ ንጉሥ ስለ ፍቅር ብለው ላኩን እንጂ ገንዘብስ አይፈልጉም» ብለው መለሱለት ። እርሱም «እርሱ የሚወደውን እኔ ፣ እኔ የምወደውን እርሱ ካላ ከልኝ ያፍ ፍቅርማ እንደ ነፋስ ነው» ብሎ ለመላክተኞቹ ደብዳቤና አራት መድፍ ፣ ሁለት የግምጃ ፣ አራት የሺት(የጨርቅ) ድንኳኖች ፣ መቶ ጠበንጃ ላከላቸው ። ደብዳቤው ምን እንደሚል ባለቃ ዘነብም ፣ በሌላም መጽሐፍ ውስጥ ለማግኘት አልተቻለም ።

ዋናው መልክተኛም አለቃ ገብረየስ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰው መልእክታቸውን ፈጽመው ምንም ያህል ጊዜ ሳይቆዩ በተመለሱበት ዓመት በ 1851 ዓ. ም. ሞቱ ። እርሳቸውንም አለቃ ዘነብ ሊቀ ማዕምራን (የዐዋቂዎች ዐዋቂ ወይም አለቃ) ይሏቸዋል ። ዘነብ ከዚህ በላይ የተጠቀሰውን የሰይድ ባሻን አነጋገር ሰምተው ፣ በጽሑፍ ያሰፈሩት ከኝሁ ምሁር መልክተኛ ያገኙት መሆን አለበት ። የመጣውን የጦር መሣሪያና የድንኳኑን ገጸ በረከት ግን ፣ ለንጉሠ ነገሥቱ በቀረበበት ቀን በዐይናቸው አይተው ጸሐፌ ትእዛዝ እንደ መሆናቸው መጠን ራሳቸው መዝግበውት ይሆናል ።[2]

---

1 The Survival of Ethiopian Independence S. Robenson pp. 211-212

2 አለቃ ዘነብ........ገጽ 28—29 ፣ 31 ፣ 39—40



የሆነ ሆኖ ፣ ያፄ ቴዎድሮስና የመሐመድ ሰይድ ባሻ አሳብ በመሠረቱ የተለያየ ስለሆነ ፣ ያሁኑ ግንኙነት ሩቅ ሳይሔድ በዚሁ ገጸ በረከት በመለዋወጥ ላይ ብቻ እንደ ቆመ ይታያል ። ባንድ ወገን ሊቀ ጳጳሱ አቡነ ቄርሎስ በኢትዮጵያ በቆዩባቸው የ11 ወራት ጊዜዎች አንዳንድ ጊዜ ንጉሡ በመኳንንቶቻቸው ፣ እርሳቸውም በአቡነ ሰላማና በዕጨጌው ፣ በካህናቱ ታጅበው በክብር ፣ በደስታ ወደ ቤተ ክርስቲያን እየደረሱ ሲመለሱ ወይም አዲስ ተሠርቶ የሚመረቀውን ቤተ ክርስቲያን ባርከው ታቦት ሲያስገቡ ፣ ደግሞ አንዳንድ ቀን አቡነ ሰላማና ዐፄ ቴዎድሮስ በየርስቱ ፣ በየሥልጣኑ ሲጣሉና ሲጨቃጨቁ ፣ ሰላማ «ቴዎድሮ ስን የተከተለ ገዝቻለሁ» ብለው የንጉሡን ቁጣ ሲቀሰቅሱ ፣ ቄርሎስ ደግሞ «ግዝቱን እኔ ፈትቸዋለሁ» ብለው ቁጣውን ሲያበርዱ ፣ የንጉሡን ቁጠኝነት የብዙ ሰውንም ያለ ሕግ ቅጣት ተመልክተው አለኝታም ፣ ትዝብትም ተሸክመው ወደ አገራቸው የተመለሱ ስለሆነ ፣ ስላፄ ቴዎድሮስ ለመሪያቸው ለሰይድ መልካም ስሜት ያለበት ራፖር የሚሰጡ አይመስልም ።

በዚህ ምክንያት ፣ ዐፄ ቴዎድሮስም ለጊዜው ግድ ሆኖባቸው በገላጋይ ቄርሎስን ካሰሩበት ፈትተው ቢታረቁምና አስደስተው ቢሸኙም ፣ ለሰይድ ባሻም ገጸ በረከት ልከው ከርሱ የመጣውንም ቢቀበሉም ፣ የግብጾቹንና የቱርኮቹን ከኢትዮጵያ ዙሪያ የግስ ወጣቱን መሠረታዊ ምኞታቸውን በፍጹም አልተዉትም ። ይኸንንም ግዛት የመመለስና ያገር ፍቅር ዓላማቸውን በነፕሎውዴን ፣ በነ ዮሐንስ ቤል አማካይነት ከእንግሊዝ መንግሥት በሚያገኙት እርዳታና ኅብረት ወደ ፍጻሜ እንደሚያደርሱት ያምኑ ነበር ። ራሳቸውም በአውሮፓ የሠለጠኑት መንግሥታት እንደሚያደርጉት ፣ የንግድና የፖለቲካ ወኪል አስቀምጠው የአውሮፓን ሁኔታ የእንግሊዝንና የቱርክን መንግሥት መልካም ግንኙነት ገልጠ በጽሑፍ የሚያስረዳቸው ስለሌለ ፣ ባጠገባቸው ያሉት እንግሊዞችም ካገር እንዳያባርሯቸው ወይም እንዳያስሯቸው ትክክለኛውንና ሐቁን በመናገር ፈንታ ፣ አብዛኛውን ጊዜ በንጉሡ ፊት ሞገስ የሚያገኙበትን የራሳቸውን ምቾትና ጥቅም የሚጠበቅበትን ብቻ ይነግሯቸዋል እንጂ ፣ ከግብጽና ከቱርክ ጋር በግዛት ቢጣሉ እንግሊዝ አይረዳዎትም ብለው በሐቅ አይነግሯቸውም ። ፕሎውዴንና ዮሐንስ ከሞቱ ወዲህ ይህ ዐይነቱም የድብብቆሽ ሥራ በሚቀጥለው ጊዜ በግድ መገለጥ ሲኖርበት ፣

ያን ጊዜ በቴዎድሮስና በእንግሊዞች መካከል በመድበስበስ ዐመድ ውስጥ የተዳፈነ ወዳጅነት እያደር ይገለጥና በግድ ሁለቱ ወገኖች ወደፊት እንደምናነበው ፥ የተወጠነው ወዳጅነት ቀርቶ የጠቡን መሥመር ይይዛሉ ።

መሐመድ ሰይድ ግን ፥ ባገሩ ብዙ ዕውቀት በማስገባት ፥ የስዊስ ቦይን በማስቀደድ ፥ ወደቦችን በደንብ በማሠራት ፥ ተማሪ ቤቶች ፥ ሙዚዬሞች ፥ የጥናት ድርጅቶች አቋቁሞ ካፄ ቴዎድሮስ በፊት እ. ኤ. አ. በ1863 ዓ. ም. ስለ ሞተ ፥ በመንግሥቱ የወንድሙ የኢብራሂም ልጅ ኢስማኤል ባሻ ተከተለው ። በኢስማኤል ዘመን ፥ ዐፄ ቴዎድሮስ የኢትዮጵያን ግዛቶች የማስለቀቁ ነገር ሳይሳካላቸው በምኞት የቀረውን የቴዎድሮስን ዓላማ ይዘው የተነሡት ዐፄ ዮሐንስ ፥ በምን አኳኋን ከኢስማኤል ጋር እንደ ታገሉ ታሪክ መዝገቦታልና ወደፊት ዝርዝር ሁኔታውን እንመለከታለን ።



ሰይድ ፓሻ
(ከአባ ማስያስ መጽሐፍ)

# ምዕራፍ ሐያ

ነዋሪው የሥልጣን ሽሚያ ፤ የዋግሹም ገብረ መድኅን ስቀላት ፤ የፕሎውደን አሟሟት ፤ በጋረድና በንጉሡ መካከል የተደረገው ጦርነትና የሊቀ መኳስ ዮሐንስ መሠዋት ፤ የምርኮኛ መከራና ፍዳ

ዐፄ ቴዎድሮስ ጐጃምን ፣ በጌምድርንና ትግሬን ፣ ወሎንና ሸዋን በመላው በጦር ኃይል ድል አድርገው የኢትዮጵያን የንጉሠ ነገሥታዊና ማዕከላዊ ሥልጣን መሠረቱ ። የኢትዮጵያ ደቡባዊው ክፍል ሐረርጌ ፣ የሲዳሞና የኦሮሞ ወገኖች የሰፈሩበት ከአክሱም ዠምሮ በዛጉዬዎቹ ዐልፎ የመንግሥቱ መደብ ሸዋ በነበረበት ጊዜ ፣ ማለትም ከ13ኛው እስከ 16ኛው መቶ ዓመት በነዐፄ ዓምደ ጽዮን ፣ በነዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ዘመን ሁሉ ግራኝ አህመድ እስከ መነሣቱ ድረስ የኢትዮጵያ አካል እንደ ነበረ ሠንዶች በግልጽ ያሳያሉ ።

በዚህ ምክንያት ፣ ቴዎድሮስ ከሸዋ ዘመቻ በኋላ ወደ ደቡቡ ክፍለ ሀገር ዘመቻቸውን ለመቀጠል የጊዜው ሁኔታ ፣ የመሳፍንቱ በየአውራጃው መሸፈትና የወታደራዊው አቅዋም በደንብ አለመደራጀት ፣ ይኸ ሁሉ ተደራርቦ አላስቻላቸውም ። እንኳን የደቡቡ ክፍል የመካከለኛውና የሰሜኑ ክፍለ ሀገር እንኳን በዘመነ መሳፍንት ጊዜ፣ ሁሉም በየባላባቱ የቤቱ ጌታ መሆን ስለ ለመደና አሁን በቴዎድሮስ የሚመራው ማዕከላዊ መንግሥት ሥልጣን ሥር ሆኖ መተዳደሩ በሕይወት ላሉት መሳፍንት ወይም ለወራሾቻቸው የማይዋጥ ጉርሻ ሆኖባቸዋል ። ራሳቸው ቴዎድሮስ ባለፈው በወጣትነታቸው ጊዜ ለነራስ ዐሊ ፣ ያውም አማችነት ተጨምሮ ፣ መታዘዝን እምቢ ያሰኛቸው አንደኛ በሚያሳዝን አኳኋን የአገሪቱ መከፋፈል ፣ ሁለተኛ ያስተዳዳሪዎቹ የእነራስ ዐሊ ከዳዊት ፣ ከሰሎሞን አለመወለዳቸው መሆኑ በግልጽ ይታወቃል ።

አሁንም እርሳቸው በጦር ኃይል ሥልጣን ጨብጠው ፣ በጳጳስ ተቀብተው ዘውድ ቢጭኑም አመጣጣቸው ከቋራና ከደምቢያ ከነዳጃች ክንፉ ቤት ስለሆነ ፣ በጐጃም የነታላቅ ራስ ኃይሉ ቤት እነ ደጃች ተድላ ጓሉ ፣ በስሜን የነራስ ገብሬ ቤት እነደጃች ንጉሤ ፣ በዋግ በላስታ የዋግሹም ክንፉ ቤት እነ ዋግ ሹም ገብረ መድኅን ፣ በወሎ የነራስ ዐሊ ቤት እነ በሺር አህመድ (ወረሼህ) ፣ በእንደርታ የነራስ ወልደ ሥላሴ ቤት እነ ባልጋዳ አርአያ ፣ በሸዋ የንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ቤት እነ አቤቶ ሠይፉ ፣ ወዘተ...... ከደምቢያና ከቋራ ለመጣው ለደጃች ክንፉ ቤት ለቋረኛ ካሣ እንዴት እንገዛለን በማለት በመዠመሪያው የዘመቻ ወቅት እየተሸነፈ ተገዛሁ ቢልም ፣ መገዛቱ ግዴታዊ እንጂ ልባዊ አይደለም ።

ስለዚህ በጦር ከበድ ብለው ሲመጡበት ግማሹ አመንሁ ፣ ገበርሁ ብሎ ይገባና ከርሳቸው ያገኙን ሹመት ተቀብሎም ሳይቀበልም እንደቆየ እርሳቸው ዕልፍ ሲሉ ይሸፍታል ። የቀረውም በመሥጋት የንጉሡን ፊት አታሳየኝ እያለ ከመዠመሪያው ዠምሮ በሽፍትነት የቀጠለ አለ ። እንኳን ከሌላ የቅርንጫፍ ቤተሰብ የመጣው ቀርቶ ከራሳቸው ከደጃች ክንፉ ቤት የገዛ ዘመዶቻቸው እነጋረድ ክንፉ የርሳቸውን ንጉሥ መሆን አልተቀበሉም ። የጋረድን አሸፋፈት ምክንያት ሰበቡን በዝርዝር የሚነግረን ጽሑፍ ብናጣም ፣ በትክክልና በተለመደው ባህላዊ አወራረስ እኔ የደጃች ክንፉ ቀጥተኛ ልጅ እያለሁ እርሱ ወንድም ወይም የወንድም ልጅ ሆኖ ከደምቢያ ተነሥቶ እንዴት ይነግሣል? የሚል መሆን አለበት ። በዚህ ምክንያት እርሱ በኃይሉ እዚህ ንጉሠ ነገሥታዊ ሥልጣን ላይ ከደረሰ እኔንስ ለመሞከር ምን የሚከለክለኝ ነገር አለ ማለቱ ነው ። ከባዕድ ጠብ አንዳንድ ጊዜ የዘመድ ጠብ ስለሚበረታ ፣ ጋረድ እርሳቸውን ለመግደል እንደ ምን እንደጣረ በዚሁ ምዕራፍ እንመለከታለን ።

ስለዚህ ከሰሎሞን ይወለዳሉ ተብለው ታምኖባቸው በዙፋን እየተከታተሉ በሕጋዊ መንገድ በሙሉ ሥልጣን ይገዙ የነበሩት ነገሥታት ሥልጣናቸው በነራስ ስሑል ሚካኤል ፣ በነታላቅ ራስ ዐሊ ከተደመሰሰ ወዲህ ፣ በየመሳፍንቱ ልብ የተተከለው እልኸኛ መንፈስ «ማን ለማን ይገዛል» የሚለው ወይም እኔ ልግዛ የሚለው የሥልጣን ምኞት ነው ። በዚህ ሰበብ በ1790-92 ላይ በሥልጣን ሽሚያ የተነሣ ራስ ገብሬ የስሜኑ ፣ ራስ



መርድ የጐጃሙ ራስ ወልደ ገብርኤልና ራስ ዐሥራት የላስታዎቹ አራት ራሶች ባንድ ዠምበር ተዋግተው ራስ ገብሬ ብቻ ነፍሳቸውን አትርፈው በሕይወት ወደ አገራቸው ሲመለሱ ሦስቱ ራሶች ባንድነት ተነባብረው ከጦርነቱ ሜዳ ላይ ወድቀው ቀርተዋል ።[1] ያንዱ መከራ ለሌላው ደስታ ያመጣል እንደሚባለው ከዚህ እልቂት በኋላ ፣ ጉግሣና ወንድማቸው አሉላ በራስ ወልደ ገብርኤል ሥር ዘምተው ሳለ የታላላቆቹ ሬሣ እንደ ወደቀና ባለሥልጣን ሲጠፋ አሉላ ፣ ጉግሣን ፣ «የእንደራሴነቱን ሥልጣን ያዝ» ብሎ መከራቸው ። «ማን ሰጠኝ ብዬ ልያዝ?» ቢሉት«ረቢ (እግዚአብሔር) ሰጠኝ» ብለህ ያዝ አላቸው ። ያዙና ገናና መስፍን ሆነው 28 ዓመት አስተዳደሩ ።(*)

አሁንም ዐፄ ቴዎድሮስ የመዠመሪያውን ጥርጊያ ጐዳና ባለፈው እንዳነበብነው ከተወጡት በኋላ ፣ ደግሞ እንደገና እያንሠራራ በያለበት እንደ እንጉዳይ የሚበቅለውን የመሳፍንት ተወላጅ በሸፈተ ቁጥር በትዕግሥትና በፍቅር መሳቡም ፣ በጦር ኃይል አስገድዶ ለዘለቄታ ማሳመኑም አልሆነላቸውም ።

ዐፄ ቴዎድሮስ ወደ ሸዋ ዘምተው ሲመለሱ በጐጃም ሸፍተው ያገኙዋቸው ደጃች ተድላ ጓሉን ነው ። ደጃች ተድላ ትውልዳቸው እንደዚህ ነው ። እቴጌ ምንትዋብ ከምልምል ኢያሱ ወለተ እሥራኤልን ፣ ወለተ እሥራኤል ከደጃች ዮሴዴቅ ታላቅ ራስ ኃይሉን ፣ ኃይሉ ራስ መርድን ፣ መርድ ደጃች ጓሉን ፣ ጓሉ ደጃች ተድላን ይወልዳሉ ። ባንድ ወገን ደግሞ እኚሁ ራስ ኃይሉ ድንቅነሽን ፣ ድንቅነሽ ደጃች ጐሹን ፣ ጐሹ ደጃች ብሩን ይወልዳሉ ። አንባቢ እንደሚያስታውሰው ፣ ጐሹና ብሩ ባፄ ቴዎድሮስ ከተደመሰሱና የጐጃሙ ደጃዝማች ተድላ ወዳፄ ቴዎድሮስ ገብተው የአባታቸውን ግዛት ከአስመረቁ ወዲህ ፣ ንጉሡ ለዘመቻ ወደ ሸዋ ሲጓዙ ከወሎ ከድተው ወዳገራቸው ወደ ጐጃም ተመልሰው ሸፈቱ ። ለመሸፈት ካበቃቸው ምክንያት አንዱ ፣ ምናልባት የሸዋው ንጉሥ ኃይለ መለኮት ጦራቸው የማይደፈር ስለሆነ ፣ ዐፄ ቴዎድሮስ እዚያ ተሸንፈው ወይም ደክመው ሲመለሱ እኔ ከዚህ የጐጃምን ጦር ይዤ የደከመውን ጉልበታቸውን ባዲስ ጉልበት ተቀብዬ አሸንፋቸዋለሁ የማለት ተስፋ ይሆናል ።

1 ታሪከ ነገሥት ፓሪስ ቤተ መጻሕፍት በቁጥር 143 የተቀመጠው ገጽ 355—360

* እሉላን አንዳንድ መጽሐፍ የጉግሣ ልጅ ያደርጋቸዋል ።

ነገር ግን ፥ ከቴዎድሮስ ኋላ መሸፈት እንጂ በቴዎድሮስ ፊት ያን ጊዜ የሚቆምና ቢቆምም እስከ መጨረሻ የሚመክት ስለሌለ ፥ ለመይሳው ካሣም የተገኘ ድል ሁል ጊዜ ጉልበታቸውን ስለሚያጠነክረው ፥ ከሸዋ ቀንቷቸው እንደ ተመለሱ ደጃች ተድላን ሸፍተው ሲያገኙዋቸው የጐጃምን ግዛት ከጐጃም ለሚወለዱት ታማኛቸው ለራስ እንግዳ ሰጥተዋቸው ስለነበረ ፥ ዐፄ ቴዎድሮስ ከሸዋ መልስ በሐምሌ ወር ላይ ጐንደር እንደገቡ ራስ እንግዳና ደጃች ተድላ ተዋግተው ፥ እነ ራስ እንግዳ አሸንፈናል የሚል የምሥራች በነሐሴ ወር ልከውባቸው በጐንደር ደስታ ሆኖ ነበር ። ነገር ግን ፥ ደጃች ተድላ ሲመቻቸው ግዛት እየያዙ የቴዎድሮስ ጦር ሲመጣባቸው ወደ ጅበላ ተራራ እየወጡ በመደበቅ ለጠላታቸው ሳይመቹ ጊዜያቸውን ሲፈጁ ኖረው በመጨረሻ ሞት ገላገላቸው ።

እንደዚሁም ፥ የዋግና የላስታው ባላባት ዋግሹም ገብረ መድኅን ከሸዋ መልስ አገራቸውን አስመርቀው ከገቡ በኋላ ፥ መሸፈታቸው እንደ ተሰማ ንጉሡ ፊታቸውን ከጐንደር ወደ ዋግ አዞሩ ። በዚያን ጊዜ ተድላ ወደ ጀበላ በተደበቁ ቁጥር የንጉሡ ወታደር ጐጃምን በእሳት ማቃጠሉን ፥ የወሎም ሽፍታ በጥይት መደብደቡን በማውሳት ፥

«ጐጃምን ብንቆጣው በእሳቱ ተቀጣ
ወሎን ብንቆጣው በነፍጡ ተቀጣ
ይብላኝ ለወራሂ (ወረሂመኑ) ይብላኝ ለሰቆጣ»

ብለው ራሳቸው ትንቢታዊ ግጥም ገጣጥመው ፥ ወደዋግ ሹም ገብረ መድኅን መገሥገሣቸውን አለቃ ዘነብ ካመለከቱ በኋላ ፥ ከዚሁ አያይዘው ንጉሡ ወደ ዋግሹም ገብረ መድኅን ሲገሠግሡ የዚህን ወሬ የሰሙ የአገው ተወላጆች ራሳቸው ተዋግተው ዋግሹም ገብረ መድኅንን ፥ ቢቶደድ ብሩንና አባ ጫጐን ገና ንጉሡ ሳይደርሱ እንደ ማረኩዋቸውና ቴዎድሮስ ሦስቱን መኳንንትና ከጐጃም ተማርከው የመጡትን አስኔ ደረስን ፥ ጐለም ወልደ ሚካኤልንና ማሩ ስሎሞንን ጨምረው በግንቦት ወር (1850) ገረገራ ላይ በፍትሐ ነገሥት አስፈርደው ፥ እጅና እግራቸውን አስቆርጠው



በግራር ላይ እንደ ሰቀሏቸው ይደመድማሉ ። (1) በበኩሉ ዶክተር ብላንክ ዋግሹም ገብረ መድኅንን ተዋግተው እጃቸውን ለቴዎድሮስ የሰጡ የገዛ ዘመዳቸው ዋግሹም ተፈሪ መሆናቸውን ያመለክታል ።(2)

በዚህ ዐይነት ፥ በጐጃምና በላስታ ለጊዜው ቀንቷቸው ዐመጹ በሺርና ጓደኞቹ በወሎ የቀሰቀሱትን ሽፍትነት ከመደምሰስ ላይ ባሉበት ሰዓት፥ ባለፈው ምዕራፍ በዝርዝር ያነበብነው የአቤቶ ሰይፉን ሽፍትነት ከነአቶ በዛብህ መልክተኛ እንደ ሰሙ ወደ ሸዋ መዝመት ግዴታ ሆነባቸው ። ወደዚያም በዘመቱበት ሰዓት ቀደም ብለው የሸፈቱት ጋረድ ከንፉና ደጃች ንጉሤ እየተለያዩም እየተባበሩም የሽፍትነት አቅዋማቸውን ማጠንከራቸውን ወደ ሸዋ በዘመቱበት ሰዓትም ፥ እስከ መናገሻው ከተማ እስከ ጐንደር ገብተው ሀብትና ንብረት መዝረፋቸውን ሰሙ ።

ከሁሉ የበለጠ ያናደዳቸው ፥ የወዳጃቸው የምስተር ፕሎውዴን በጋረድ ሰዎች እጅ ክፉኛ ቆስሎ በዚሁ ቁስል የመሞቱ ነገር ነው ። ፕሎውዴን ሙሉ ስሙ ወልተር ቼችል ፥ ፕሎውዴን በካልኩታ (ሕንድ) የንግድ ሥራ ሲያካሒድ ቆይቶ ወደ እንግሊዝ አገር ከተመለሰ በኋላ ፥ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ከሎርድ ፓልሜርስተን ጋር ተነጋግሮ በ1848 ዓ. ም. እንደ ቆንሲል ሆኖ በምጥዋ በኩል አድርጎ ወደራስ ዐሊ ዘንድ መጣ ።(3) ሲመጣም ከርሱ ጋር ጆን ቤል የሚባለው ጓደኛውና ወዳጁ አብሮት ነበር። ሁለቱም ለራስ ዐሊ ወዳጆች ሆነው ወጣ ፥ ገባ እያሉ የንግድም የፖለቲካም ነገር ሲያካሒዱ በመካከሉ ራስ ዐሊ ባፄ ቴዎድሮስ ሲሸነፉ ሁለቱም ወደ ቴዎድሮስ ዞረው ዋና አማካሪዎችና ባለሟሎች ሆኑ ። ሁለቱም የኢትዮጵያን ሴት አግብተው ልክ እንደ ኢትዮጵያ መኳንንት ሆነው ዐፄ ቴዎድሮስን ያገለግሉ ዠመር ። ፕሎውዴን እንደ ኢትዮጵያ መኳንንት ጭፍራም ፥ ጋሻ ዣግሬም ነበረው ። የፈረስ ስሙም አባ ነፍሶ ይባል ነበር ይባላል ። (4)

1 አለቃ ዘነብ ገጽ 32 –34 በቴዎድሮስ የወጣትነት ዘመን ወንድማቸው ደጃች ክንፉ በዋግሹም ክንፉ (በዋግሹም ገ/ መድኅን አባት) ተጠቅተው ነበር ።
2 የአስራት ዘመን በአበሻ አገር ገጽ 172
3 ፉዜላ ያሳተመው ያጤ ቴዎድሮስ ታሪክ ገጽ 20—21
4 Historie de l' Abyssinie - A.H.M. Johnes - E. Monoroe pp. 174-176

ፕሎውዴን የእንግሊዝ ቆንሲል በመሆኑ ትንሽ ነጠል ገርበብ ቢልም ፣ ጓደኛው ዡን ቤል ግን ካፄ ቴዎድሮስ ልጥፍ ብሎ አገልግሎቱንና ምክሩን ከመለገስ ጋር በጦርነት ላይ ዠብዱ ስለ አሳየ ፣ የሊቀ መኳስነት ማዕረግ ይዞ መጠሪያ ስሙ እንግሊዝኛው ዡን ወደ ዮሐንስ ተለውጠ ሊቀ መኳስ ዮሐንስ እየተባለ ይጠራ ዠመር ።

ዐፄ ቴዎድሮስ ፣ ከሁለተኛው የሸዋ ዘመቻ እንደ ተመለሱ ባለቤታቸው እቴጌ ተዋበች ሞተውባቸው ደብረ ታቦር በሐዘን ላይ እንዳሉ ፣ የፕሎውዴን ባለቤት ከነጓዟ በጐንደር ከተማ ስለ ነበረች ፣ ፕሎውዴን ወደ ጐንደር ለመሔድ ንጉሡን ስንብት ቢጠይቅ የጋረድን መበርታት ከየሰዉ ሰምተውት ነበርና ፣ «አይሆንም ፣ ሽፍታ ያጉላላሃል ፤ ብቻህን አትሒድ» ብለው ቢመክሩት ፣ «እኔ አባ ነፍሶ! እኔን እንዴት ያለ ሽፍታ ይገድለኛል» ብሎ በመፎከር ከንጉሡ አስፈቅዶ ወደ ጐንደር ተጉዞ እከተማው አጠገብ ካለው ከቀሃ ወንዝ ሲደርስ የጋረድ ሰዎች ከቀኝና ከግራ ከተደበቁበት ወጥተው ፣ በሮምታ ተኩሰው ፣ ክፉኛ አቁስለው ፣ ካሽከሮቹም ላይ ብረታቸውን ቀምተው መሔዳቸውን ፣ ከዚያ እንደ ቆሰለ ወገኖቹ ወስደውት ዘጠኝ ቀን ያህል እንደ ቆየ መሞቱን ጸሐፊዎቹ ያረጋግጣሉ ። ለዡን የተባለ ሰው ደግሞ የበኩሉን ሲገልጥ የተመታው በጦር ከጐኑ ላይ መሆኑን ፤ እንደ ቆሰለም ተማርኮ ጐንደር ያለችውን ሚስቱን 2,000 ብር ላኪ ፣ አለዚያ እንገድለዋለን ብለው አስፈራርተው መቀበላቸውንና ከዚያ ፕሎውዴን መሞቱን ያመለክታል ።([1])

የዚህን ወሬ ዐፄ ቴዎድሮስ እንደ ሰሙ ምንም እንኳን የፈሩት ቢደርስ ፕሎውዴን ባንድ ወገን የእንግሊዝ መንግሥት ወኪል ቢሆንም ፣ በሌላ በኩል እንደ ግል ወዳጅ ሆኖ በማናቸውም እየመከራቸው ፣ ከዚህም ዐልፎ አብሮ ወደ ጦር ግንባር እየሔደ ውጊያ እስከ መካፈል ደርሶ ስለ ነበረና በዚህም ላይ በርሱ አማካይነት ከእንግሊዝ መንግሥት ብዙ የሚጠብቁት የእርዳታ ተስፋ ስለ ነበራቸው ፣ አሁን በጠላታቸው በጋረድ እጅ በመሞቱ አዝነው ለመበቀል ወሰኑ ። ሊቀ መኳስ ዮሐንስማ ደንበኛ ሐዘንተኛ ሆኖ እንደ ሰነበተ ጸሐፊው ሁሉ አብራርቶ ገልጦታል።

1 Theodore II Nouvel Empire D'Abyssinie pp. 104 - 105.



ከዚህ በኋላ ንጉሡ «ያንድ ሳምንት ስንቅህን ያዝ ። ጠንካራ በቅሎ ፣ ጠንካራ አጋሰስ ፣ ጠንካራ ፈረስ ይዘህ እኔ በመራሁህ ተጓዝ» የሚል ዐዋጅ አናግረው ወደ ጐንደር ገሠገሡ ። ጋረድ ክንፉም ያፄ ቴዎድሮስን ለጦርነት ተዘጋጅቶ መምጣት ሲሰማ ከጐንደር አካባቢ ከነጭፍራው ተነቃንቆ በዋልድባ በማይ ተክሊት ዐልፎ ወደ አዲ አርቃይ ሔዶ ሰፈረ ። የተከተለውም ጦር ካገሩ ከደምቢያና ከአካባቢው ከጭልጋ፣ ከወልቃኢትና ከወገራ ፣ ከደጋውም ፣ ከቆላውም የተጠራቀመ የሽፍታ ጦር ነበረው ።

ጋረድ ፣ ያፄ ቴዎድሮስ አጐት (እንደ ግማሾቹ ወንድም) የደጃች ክንፉ ልጅ እንደ መሆኑ በቀላሉ ይሸነፋል ተብሎ ስለ ማይገመት ፣ ንጉሠ ነገሥቱ የበረከተ ጦራቸውን አጠንክረው በለማልሞ ቁልቁለት ወርደው ድብ ባሕር ላይ ሰፍረው በታዩበት ጊዜ ከወገኖቹ ውስጥ ፣ «አንችላቸውምና እንሽሽ» ብለው ቢያማክሩት ፣ «ሳልዋጋ ብሸሽ ግዝት ያድርግብኝ» ብሎ በመሐላ ፎክሮ በማይ ተክሊት እንደ ተሰለፈ ሲጠባበቅ ፣ የጦር መላ በማወቅ ተወዳዳሪ የሌላቸው ቴዎድሮስ ቦታው ጥኑ ዱር (በረሃ) ስለ ነበረ ፣ የእግር ነፍጠኛ በግራና በቀኝ ሰደዱበትና ፣ «ተሰጥተህ (በልብህ ተኝተህ) ተቀመጥ ፣...... እኔ በመኻል (በመካከል) ስዠምር ፊትህን ሳታዞር ተሻማው» ብለው ትእዛዝ ለወታደሩ አስተላልፈው አደሩ ። ሲነጋ የቀኙ በቀኝ ፣ የግራው በግራ ፣ የመይሳው ልጅ (ቴዎድሮስ) በመካከል ሆነው ጦርነቱ ተዠምሮ ጋረድም ከነጭፍሮቹ እስከ እኩለ ቀን ድረስ በርትቶ መዋጋቱን አንድ ስማቸው ያልታወቀ ጸሐፊ ያመለክታሉ ።

ከዚሁ አያይዘው ጸሐፊው በመጨረሻ ጋረድ ጀርባውን ወደ ጫካው አድርጎ ፣ በፊቱ የንጉሡ ጦር አስጨንቆ በወጋው ጊዜ ንጉሡን ገድዬ እሞታለሁ ብሎ ማኸል ለማኸል በፈረስ ጮሬውን (ጦሩን) እየሰበቀ ፣ አንድ ዠግና ፈረሰኛ አስከትሎ ንጉሡ ወደ አሉበት እንደ ዕብድ ሽምጥ እየጋለበ ፣ ሰዉም ከፊቱ እየሸሸ መድረሱንና ደርሶም ንጉሡን በቀጥታ ሊወጋ ሲሰነዝር ሊቀ መኳስ ዮሐንስ ፣ «የማንን ጌታ ትገድላለህ?» ብሎ በጠበንጃ ደረቱን መትቶ በቅድሚያ እንደ ጣለው ፣ የጋረድ ዠግና ጓደኛውም በበኩሉ በፈረሱ ላይ እንዳለ ፣«አንተስ የማንን ጌታ?» ብሎ በጦር የሊቀ መኳስ ዮሐንስን ዐይን ወግቶ እንደ ገደለው ፤ በመጨረሻም ቴዎድሮስ ራሳቸው «የማንን ሎሌ ገድለህ

ልትሔድ ነው?» ብለው በጠበንጃ የዮሐንስን ገዳይ እንደ ጣሉት ያረጋግጣሉ ።[1]

ጦርነቱ በዚህ ዐይነት ዝግንነትና መበቃቀል ባለበት ግድያ ሲፈጸም ፣ ንጉሡ ባንድ ወገን የወዳጃቸውን የፕሎውዴንን ደም መበቀላቸውና በዚህም ጦርነት ደግሞ ፣ እስከ ሞት ድረስ የሚፈልጋቸውን የዘመድ ጠላታቸውን ለዘለቄታ መደምሰሳቸው ሲያስደስታቸው ፣ በሌላው ወገን ምትክ የሌለው የወዳጅ አሽከራቸው ዮሐንስ ሕይወቱን መሠዋቱ በጣም አሳዝኗቸዋል ። በርሱ መሞት ያዘኑት ንጉሡ ብቻ ሳይሆኑ በጐንደር ፣ በደብረ ታቦርና በጋፋት ያሉት የእንግሊዝና የጀርመን ተወላጆች ሁሉ አዝነዋል ። ምክንያቱም ፣ ዮሐንስ የንጉሡ ባለሟል እንደ መሆኑ መጠን፣የነርሱን ጉዳይ ለንጉሡ እየነገረ በማስፈጸም እንደ ጠበቃዋና ተከላካያቸው ነበር ።[2] መቼም አንድ የጦርነት ድል ፣ ለድል አድራጊው ደስታና ሐዘን የበረከተበት ስሜት ማሳደሩ ከጥንት የተለመደ ነው ። ደግሞም በዚህና በማናቸውም ጦርነት ከሁለቱም ወገን በውጊያው ላይ የሞተ በጣም ዕድለኛ ነው ማለት ይቻላል ። ምክንያቱም እያንዳንዱ ጠላቴን እገድላለሁ ወይም እማርካለሁ ብሎ ሲዋጋ ሳያስበው ረዘም ያለ የመንፈስ ሥቃይና ጭንቀትም ሳይደርስበት በድንገት ይሞታል ማለት ነው ። በጣም የሚያሳዝነው በጐጃም ፣ በወሎና በሸዋ እንደ ደረሰው አሁንም ከጋረድ ወገን ሆነው ሲዋጉ የተማረኩት ናቸው ። እነሱም ከተማረኩበት ደቂቃ ዠምሮ በጥይት ተመትተው ፣ ወይም በሰይፍ እግርና እጃቸው ተቆርጦ ነፍሳቸው እስኪታልፍ ድረስ የሚሰማቸውን ሥቃይ ለመገመት አያዳግትም ። ከጌታህ ጋር ተሰልፈህ የወጋኸኝ ጥፋቱ የመሪህ ነውና ምሬሃለሁ የሚለውን ዐዋጅ በዚህ ጊዜ ካፄ ቴዎድሮስ አደባባይ የሚጠብቅ የለም ። በውጊያ ላይ ለተማረከ የጠላት ጦር ይህ ዐይነቱ ምሕረት የሚበዛ ቢሆን እንኳ 40 (ዐርባ) ጊዜ ተገርፎ ፣ ሁሉም ይለቀቅ ወይም ወደ ንጉሥ ጦር ይቀላቀል ወይም ይታሰር ማለትም ከኃይለኛው ቴዎድሮስ ልብ የሚመነጨው በብርቅ ነው ። እንደዚህ ያለውንም የለሰለሰ ምክር በእንደዚህ ያለ የቁጣ ጊዜ ለንጉሡ የሚያቀርብ እንደ ንጉሥ ጠላት ይቆጠራል ።

1 ቶዜላ ያሳተሙት ገጽ 21—22
2 Ten Years with King Theodore in Abyssinia - Th. Wadmeir pp. 67 - 68



ስለዚህ ወዲያው ጋረድ ተመትቶ እንደ ወደቀ ቴዎድሮስ ከፈረሳቸው ላይ ወጥተው፣«ጌታህ ወድቋልና ተማረክ» ተብሎ በጋረድ ሰፈር እንዲለፈፍ አድርገው ወዲያው ለራሳቸው ወታደር ፣ «ምርኮኛ የሰደድህ ለአካላትህ እዘንለት» ይኸውም ማለት የጋረድን ወታደር ያልማረክህና ያላቀረብህ በአካልህ ትቀጣለህ ብለው ዐወጁና ወደ ደባርቅ ሔደው ሰፈሩ ። ሁሉም በጦርነት ላይ እያሳደደ የማረከውን ሰብስቦ አቀረበላቸው ።

የቅጣቱን ጉዳይ ጸሐፊው በራሳቸው አነጋገር እንደዚህ ሲሉ ገልጠውታል ። «......በሊቀ መኳስ ዮሐንስ ሞት ሲያለቅሱ ሰነበቱና ከጋረድ ጋር የተገኘውን ምርኮኛ ሁሉ እንደ ግድግዳ ማግረው (በደንብ አሰልፈው) በጠበንጃ ፈጁት ።[1] ደብድበው ታበቁ ወዲያ «የሊቀ መኳስ ደም ነው ፤ ጋረድ ሊገድለኝ ኑሮ (ሲል) ስለኔ ተለውጦ (ቤዛ ሆኖ) ዮሐንስ ሞተ» ብለው ተናገሩ...... የጋረድን ሠራዊት ደብድበው ከጨረሱ ወዲያ ፣ ከደባርቅ ወደ ጐንደር ሊነሡ አንድ ቀን ሲቀራቸው እንዲህ ብለው ዐዋጅ አስነገሩ ። «አራሽ እረስ ፣ ነጋዴም ነግድ ፤ ሽፍታ ፣ ወንበዴ ተው ግባ ፤ ይሻልሃል ። ተዚህ ቀደም የበደልኸው ፣ ቋንቋ የቆረጥህ ፣ ነፍስ የገደልህ ምሬሃለሁ ። በዱር በገደል ያለህ ግባ ። አልገባም ብለህ ዐዋጁን ያለፍህ (የሻርህ) ግን ፣ ለአካልህ እዘንለት ።»

ይኸን አድርገው ንጉሠ ነገሥቱ ከደባርቅ ወደ ጐንደር በድል አድራጊነት ግርማ ገቡ ። ከእንደዚህ ያለ ጦርነት በድል አድራጊነት ወደ መናገሻ ከተማው የገባ ንጉሥ ፣ በቤተ መንግሥቱ አዳራሽ ተቀምጦ ለመኳንንቱ ፣ ለሠራዊቱ ግብር ማግባት የኢትዮጵያ ባህል ስለሆነ ፣ ዐፄ ቴዎድሮስም ጐንደር ገብተው ለሠራዊታቸው ግብር አገቡ ። በመብልና በመጠጡም መካከል የቤተ መንግሥቱ ምርጥ አዝማሪዎች የዕለቱን ውጊያ የሚመለከት ፣ የጠላትን ስም እያራከሱ ፣ የንጉሡን ዝና እያነሣሡ በግጥም ማሞጋገስ የተለመደ ስለሆነ ፣ በዚሁ ግብር ጊዜ አንዱ የታወቀው የንጉሡ አዝማሪ በግብሩ ላይ ቆሞ እንደዚህ ብሎ ገጠመ ።

በጠበንጃ የተደበደቡት ቁጥራቸው እስከ 1500 ይደርሳል ይባላል ። አለቃ ወልደ ማርያም ገጽ 20—21

«ጋረድ ሞተ እንኳ ተቀበረ
ያንት ወንድም ነውና እንፈራው ነበረ»([1])

በዚህ ሰዓት ፣ ባዬ ቴዎድሮስ ላይ በመሸፈት ጋረድ ፣ የስሜንና የአገው ተወላጅ የሆኑት ደጃች ንጉሤና ወንድማቸው ደጃች ተሰማ ኅብረት አድርገው ስለ ነበረና አሁን ጋረድ ሲሞት ንጉሤና ተሰማ ብቻቸውን ተጋልጠው መቅረታቸውን ለማሳሰብ ይኸው አዝማሪ እንደዚህ ሲል አክሏል ።

«ይብላኝ ለንጉሤ ጀርባው ተከፈተ
ይብላኝ ለተሰማ ጀርባው ተከፈተ
የወንዶቹ (የነቴዎድሮስ) ወንድም አባ ገልብጥ ሞተ ።»([2])

ከጐንደር ሊቃውንትም ወገን ፣

«ቴዎድሮስ ነገሠና
እባብ ጠፋ በጐዳና
ወንበዴም ሔደ ምነና
ገበያችንም አለ ፈሰስ (ደመቀ)
ጋለሞታችንም አለች ፈርነስ (ተዝናናች)»

ተብሎ መገጠሙን ጸሐፊው በዚሁ በተጠቀሰው ገጽ ላይ መዝግበውታል ።

የፕሎውዴንና የወዳጃቸውን የሊቀ መኳስ ዮሐንስን ገዳዮች ፣ ከአባሪ ተባባሪዎቻቸው ጋር ሁሉንም እያስያዙ ሲገድሉ ፣ ከራሳቸው ደስታ ዐልፎ የእንግሊዝን መንግሥት እንደ አስደሰቱ ቆጥረውታል ። ለእንግሊዝ ባለሥልጣኖች በጻፉት ደብዳቤ ላይም ይኸንኑ ደጋግመው ጠቅሰውታል ። በተለይ ራፋኤል ባሮኒ ለሚባል የኢጣልያ ተወላጅ ለፕሎውዴን ወዳጅና

---

1 ቀዚላ ያሳተሙት ገጽ 20—23 ፣ አለቃ ወልደማርያም ገጽ 22—23 ወልደማርያም «ያንት ወንድም ነውና እንፈራው ነበረ» ያሉት የቀዚላው ጽሑፍ «እንሰጋው» ነበረ ይለዋል ። ትርጉሙ ያው ነው ።
2 ጋረድ ቴዎድሮስን ገልብጨ እነግሣለሁ የሚል ምኞት ስለነበረው የፈረስ ስሙ አባ ገልብጥ ተብሎ እንደ ነበረ ጸሐፊው ያወሳል ። ገጽ 23



ስለርሱም ሆኖ በምጥዋ ለእንግሊዝ መንግሥት እንደ ተጠባባቂ ወኪል ሆኖ ለሚያገለግለው የጻፉለት ደብዳቤ ይኸንኑ በትክክል የሚገልጽ ነው ።

«በስመ አብ...... ይድረስ ከአቶ ቦረኒ...... የምሥራች በእግዚአብሔር ኃይል ቀናኝ። ወዳጆቼን ቡላዲንን ፣ ዮሐንስን የገደሉ ሰዎች ፈጀኋቸው ። በእግዚአብሔር ኃይል ከሴት በቀር ከሰልፍ ያገኘሁትን ሁሉ ፈጀሁት ። አንድ አልተውሁም ። ወዲያው ተከታትዬ ተሻግሬ ሌባ ንጉሤን(*) በእግዚአብሔር ኃይል ከነሠራዊቱ ፈጀሁት — አክሱም ከሜዳው ላይ ። አንተም ቶሎ ናልኝ ። ከእንግሊዝ ንግሥት ከወዳጇ እግዚአብሔር ያደረገልኝን የደስታዬን ወሬ የምልክ ሰው የምሰድ ነኝና ቶሎ ናልኝ ፣ ይዘህልኝ የምትሔድ አለና ። የሊቀ መኳስ ዮሐንስን የአቶ ቡላዲንን ሰዎች እስታሁን ያቆየሁዋቸው ከኔ ሰው ካንተ ጋር ይሒዱ ብዬ ነው ።»

ማ ኅ ተ ም
ንጉሠ ነገሥት ቴዎድሮስ ዘኢትዮጵያ

---

* ደጃዝማች ንጉሤ ወልደ ሚካኤልን ነው ። ሌባ ያሉበት ምክንያት በሚቀጥለው ምዕራፍ እንደሚነበበው ነው ።

# ምዕራፍ ሐያ አንድ

*የፈረንሣይ መንግሥት ጣልቃ ገብነት ፤ የደጃዝማች ንጉሤ ወልደ ሚካኤል ለነግሥና ለወዳደቀ ፤ የእቴጌ ጥሩ ወርቀ ጋብቻና ወይዘሮ የተመኙ ።*

ከ16ኛው መቶ ዓመት ዠምሮ በተለይ ፣ በዚህ ዘመን ኃይል የሚሰማቸው ሥልጣኔን የተቀዳጁ የአውሮፓ መንግሥታት ፖርቱጋል ፣ ቤልዥክ ፣ ኤስፓኝ ፣ ጀርመን ፣ እንግሊዝና ፈረንሣይ ፣ በአፍሪካና በሌላውም ኋላ ቀር ክፍለ አህጉር በቅኝ አገዛዝ መስክ ተሠማርተዋል ። ከመካከለኛው ምሥራቅ ደግሞ የቱርክ መንግሥት ተነሥቶ በዚሁ ዘመን ጐረቤቶቹን የአውሮፓን የባልካን አገሮች ፣ የአፍሪካን ሰሜን በቀይ ባሕር ዳርና ዳር ያሉትን አገሮች ከአውሮፓውያኑ ኃያላን ጋር እየተፋለመ ይዟል ። የኢትዮጵያም ወደቦች ምጥዋና አካባቢዋ በቀጥታ በሱው እጅ ወይም በታዛዡ በግብጽ እጅ ከገቡ ቆይተዋል ።

ከነዚህ መካከል ፣ ዐፄ ቴዎድሮስ የኢትዮጵያን አንድነት ለመመሥረት ላይና ታች በሚራሯጡበት ጊዜ ፣ በኢትዮጵያ ላይ የንግድ ወይም የፖለቲካ ይዞታቸውን ለማጠንከር በከፍተኛ ፉክክር የሚሻሙት በተለይ እንግሊዞችና ፈረንሣዮች ናቸው ። ከዐፄ ቴዎድሮስ በፊትም የነርሱ ፉክክር ከዠመረ ቆይቷል ። የእንግሊዝ መንግሥት በ1834 ዓ. ም. ካፒቴን ሐሪስን ወደ ሸዋ ልኮ ከንጉሡ ሣህለ ሥላሴ ጋር የንግድና የወዳጅነት ውል ሲዋዋል ፣ የፈረንሣይ መንግሥት በበኩሉ በ1836 ዓ. ም. ሮሼ ዴሬ ኩርን ልኮ ከኝሁ ንጉሥ ጋር ተመሳሳይ ውል አድርጓል ። ከዚያ ወዲህ ደግሞ ፣ ፈረንሣይ በምጥዋ በ1841 ዓ. ም. የቆንስላ ቢሮ ከፍቶ እነጉዮም ለዣንን ወደ ራስ ዐሊ ሲልክ ፣ ቀጥሎ እንግሊዝ በ1850 ዓ. ም. በዚሁ በምጥዋ እነ ፕሎውዴንን ልኮ ቆንስላ ከፈተ ። ሁለቱም ቆንሲሎች ወደ ጐንደርና ወደ ደብረ ታቦር እየተመላለሱ ፣ ከነራስ ዐሊ ጋር የወዳጅነትና የንግድ ግንኙነት ለመፍጠር ሲታገሉ ቆይተው ፣ ራስ ዐሊ ተሸንፈው የመንግሥቱ ሥልጣን ባፄ ቴዎድሮስ እጅ ሲወድቅ ፣ ሁለቱም መንግሥታት

ያፄ ቴዎድሮስን ሞገስ ለማግኘት ይጣጣሩ ዠመር ። ነገር ግን እስከ ካሜሮን መምጣት ድረስ ባፄ ቴዎድሮስ ዘንድ የእንግሊዝ ይዞታ እየተስፋፋ ሔዶ ፣ የእንግሊዝ ቆንሲልና ዜጎች በንጉሡ ዘንድ ባለሟልነት አግኝተው እንደ ልባቸው ይወጡ ይገቡ ነበር ። በመጀመሪያ ጊዜ መልካም ግንኙነት በመፍጠር ቅድሚያ የነበረው ፈረንሣይ ፣ ከዐፄ ቴዎድሮስ በኩል የሚጠየቀውን የወዳጅነት ጥያቄ የፈረንሣይ ንጉሠ ነገሥት ናፖሊዮን 'ቴዎድሮስ ካቶሊኮችን ያጉላላል' በሚል ሰበብ ችላ ስላለው ፣ ቆንሲሉ ጉዮም ለዣን እስከ መታሰር ደርሶ ነበር ።([1])

በዚህ ዐይነት ፣ ባለፈው በምዕራፍ 6 እንደ ተመለከተው ፣ እንግሊዝና ፈረንሣይ ከቀድሞ ዠምሮ በቆንሲሎቻቸው ብቻ ሳይሆን ባገር ጐብኚ ፣ በነጋዴና ወንጌልን እናስተምራለን በሚሉ ሚሲዮናውያን አማካይነት ወደ ኢትዮጵያ ገብተው የበላይነታቸውን ለማጠንከር ፣ በተለይ ከሁሉም ክፍል ፣ በሚሲዮናውያኑ በኩል የበለጠ በሚሠሩበት ጊዜ ፣ በኢትዮጵያ መሳፍንት ዘንድ ደግሞ ቱርኮቹና ግብጾቹ በምሥራቅ በምጥዋ ፣ በምዕራብ በመተማ በኩል ዐልፎ ዐልፎ የማጥቃት ተግባር መፈጸማቸው ስለ አልቀረ ፣ ፈረንጆቹ ክርስቲያኖች ስለሆኑ ከዚህ ጥቃት ያድኑናል ፣ በነርሱም እርዳታ አገራችንን እናሠለጥናለን በሚል ተስፋ ከፈረንጆቹ ጋር የመቃረቡንና የመዛመዱን መንገድ በመጀመሪያው ወቅት አልጠሉትም ነበር ።

ዳሩ ግን ፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን በወረሰችው እምነት ፣ የክርስቶስ ባሕርይ ሰውነታዊና መለኮታዊ ባሕርይ ተዋሕዶ አንድ ሆኗል ስትል ፣ ባንድ ወገን ፈረንሣዮች የሚደግፏቸው የካቶሊክ ሚሲዮኖች በክርስቶስ ዘንድ ሁለቱ ባሕርይ ሳይዋሐዱ መኖራቸውን ስለሚያምኑ ፣ በሌላ ወገን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ወደ መንግሥተ ሰማያት ለመግባት ጸድቃን ፣ ሰማዕታት ያማልዳሉ ስትል ፣ የእንግሊዝ መንግሥት የሚደግፏቸው ፕሮቴስታንቶች ደግሞ ፣ ወደ መንግሥተ ሰማያት የሚገባው በበጐ ሥራ እንጂ በአማላጅነት አይደለም ስለሚሉ ፣ የነዚህ መንፈሳዊ ጠብና ክርክር የሥጋዊውንና የፖለቲካውን ጉዳይ እያበላሸው

1 Record of the Expedition - T.J. Holland p. 11



የኢትዮጵያ ሙንግሥት መሪዎችም ራሳቸው የሚያምኑበትንና የብዙ ሕዝብ ሃይማኖት ሆና ከአራተኛው መቶ ዓመት ዠምሮ የጸናውን ተዋሕዶ ሃይማኖት ለማስከበር ሲሉ ፣ በየአውራጃው ከተሠማሩት ሚሲዮናውያን ጋር ጠቡ እየተባባሰ ሔደ ። ከሚሲዮናውያኑም እያለፈ ጠቡ ወደ መንግሥትም መሪዎች ደረጃ እየደረሰ ፣ የተዠመረውን የሰላም ግንኙነት ሲያደፈርሰው ኖረ ።

በዚህ ምክንያት ፣ ዐፄ ቴዎድሮስም ከነገሡ በኋላ ፣ ካነገሡዋቸው ከጳጳሱ ከአቡነ ሰላማ ጋር እየተማከሩ በነፕሎውዴንና በነዮሐንስ ቤል ወዳጅነት ምክንያት ፣ የእንግሊዝን የፕሮቴስታንት ሚሲዮኖችን ለጊዜው ችላ ብለው ከኢትዮጵያ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጋር በጣም የሚፃረረውን ፣ ከዚህ በፊት ባፄ ሱስንዮስ ዘመነ መንግሥት (1599—1624) ብዙ ደም ያፋሰሰውን የካቶሊክ ሃይማኖት በያለበት በከረን ፣ በአካለ ጉዛይ ፣ በሠራዬ በወዲህኛው ትግሬ ተስፋፍተው ያስተምሩ የነበሩትን እንዳያስተምሩ ከለከሉዋቸው ። እነርሱ ግን ፣ በቆንሲሎቻቸው እየተደገፉ ፣ ባገራቸው ኃያልነት እየተመኩ ፣ ትእዛዝ እምቢ እያሉ በተዋሕዶ ሃይማኖት ያምን የነበረውን ያገር ተወላጁን በካቶሊክነት እያጠመቁ ፣ ቅስናም እየሰጡ ስላስቸገሩ ፣ በዚሁ ምክንያት በትእዛዝ አፍራሽነት ከሙካከላቸው ዋንዬው አባ ደዣኮቢስ የሚባሉት የፈረንሣይ ቄስ እስከ መታሰርና በካቶሊክነት የቀሰሱት እነ አባ ገብረ ሚካኤልም በእስር ቤት እስከ መሞት ደርሰዋል ።([1])

በዚህ ጊዜ ነው ፣ የፈረንሣዩ ቆንሲል ለዣን ካፄ ቴዎድሮስ በሚከራከርበት ጊዜ ፣ «.........የፈረንጆቹን አድራጐት ዐውቀዋለሁ ። አንድ አገር ለመያዝ ሲፈልጉ በቅድሚያ ሚሲዮኖች ይልካሉ ። ከዚያ እነርሱን የሚደግፍ ቆንሲል ፣ ቀጥሎ ደግሞ ቆንሲሉን የሚረዳ ወታደር ይላካል» ያሉት ።([2]) በማናቸውም ረገድ ባርደል በሚባል የፈረንሣይ ተወላጅ እጅ ወደ ናፖሊዮን ሦስተኛ ለላኩት ደብዳቤ መልስ ስላጡ ፣ ቆንሲሉ ለዣንም

1 Histoire Palitique et Rel. J.B. Goulbeaux Vol. II. Chap. III pp.43C-436.
2 Theodros et Nouvel Empire D'Abyssinie p. Gli Italiani in Africa......... Angelo Delboca. P 24

በዚሁ ጠብና ክርክር እስረውት ቆይተው በመጨረሻ እርሱም ተለቆ ወደ ምጥዋ ተመለሰ ። በዚህ ምክንያት ባፄ ቴዎድሮስ አገዛዝ በመጀመሪያው ዘመን (1847—53) የፈረንሣይና የኢትዮጵያ ግንኙነት እየተበላሸ በሔደ መጠን ፣ ከእንግሊዞቹ ጋር ያለው ግንኙነት በመጨረሻ እስኪበላሽ ድረስ እየሠመረ ሔደ ።

በትግሬ የካቶሊክ ሚሲዮንን የሚመሩት እላይ ስማቸው የተጠቀሰው ደዣኮቢስ ከፋ ውስጥ ለዚሁ ትምህርት የተቀመጡት ቄስ ሊዎን ዴዛ አቫንሸር በሐባብና በቦጐስ የታወቁት ሳፔቶ ወደ ፈረንሣይ ንጉሠ ነገሥት ወደ ናፖሊዎን ሦስተኛ ፣ ወደ ሣርዴኛው (ኢጣልያ) ንጉሥ ወደ ቪክቶር ኢማኑኤል ደብዳቤ እየጻፉ በቃልም እየተላላኩ ፣ «ቴዎድሮስ እኛን ያጠቁናል ፤ በርሳቸው ፋንታ በአገውና በትግሬ ሆኖ ፣ በርሳቸው ላይ የሸፈተውን አገው ንጉሤን ብትደግፉት ለእናንተም አገር ቆርጦ ለመስጠት ፣ እኛንም ለመደገፍ የተዘጋጀ ነው» እያሉ ማሳሰብ ዠመሩ ።

አገው ንጉሤ በአባታቸው በወልደ ሚካኤል የአገው ተወላጅ ስለሆኑ ፣ ራሳቸው ብዙ ጊዜ አገው ንጉሤ እየተባሉ ይጠራሉ ። እናታቸው ግን ፣ የስሜኑኛው የደጃች ውቤ እኅት የወይዘሮ መንታዬ ልጅ ስለሆኑ ፣ አገው ንጉሤ ከልጅነታቸው ጀምሮ ለደጃች ውቤ የዘመድ አሽከር ሆነው ሲያገለግሉ ቆይተው ፣ በ1847 ዓ.ም. ደጃች ውቤና ደጃች ካሣ (ቴዎድሮስ) ተዋግተው ፣ ካሣ አሸንፈው ውቤ ሲማረኩ አገው ንጉሤም የውጊያው ተካፋይ ሆነው ቆስለው እንደ ተማረኩ ፣ አለቃ ዘነብ ጽፈውት ኢኖ ሊትማን ያሳተሙት መጽሐፍ እንደዚህ ሲል ባጭሩ ይገልጻል «...... ንጉሤ ደጃች ውቤን ንጉሡ (ቴዎድሮስ) ተዋግተው ከቧሂት ላይ የያዟቸው ጊዜ ቆስሎ ነበር ። ንጉሡም ማሩን ፣ ቅቤውን ፣ ፍሪዳውን ዳርገውት አድኑት ብለው........... ሸዋ ሔዱ ።» ([1])

ከዚህኛው በመጠኑ ሰፋ አድርጎ ፣ የደራሲው ስም የማይታወቀውና ሉዊጂ ፉዜላ ያሳተሙት መጽሐፍ ስለ አገው ንጉሤ አሸፋፈት ቀጥሎ ያለውን አስፍሯል ። «በዐፄ ቴዎድሮስ መንግሥት ደጃች ንጉሤና ደጃች ተሰማ የሚባሉ ሁለት ወንድማማቾች ሸፈቱ ። እነዚህ ሁለቱ ያጤ ቴዎድሮስ ሎሌሎት (አሽከሮች) ነበሩ ። በሳህላ መሬት ሽፍታ ሆነው ተቀመጡ ።.......... ደጃች ንጉሤም ጥቂት በጥቂት ሰው ሰበሰቡና ወደ ትግሬ ተሻገሩ ። የስሜን ፣ የሳህላ ፣ የልዋሌ ፣ የጠለምት ወታደር እበላለሁ እያለ ተከተላቸውና ወታደር በዛ ። ትግሬ ገብተው ጥቂት እንደ ቆዩ ደጃች ኃይለ ማርያም (ኃይሉ) አባ ጐርፌ ፣ የራስ አርአያ ወንድም ፣ የትግሬ ገዥ ነበሩና ከአገው ንጉሤ ጋር ፣ በሐውዜን ወገን ሀራህር በሚባል ሥፍራ ገጠሙ ፤ እጅግ ብርቱ ጦርነት ተዋግተው በዚያን ጊዜ ደጃች ኃይለ ማርያም ሞቱ ። ደጃች ኃይለ ማርያምን ድል አድርገው አገው ንጉሤና አገው ተሰማ ሲባሉ የነበሩ ሁለቱ ወንድማማች ደጃች ንጉሤና ደጃች ተሰማ ተባሉ ። ጠቅለው ትግሬን ያዙ.........» (*)

እላይ ከሁለቱ ወንድማማቾች ዋነኛው የበላይ አዛዥ ንጉሤ ናቸው ። ትውልዳቸው አገው መሆኑ ነው ። ንጉሤ ከቴዎድሮስ ሲሸፍቱ የተከተላቸው የሳህላ ፣ (ጃናሞራ አውራጃ ግዛት ውስጥ) የልዋሬ (በየጁ አውራጃ) የስሜንና የወልቃይት ፣ የጸገዴ ፣ የጠለምት ሕዝብ ያባትና የእናታቸው ወገን ስለሆነ ፣ ወደ ትግሬ ገብተው ደግሞ በዚያው ግዛታቸውን ያጠበቁት ከርሳቸውም ከቴዎድሮስም በፊት የእናታቸው አጐት ደጃች ውቤ ከስሜንና ከወገራ ጋር ትግሬንም ጠቅለለው እስከ ምጥዋ ይገዙ ስለ ነበረ በዚያ ሳቢያ መሆን አለበት ።

የሆነ ሆኖ ፣ ከአያታቸው ከወይዘሮ መንታዬ ወንድም ፣ ከደጃች ውቤ ጋር ሆነው ቴዎድሮስን ወግተው ቆስለው ከዳኑና ላፄ ቴዎድሮስ ከገቡ በኋላ ፣ እንደገና ባፄ ቴዎድሮስ ላይ ለመሸፈት ያበቃቸው ትክክለኛው ምክንያት አይታወቅም ። በግምት ራሳቸው በተካፈሉበት ጦርነት የራሳቸውም መቁሰል ፣ የጌታ ዘመዳቸው የደጃች ውቤ መሸነፍና ፍጻሜያቸው ቂሙ ከልባቸው አልጠፋም ይሆናል ። በዚህ ጐን ደግሞ ፣ ንጉሤ ከጠባያቸው ደግ ሰው መሆናቸውና ባፄ ቴዎድሮስ ትእዛዝ በየጊዜው የሰው እጅና እግር እየተቆረጠ መቀጣቱ ያሳዘናቸው መሆኑን ይኸው እላይ የተጠቀሰው መጽሐፍ እንደዚህ ሲል ይጠቅሳል ። «ጠቅላዩ ደጃች ንጉሤ ናቸው ። እርሳቸውም ጭራሽ ርኅሩኅ

1 The Chronicle of King Theodore of Abyssinia Enno Littmann pp. 46

* ኃይለማርያም ያኔ ዮሐንስ ታላቅ ወንድም የጉግሣ ልጅ እንጂ የዐፄ ዮሐንስ ወንድም አይደሉም ።

ነበሩ ይላሉ ። ይቆረጥ ይብቃ (ጥፋተኛው) ተብሎ የተፈረደበት እንደሆነ «አያ! እግርና እጅ በውሃ (እንዳትክልት) አይበቅልም ! ገርፈህ ስደደው» ይሉ ነበር ይላሉ ። ይሙት በቃ ቢፈረድበትም (ለተፈረደበት ከራሳቸው) ገንዘብ ይከፍሉ ነበር ።»[1]

ዐፄ ቴዎድሮስ በነገሡበት ዘመን በፈረንሣይ አገር ንጉሠ ነገሥቱ ናፖሊዎን ሦስተኛ ሲሆን ፥ በእንግሊዝ አገር ንግሥት ቪክቶሪያ ናቸው ። ኢጣልያኖች ግን ግማሾቹ እርስ በርሳቸው የተከፋፈሉ ብቻ ሳይሆን ፥ ሰሜኑንና ምሥራቅ ሰሜኑን አውስትሪያ ፥ ምዕራቡን ሳቮያና ፒዬሞንቴ የሚባሉትን ፈረንሣይ ሲገዙዋቸው ፥ ከነዚሁ መንግሥታት ጋር በሰላምም ፥ በጦርነትም እየተከራከሩ ሣርዴኛና ፒዬሞንቴን አዋሕደው በቅድሚያ በካርሎ አልቤርቶ መሪነት ፥ ቀጥሎ በልጁ በቪክቶር አማኑኤል ዳግማዊ የሚመራ ንጉሣዊ አገዛዝ መሥርተዋል ። በዚሁም ጊዜ ካሚልዩ ቤንዝ ኮንቴ ዲ ካቩር የሚባለው ጠቅላይ ሚኒስትር ሆኖ ይመራል ። (1848—1859)

ደጃች ንጉሤ ባለፈው እንደ ተመለከትነው ከስሜን ፥ ከወልቃይትና ከጠገዴ ዐልፈው ተምቤን ገብተው ፥ ዐፄ ቴዎድሮስ የሾሟቸውን ደጃች ኃይሉን (ኃይለ ማርያምን) በጦርነት ገድለው ፥ ትግሬን ከጠቀለሉ ወዲህ ደጃዝማችን የገደለ ፥ ደጃዝማች መባል በኢትዮጵያ የቆየ ልማድ ስለሆነ ፥ ከዚህ በኋላ ደጃዝማች ንጉሤ እየተባሉ ቆይተው ፥ በመጨረሻም «ንጉሤ የኢትዮጵያ ንጉሥ ወይም ደጃች ንጉሤ ንጉሥ ዘብሔረ ኢትዮጵያ» እያሉ በራሳቸው ፈቃድ መጠራት ፥ በዚሁ ያንበሳ ምልክት ያለበት ማኅተምም አሠርተው መጻጻፍ ዠመሩ ።

ላጭር ጊዜ ቴዎድሮስ በሌሉበት ሰዓት ጐንደርን እስከ መውረር ደርሰዋል ። አንድ ጊዜ ከሸፈቱ በኋላ ፥ ያፄ ቴዎድሮስን ኃይል ያውቁታልና በማናቸውም ረገድ እርዳታ ለማግኘት ሲሉ ፥ «እኔ በቴዎድሮስ ምትክ ንጉሠ ነገሥት ብሆን ባገር ሰላም

1 ያጤ ቴዎድሮስ ታሪክ ስሙ ከማይታወቅ ኢትዮጵያዊ የተጻፈና ሉዊጂ ፋዜላ ያሳተመው ገጽ 24—25 ።
Rassegna di Studi Ethiopci Volume VIII - L' Ambasciata Francese a Negusse - Luioi Fusella pp. 176 - 191.



እንዲሰፍን ፥ ንግድ እንዲስፋፋ ፥ ያውሮፓ ዕውቀትና ሥርዓት ባገሬ እንዲገባ ፥ እናንተም ካቶሊኮቹ እንደ ልባችሁ ሃይማኖታችሁን እንድታስፋፉ አደርጋለሁ ። በቀይ ባሕር ዳርም የንግድ ማስፋፊያ ፥ የመርከብ ማሣረፊያ የወደብ መሬት ለፈረንሣይም ፥ ለኢጣልያም እሰጣለሁ» እያሉ ተስፋ መስጠታቸው አልቀረም ። በዚህ ምክንያት ፥ እላይ ስሙን የጠቀስነው ሊዎ ዲዛ ቫንሸር የሚባለው ሚሲዮናዊ በቅድሚያ ከሣርዴኛው ጠቅላይ ሚኒስትር ከኮንት ካቩርና በተለይ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ባለሥልጣኖች ከነኔግሪ ጋር ተጻጽፎ ከተስማማ በኋላ ፥ ለንጉሤም የመረዳዳት የውል ረቂቅ አቅርቦ ፥ እንደዚሁም ለሣርዴኛው ንጉሥ ደብዳቤ ቢጽፉ ከቴዎድሮስ ጋር ለሚያደርጉት ውጊያ ሁሉ እርዳታ ሊያገኙ ይችላሉ በማለት ደብዳቤ እንዲጽፉ አድርጓቸዋል ። እርሳቸውም ያፄ ቴዎድሮስን ኃይልና ጭካኔ ፥ በፊታቸው የገጠማቸውን መሳፍንት ሁሉ ደጃች ውቤን ሳይቀር በቀላሉ እያሸነፉ የነገሡ ፥ ከነገሡም ወዲህ አንድም በፊታቸው ቆሞ ለዘለቄታ የመከተ አለመኖሩን ስለሚያውቁ ፥ «እኔስ ከኝህ ንጉሥ እድን ይሆን ወይስ እሞት ይሆን?» እያሉ በሚሠጉበት ጊዜ ፥ እንደ ተመከሩት በቅድሚያ ለሣርዴኛው ንጉሥ «..........ደጃዝማች ንጉሤ ፥ ንጉሥ ዘብሔረ ኢትዮጵያ ..........የእሮም አገር ሁሉ ጳጳስ የአቡነ ማስያስ ቄስ መልክተኛ አቡነ ልዮኔ..........ከኔ ሠፈር መጣ ።..........የምትፈልገውም ነገር ሁለታችን ያንድነት ፍቅር እንድናደርግ ፥ የነጋዴን ሥራት ሁሉ እንድናቀና መሆኑን ሰምቼ እጅግ ደስ ብሎኝ ነው ። ነገር ግን ያንተ ወኪል መጥቶ ይኸን ሥራት ቶሎ ይፈጽም ።..... እኔም የእግዚአብሔር ፈቃድ ቢሆን እንደ ብርሃን የሆነ የአውሮፓ ሥራት ወዳገሬ ኢትዮጵያ እንዲደርስ ፥ በነጋዴ ሥራት በሌላውም ነገር ሁሉ እንዳገርህ እንዲሆንልኝ ። ይህም እስኪፈጸም ድረስ በሰቂለ ሕሊና ልኖር ነኝ» (*) የሚል ደብዳቤ ጽፈው ላኩ ።[1]

ከደብዳቤው ግርጌ ያንበሳ ምልክት ያለበት ማኅተም ፥ ከአናቱ ላይ የደብዳቤው ቀን እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር 1851 ዓ. ም. የካቲት 4 ቀን መሆኑ በግልጽ ይታወቃል ።

* በሰቂለ ሕሊና ማለት ፥ ይኸ ምኞቴ እስኪፈጸም ለልቤ ዕረፍት ሳላገኝ እጠብቃለሁ ማለት ነው ።
1 Archivio Storico del Ministero Degli Affari Esteri Pozizion. ROMA

ይህ ዘመን ፣ የስዊስ ቦይ ሥራውን የጀመረበት ጊዜ ስለ ነበረ ፣ በዚሁ ቦይ አማካይነት እንደ ሌሎቹ ኃያላን የሣርዴኛው ንጉሥም ወደ አፍሪካ መላክተኞቹን እየላከ ንግድ ለማስፋፋት ፣ ቢቻልም በዚሁ በኤርትራ ባሕር አካባቢ እግሩን የሚያሳርፍበት መሬት ለማግኘት መመኘቱን ይኸው ሊዎን ዴዛቫንሸር ገልጸላቸው ነበር ። ንጉሤም በበኩላቸው የጦር መሣሪያም ፣ ማኖቻቸውንም እርዳታ ለማግኘት ሲሉ በዋጋ ቤት 4,500 የማሪያ ቴሬዛ ብር ተቀብለው በቀይ ባሕር ዳር ፣ በዙላና በአራፋሌ አጠገብ መሬት ቆርሰው ለመስጠት ፈቃደኛ መሆናቸውን ይኸው እላይ ስሙን የጠቀስነው ቄስ ያመለክታል ። ([1])

ዳሩ ግን ፣ የሣርዴኛ ንጉሥ ገና ያገሩን የኢጣልያን አንድነት ለማቋቋም ከሮማ ጳጳስ የሚጨቃጨቅበት ፣ ከየአውራጃው መሳፍንትና ፕሬዚዳንቶች ጋር የሚዋጋበት ጊዜ ስለ ነበረና የወታደሩም ድርጅት ፣ የሀብቱም አቅም ዝቅተኛ በመሆኑ ፣ እንደዚሁም በደንበኛው ንጉሠ ነገሥት ቴዎድሮስ ፊት የደጃዝማች ንጉሤ አቅዋም የጸና አለመሆኑን ከሌሎች ምንጭ በመስማቱ ፣ የመሬት መያዙን ጉዳይ ለሌላ ጊዜ አስተላልፎ ጉዳዩን ተወው ።

ስለዚህ የዚህን ጉዳይና ደጃች ንጉሤን በመደገፍ ፣ ሊገፋበት የፈለገው የእንግሊዝ ዋናው ተፎካካሪ የፈረንሣይ መንግሥት ብቻ ሆነ ። በዚህ ምክንያት የደጃች ንጉሤ መልክተኞች ዐረብኛ የሚያውቁ አባ እምነቱና ልጅ ጸጋዬ የሚባል (አስተርጓሚ) ወደ ሣርዶኛው ንጉሥ በተላኩ በዓመቱ ወደ ፈረንሣይ ንጉሠ ነገሥት ወደ ናፖሊዎን ሦስተኛ በ1852 ዓ. ም. የተጻፈ ደብዳቤና ገጸ በረከት ፣ እንደዚሁም ለሮማ ጳጳስ ለፒዮስ ዘጠነኛ ጭምር እንደ ያዙ በሚሲዮኖቹ አለቃ በአባ ያዕቆብ (ደዣኮቢስ) መሪነት በተለመደው የጉዞ መሥመር በምጥዋና በስዊዝ አድርገው ሮማ ደርሰው እ. ኤ. አ. ጥር 18 ቀን 1859 ዓ. ም. ከሊቀ ጳጳሱ ተገናኝተው ሊቀ ጳጳሱና የፈረንሣይ ንጉሠ ነገሥት ንጉሤን እንዲደግፉ ፤ ያለዚያ ኢትዮጵያ በእንግሊዞች ምክንያት ፕሮቴስታንት ለመሆን የቀረበች መሆኗን ገልጸውና ከወር የበለጠ መልክተኞቹ ከየካርዲናሎቹ ጋር በፍቅር ፣ በደስታ ሲወያዩ

1 Documenti (1859-1882) L' Italia in Africa Tome II - pp. 1-6.



ሰንብተው ፣ በመጋቢት 8 ቀን ሮማን ለቀው ፣ በ28 ቀን በዚሁ ዓመት ወደ ፓሪስ ደርሰው የያዙትን ደብዳቤና ገጸ በረከት ለናፖሊዎን አቀረቡ ። ገጸ በረከቱ አንድ በወርቅ የተጠለፈና ያማረ ኮርቻ ፣ (*) አንድ በረቂቅ ሥራ የተሠራ የወርቅ አምባር ፣ አንድ በወርቅ የተከፈፈ የአንበሳ ለምድና አንድ ጥሩ ጉራዴ መጨበጫያው የወርቅ የሆነ ነው ። ([1])

ለዚሁ የስጦታ መልስ ናፖሊዎን ሦስተኛ መልክተኞቹን በልዩ ልዩ ስጦታ አስደስቶ ፣ ለደጃች ንጉሤም የሚሰጥ ገጸ በረከትም ፣ የጦር መሣሪያም አዘጋጅቶ ከዐሥር መርከበኞች ጋር ለነዚሁ ዋና መሪ ኮንት ስታኒበላው ሩሴል የሚባለውን አድርጎ ወደ ንጉሤ ሲልክ ፣ የደጃች ንጉሤ መልክተኞች እነ አባ እምነቱ እግረ መንገዳቸውን በሮማ በኩል ዐልፈው ወደ ምጥዋ ተጓዙ ። ሩሴልና መርከበኞቹ መጀመሪያ ምጥዋ ፣ ከዚያም ወደ ሐላይ ተጉዘው ከሞንሲኞር ደዣኮቢስ ተገናኝተው ፣ ለደጃች ንጉሤ የያዙት የጦር መሣሪያና ስጦታ በርከት ያለ በመሆኑ ፣ ለዚሁ መጫኛ ከብት በሚፈላለጉበት ጊዜ ዐፄ ቴዎድሮስ ከወሎ ወደ ሸዋ ሰይፉን ለመውጋት ፣ ከሸዋ ወደ ወሎ በሺር ዐመዴን ለመደምሰስ የሚራሯጡበት ጊዜ ስለነበረ ፣ የፈረንሣይንና የንጉሤን ዝምድና የሚቃወሙት እንግሊዞች በተለይ ካፒቴን ፕሎውዴንና በምጥዋ የእንግሊዝ ቆንሲል የሆነው ባርኒ ወደ ዐፄ ቴዎድሮስ ፣ «ሩሴልና ደጃች ንጉሤ የተገናኙ እንደሆነ ይቸገራሉ» የሚል ፈጣን መልክተኛ ልከው አስረዱዋቸው ።

በፊተኛው ጊዜ ፣ ደጃች ንጉሤ ከወንድማቸው ከደጃች ተሰማ ጋር ሆነው ወደ ወገራም ፣ ወደ ተምቤንም እየተመላለሱ ጦር እያደራጁ በሚደገፏቸው ካቶሊኮች አማካይነት ከናፖሊዎንና ከቪክቶር አማኑኤል ሲላላኩ ቴዎድሮስ ወሬውን ከአገር ተወላጅም ፣ ከእንግሊዞቹም ፣ እንደ ሰሙ የንጉሤን ሽፍትነት

* ኮርቻውን ያሠሩ ለዚሁ ለናፖሊዎን ለመላክ ቴዎድሮስ እንደ ነበሩ ፣ በመካከሉ ይኸው ኮርቻ በትግሬ ባንድ ገዳም ተቀምጦ ሳለ በንጉሤ ትእዛዝ በብላታ ደስታ እጅ ከገዳሙ ወጥቶ ለናፖሊዎን መላኩን ፣ ለጀን የሚባለው የፈረንሣይ ቆንሲል ወደ አበሻ ጉዞ በሚለው መጽሐፉ በገጽ 50 ጠቅሶታል ። ስለዚህም ቴዎድሮስ ንጉሤን «ያ የኮርቻ ሌባ» ይሉት ነበር ይባላል ።

1 Rassegna di Studi et. Vol. VII p. 182.

ለመደምሰስ ከቤጌምድር ወደ ተምቤን ድንገት ሲሔዱባቸው እነ ንጉሤ ደንግጠው ፣ ወደ በረሃማው የትውልድ አገራቸው ወደ ወልቃኢት ገቡ ።

በዚህ ጊዜ ፣ ቴዎድሮስ በዐድዋ የጥምቀት በዓልን የመድኃኔ ዓለምን ታቦት በመሸኘት ካከበሩ በኋላ ፣ ወደ ወገራ ዘልቀው የነንጉሤን ወሬ ቢጠይቁ ጠፉባቸው ። ብዙ ሠራዊትም ይዘው በዚያ ለብዙ ጊዜ መቆየት ስለማይችሉ ፣ ወደ ወገራ በረሃ መግባቱም አስቸጋሪ ስለ ሆነባቸው ፣ ከወገራ በአምባ ጫራ በኩል አድርገው ደብረ ታቦር ገቡ ።

በዚያም ደርሰው ትንሽ እንደ ዐረፉ ፣ እላይ እንደ ጠቀስነው በሸዋ አቤቶ ሰይፉ የንጉሥ ኃይለ መለኮት ወንድም ሸፍተው ወኪላቸውን አቶ በዛብህን ከአንኮበር ማባረራቸውን ስለ ሰሙ ጉዟቸውን ወደ ሸዋ አምርተው ፣ አንኮበር ደርሰው ሰይፉ ብቻ ሲያመልጡ በአቶ በዛብህ ጥቆማ 'ይኸ ታማኝ ነው ፣ ይኸ የከዳ ነው' እየተባለ ከሰይፉ የተደረበውን እጅና እግሩን በመቁረጥ ጭምር በመቅጣት በዛብህን በግዛቱ አደላድለው ተመለሱ ። በዚሁ ጊዜ ወደ ሸዋ ሔዱልን ብለው ዕረፍት ያገኙ መስሏቸው የተደሰቱት እነ ደጃች ንጉሤ ወደ ተምቤን ተመልሰው ከካቶሊኮቹ ከእነ አባ ደግኮቢስ ፣ ከእነ አባ እምነቱ ፣ በነርሱም አማካይነት በፈረንሣይ አገር መርከበኛ ያንድ ክፍል ጦር ይዞ መጥቶ በሐላይ ከሚገኘው የመርከብ መኰንን ከኰማንዳ ሩሴል ጋር ይላላኩ ዠመር ።

የቴዎድሮስንም መመለስ መጠራጠራቸው ስለማይቀር ፣ እነርሱም ለውጊያ ይዘጋጁ ነበር ። በደጃች ንጉሤ ውስጥ በዠግንነት ስሙን ያስጠራና ፉከራ የሚያሳምር አንድ ሣህሉ ተሰማ የሚባል የወልቃኢት ተወላጅ ነበር ። እሱም ከቴዎድሮስ ያም ቢቀር ከፊታውራሪ ገብርዬ ጋር ጦርነት አለመቅረቱን እያነሣሣ ፣

«መገን ሣህሉ አባ ጆቢራ
ሃምሳ በፊት ሃምሳ በኋላ ፣ ሃምሳ በቀኝ ሃምሳ በግራ
ክርክር አይቀርም ከዚያ ሰው ጋራ
ከፍ ሲል ከዚያ ሰውዬ (ከቴዎድሮስ)
ዝቅ ሲል ከገብርዬ
ዘራፍ አትበሉ
ይቆጣችኋል ተሰማ ሣህሉ



ተሰማ ሣህሉ ባወጣው ጠጅ
ይንጫጩበታል እንደ ወፍ ልጅ
ደራሽ በቦራ (*) አስጨናቂ በመከራ
የንጉሤን ቤት ሠራው በኖራ...... »

እላይ እንደ ተመለከተው ፣ የንጉሤንና የኰማንዳ ሩሴልን ዓላማ ለመቅጨት በሚመኙት በእንግሊዞቹ ጥቆማ የታማኞቻቸው መልእክት ከደረሳቸው ወዲህ ፣ ቴዎድሮስ ከሸዋ በግሥጋሤ በድንገት ተምቤን ሲደርሱ በሁሉም ዘንድ ድንጋጤና ፍርሃት ወረደ ። እነ ንጉሤ በፊተኛው ጊዜ ወደ ወልቃኢት በረሃ ለመሸሽ ጊዜ ያገኙት አሁን አላገኙም ። ፊት ለፊት ጦርነት ለመግጠምም ፣ ተከታዩ በክዳትም በፍርሃትም ስለ ተበተነ አልቻሉም ። ግማሹ በሌሊት እየሸሸ ወደ አገሩ ሲገባ ፣ ግማሹ ወደ ዐድዋና ወደ አክሱም ቤተ ክርስቲያን እየገባ ሲማጠን ፣ ወታደር በያለበት እየያዘ እየጐተተ ወደ ንጉሥ ሲያመጣው ፣ ሁለቱ መከረኛ ወንድማማቾች የገዛ ሰዋቸው ከድቶ አሲያዛቸውና በሌሊት እንደ ተያዙ ወደ ንጉሡ ቀርበው ሁለት እግርና እጃቸው እየተቆረጠ ተጥለው ላሞራና ላውሬ ቀለብ ሆኑ ። ከነዚህ መካከል አባ ዱራ ብሩ የሚባል የተምቤን ሹም በሽጉጥ ጥይት ራሱን ገደለ ። ያባ ዱራ ብሩን ጠባይና ዝምታ ምንም ባናውቀውም ፣ ፉከራቸውን ያልሰማነው የርሳቸው የዚህን ዐይነት ቁርጠኛ አሟሟት ስናነብ ፣ ዋናው ፎካሪ ተሰማ ሣህሉ በውርደት ተይዞ ከዚህ እንደሚከተለው ተገደለ ።

ንጉሠ ነገሥቱ ከምርኮኞቹ መካከል ተሰማ ሣህሉን ወዲያው እንዳዩት ገብርዬን ጥራ ብለው ከመጡ በኋላ ፣ «ገብርዬ የኔንና ያንተን ተወዳዳሪ እየው» ብለው ተሰማንም በል አሁን ፎክር ቢሉት መቸም ሞት ላይቀርልኝ ብሎ እምቢ ማለቱን ፣ ከዚያ በኋላ እንዲዋረድ አህያ ላይ በግዴታ አስቀምጠው መንደር ለመንደር አዙረው ለተመልካች ካሳዩትና ካሣቁበት በኋላ ፣ እርሱንም ወታደር ቆራርጦ እንደ ጣለው ታሪካዊው መጽሐፍ ገልጦታል ። (1)

---

* ቦራ ማለቱ ቀለም ከግንባሩ ላይ ያለበት ፈጣን ፈረስ ለማለት ነው ።

1 ያጤ ቴዎድሮስ ታሪክ (ፋዚላ) ገጽ 24—27

በዚህ ዐይነት ፣ የፈረንሣይ መንግሥት በደጃች ንጉሤ በኩል በቀይ ባሕር የወደብ መሬት ለማግኘት ያቀደው ዓላማ ፣ ንጉሤም በፈረንሣይ ኃይል የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ለመሆን የነበራቸው ምኞት ለዘለቄታ አከተመ ። ስለዚህ ውስጡን ንጉሤን ለመርዳት ፣ ላዩን ለማጭበርበር ወደ ንጉሠ ነገሥቱ መልእክት ይዞ የመጣው ኮማንዳ ሩሴል መንገዱ በቴዎድሮስ ወገኖች ተቋርጦበት በጭንቅ ምጥዋ ወደሚቀመጠው የፈረንሣይ ቆንሲል ወደ ሙዜ ዤልበርት ተከብቤያለሁ ብሎ አስታውቆ ፣ ቆንሲሉም ላስተዳዳሪዎቹ የግብጽ ባለሥልጣኖች የርዳታ ወታደር ወደ ሐላይ እንዲላክለት ለምኖ ፣ እነሱም የቴዎድሮስን ጦር ፈርተው ሲያመነቱ ፣ በመካከሉ ሩሴል ባገር ተወላጁ መነኩሴ በአባ እምነቱና በሞንሲኜር ደዣኮቢስ እርዳታ በመጣ በ34ኛው ቀን እንደ አው. አቆ. በ1860 (1852) ከሐላይ በእኩለ ሌሊት አምልጦ ምጥዋ ገባ ። ከዚያም ወዳገሩ ተመለሰ ። ([1])

ዐፄ ቴዎድሮስም ከንጉሤ ሞት በኋላ በዚያው ሠፈር በጥቆማ የተገኙትን የደጃች ውቤን ልጅ ፣ የንጉሤን የቅርብ ዘመድ ወይዘሮ ጥሩነሽን ሲያገኙ ፣ «ይቺማ ጥሩ ወርቅ ናት» ብለው አግብተው በደስታ ፣ በዕልልታ ወደ ጐንደር ተመለሱ ። እርሳቸው የመልኳን ውበት ፣ የዛላዋን ማማር ፣ የደሟን ግባት አይተው ጥሩ ወርቅ ብለው ሠይመው ቢያገቧት እርሷ ግን ፣ ሴት የወደደችውን ለማግባት ፣ የጠላችውን እምቢ ለማለት ምንም የመብት ምልክት በሌለበት ፣ በዚያን የፊውዳል ጊዜ የአባቷን የደጃች ውቤን ጠላት ፣ የቅርብ ዘመዶቿን የንጉሤንና የተሰማን ገዳይ ስታገባ ወዳቸው ይሆን? ነገር ግን ፣ ከርሷ በፊት ምንትዋብ ዐሊም የአባታቸውን የራስ ዐሊን ፣ የአያታቸውንም የእቴጌ መነንን ጠላት ቴዎድሮስን አግብተዋል ። የዚህ ሁሉ ዋጋው ዞሮ ዞሮ እቴጌነት ነው ። የጥሩ ወርቅ እቴጌነት ግን ፣ እንደ ታደሉት እንደ ምንትዋብ (የዐፄ በካፋ ሚስት) በተድላ በደስታ መካከል ሳይሆን ፣ በጦርነት በሁካታ መካከል ያለፈ ስለ ነበር ዓለማየሁን ከወለዱ በኋላ በዚሁ የጦርነት ፣ የምርኮ ውዝግብና ድካም ሕይወታቸው ማለፉን ወደፊት እናንባለን ።

1 ያሬድ ወልደ ማርያም ጽሑፍ ገጽ 24 — 25



የሆነ ሆኖ ፣ እቴጌ ጥሩወርቅ ላፄ ቴዎድሮስ እንደ እቴጌ ምንትዋብ ከልብ የሚስት ጓደኛ አልሆኗቸውም ። እንደ ተዋበች የሚጠነቀቁላቸውና የሚያስቡላቸው ሆነው አልተገኙም ። በዚህ ምክንያት ፣ ከተዋበች ሞትና ከጥሩ ወርቅ ጋብቻ ወዲህ ቴዎድሮስ መበሳጨትም ፣ መጠጣትም ፣ ወደሌላ ሴት መሔድም እንደ ዠመሩ የውጭ አገር ተወላጆቹ እነ ዋልድ ማየር ሳይቀሩ ተመልክተውታል ። ([1])

በበኩሉ የፈረንሣዩ ተወላጅና ቆንሲል ለዣን ስለዚህ ጉዳይ በጻፈው መጽሐፍ ላይ ፣ «..........ከስድስት ዓመት በፊት የውቤን ልጅ ቁንጅናዋ ፣ ወጣትነቷ ፣ የልዕልትነት አቅዋሟ በመላው አበሻ ዝናዋ የተነገረላትን አገቡ ። በርሷ ላይ አንድ ጉድለት ቢኖር ከልክ ያለፈ ኩራት ነው ።..........ቴዎድሮስም በተጋቡበት ሦስት ዓመት ውስጥ ይወዷት ነበር ። በተለይ ወንድ ልጅ (ዓለማየሁን) ከወለደች ወዲህ ፍቅራቸው አልተለያትም ነበር.......... ነገር ግን ፣ በአንድ የፋሲካ በዓል በሆነበት ቀን እቴጌይቱ ያባትየው የደጃች ውቤ ወገኖች በእስራት ያሉት ምሕረት እንዲደረግላቸው ብትለምን ቴዎድሮስ ወዲያው በግልፍታ ተቆጥተው ፣ «ከኔ አባትሽን ነው የምትመርጭው?» ብለው አንድ ጥፊ አቀመሷት ። ቤል (ሊቀ መኳስ ዮሐንስ) ሊገላግል ቢሞክርም ፣ እሱም አንድ ጥፊ ተቀበለ ። ከጋብቻው ወዲህ የውቤ እስረኝነት ቀርቶ የነበረው እንደገና ታሰሩ..........ከዚህ በኋላ ሚስታቸውን ለማናደድ ሴት አስቀመጡ.....» ሲል ያመለክታል ።

ቢሆንም ፣ ወደ መጨረሻ ዘመን በጥሩ ወርቅ ትዕቢትና በሌላውም ንጉሡ እየተበሳጩ ከፈረንጆቹም ፣ ከመኳንንቶቻቸውም በተጣሉበት የእንግሊዝ ጦር በመጣበት ሰዓት ፣ ከጥሩወርቅ የበለጠ ይንከባከቧቸውና ይወዷቸው የነበሩት ወይዘሮ የተመኙ ከርሳቸው አልራቁም ።

1 Rassegna di Studi Ethiopici - Vol. VII-Vas. II - L. Fuseila-pp. 181-191.

ለዐፄ ቴዎድሮስ በግልጽ የምናውቃቸው ሚስቶቻቸው የመዠመሪያይቱ የራስ ዐሊ አሉላ ልጅ ፥ የእቴጌ መነን የልጅ ልጅ እቴጌ ተዋበችና እርሳቸው ካረፉ በኋላ ደግሞ ፥ በወግ በማዕረግ አሁን ያገቡዋቸው የስሜኑ የደጃዝማች ውቤ ልጅ እቴጌ ጥሩ ወርቅ ናቸው ።

ነገር ግን ፥ በነዚህ መካከል በተለይ ከተዋበች ሞት በኋላ ወይዘሮ የተመኙ የሚባሉ የየጁ ተወላጅ ፍቅረኛ ወዳጅ እንደ ነበሩዋቸው ፥ ዐልፎ ዐልፎ በቃልም በጽሑፍም ተገልጿል ። እስረኞቹን ለማስፈታት ከንግሥት ቪክቶሪያ ተልኮ የመጣውና በመጨረሻም ራሱ እስረኛ የሆነው ሆርሙዝ ራሳም ወዳገሩ ከተመለሰ በኋላ ፥ በጻፈው መጽሐፉ በቴዎድሮስ ዘንድ የተወደደችው እቴጌ ሲላት የቀሩት ጸሐፊዎች የሚወዷት ዕቁባታቸው እንደ ነበሩ ይገልጻሉ ።(1)

አሁን በመጨረሻ ዳዊት ኤል አፕልያርድ ወደ እንግሊዝኛ ተርጕመው ፕሮፌሰር ሪቻርድ ፓንክረስት በምልክት ያብራሩዋቸው ፥ ዐፄ ቴዎድሮስ ለኻሁ ለእቴጌ የተመኙ የጻፉዋቸው ደብዳቤዎች ንጉሠ ነገሥቱ ሴትዮዋን በጣም ይወዱ እንደ ነበረ ፥ ሴትዮዋም በበኩላቸው ቴዎድሮስን በተለያዩበት ጊዜ ይናፍቁዋቸው እንደ ነበረ ያስረዳሉ ። ከደብዳቤዎቹ አንዱ ከዚህ ቀጥሎ የሠፈረው ነው ።

«በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ ፥ ንጉሠ ነገሥት ቴዎድሮስ ፥ ይድረስ ከእቴጌ የተመኙ ፥ እንዴት ከረምሽ ፤ እኔ እግዚአብሔር ይመስገን ደህና ነኝ ። እናትሽንም ፥ እነ ወይዘሮ ሠናይትንም ፥ የቤቴን ሰዎች ሁሉ እንዴት ከረማችሁ አለ በይልኝ ። አሁንም አይዞሽ ፥ በእግዚአብሔር ኃይል ዐፈር ካልበላሁ ሳላይሽ አልቀርም ፥ አትባቢ ። ተዋበችንም ከነደጃች ጕሹ ፥ ከነብሩ ዐሊ ስዋጋ ቋራ አስቀምጫት ነው ። አሁንም ቋራ መቅደላ ነው ። ነፍስና ሥጋዬ ካልተለያየ የማልቀርበት ሥፍራዬ ነው ። በጳጉሜ 5 ቀን ተጣፈ ።»

---

1 Letters from Ethiopian Rulers........David L. Appleyard A.K. Irvine R. Pankhrust. B. Tafla pp. 250



ደብዳቤው የሚያስረዳን ቀድሞ በንጉሠ ነገሥትነታቸው ዘመን ዋዜማ ላይ ከጕጃሙ ባላባት ከነደጃዝማች ጕሹ ጋር ፥ ከየጁው ባላባት ከነደጃዝማች ብሩ ዐሊ ጋር በሚዋጉበት ዘመን ደንበኛ ባለቤታቸውን እቴጌ ተዋበችን ከትውልድ አገራቸው ከቋራ ማስቀመጣቸውን ፥ አሁንም ለእርሳቸው አልገዛም ብሎ የሸፈተባቸውን ለማሳመን ወዲያና ወዲህ በሚባክኑበት ጊዜ ምንም እንኳን በመካከላቸው ልባዊ ፍቅር ባይኖርም በደንበኛ ባለቤታቸው በእቴጌ ጥሩ ወርቅ ላይ ፥ እኝህን ወይዘሮ የተመኙን ከልባቸው እንደሚወዷቸውና በመቅደላ ተራራ ለየት ካለ ቦታ አስቀምጠዋቸው ስለ ነበረና የተገናኙበትም ጊዜ ረዘም ስላለ ሴትዮዋን ለማጽናናት የተጻፈ ነው ።

በሕይወታቸው ያገቡዋቸውና የታወቁት ተዋበችና ጥሩ ወርቅ ሆነው ሳሉ እኝህን የየጁ ወይዘሮ ምንም እንኳ ቆንጆና የተወደዱ ቢሆኑ ፥ ዞሮ ዞሮ እንደ ዕቁባት ናቸውና በእቴጌነት ሊጠሩዋቸው የሚገባ አይመስልም ። እንደ ሚስትም በበኩላቸው ቆጥረዋቸው እንደሆነ ባንድ የጊዜ ወቅት ሁለት በእቴጌነት የሚጠሩ ሚስቶች ነበሩዋቸው ማለት ስለሆነ ፥ ነገሩ ከሥርዓት ውጭ መሆኑን ያሳያል ።

ሌሎቹ ለእቴጌ የተመኙ የጻፉዋቸው ደብዳቤዎች በይዘትም ፥ በቅርፅም ተመሳሳይ ናቸው ። ባንደኛዋ ደብዳቤ ግርጌ ከሰላምታ ቀጥሎ ፥ «አይዞሽ እቴ የናቴ ልጅ ፥ ነፍስና ሥጋዬ ካልተለያየ ሳላይሽ አልቀርም» የሚል የናፍቆት ዐረፍተ ነገር አለበት ። ደብዳቤዎቹ ዓመተ ምሕረት የሉባቸውም ። ነገር ግን ደብዳቤዎቹን የጻፉዋቸው በመጨረሻ ዘመን ጓዛቸውን ወደ መቅደላ ካወጡና የሚጠረጥሩትን ሁሉ በግዞት መቅደላ ተራራ ላይ ባስቀመጡበት ወቅት ምናልባት እንደ ኢ.ት. አቆ. በ1856—60 ዓ. ም. መካከል ሳይሆን አይቀርም ። (1)

ሁኔታው ሲገመገም ከሚወዷቸው ከእቴጌ ተዋበች ወዲህ ባገቧቸውና የንቀት መልክ በሚያሳዩዋቸው በእቴጌ ጥሩ ወርቅ

---

1 Record of the Expedition - T. J. Holland p. 11.

ውቤ መካከል እንደ ተዋበች መሰል ሁነው በፍቅርና በማንከባከብ የያዙዋቸው እኚሁ የየጁ ቆንጆ ወይዘሮ የተመኙ መሆናቸው ይታያል ። በደብዳቤያቸው ውስጥ ቴዎድሮስ «እቴ የናቴ ልጅ» የሚል ዐረፍተ ነገር እስከ ማስፈር የደረሱት ፣ ከዚሁ ልባዊ ፍቅር የተነሣ መሆኑ የታወቀ ነው ።


የዚህኑ ሁኔታ ሆርሙዝ ራሳም በበኩሉ ሲያትት በመጨረሻ ጊዜ የቴዎድሮስን ልብ በፍቅር ይዘው የነበሩት የተመኙ እንደ ነበሩ ፣ በፋሲካ በዓል መልካም ድግስ አዘጋጅተው በማስተናገድ ማስደሰታቸውን ይገልጻል ። [1]

1 Record of the Expedition - T.J. Holland. p. 11



ሌዎን ዴዛቫንሸር
(ከአባ ማስያስ መጽሐፍ)

# ዐፄ ቴዎድሮስ ጋረድንና ደጃዝማች ንጉሤን ለመደምሰስ የተጓዙባቸው መሥመሮች ።



# ምዕራፍ ሐያ ሁለት

## ያፄ ቴዎድሮስ የመጨረሻው ዘመን ችግር

ዐፄ ቴዎድሮስ በ19ነኛው መቶ ዓመት አጋማሽ ላይ ሳይታሰቡ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ብቅ ያሉ ፣ ልዩ ጠባይ ከጠንካራ አካል ጋር ያላቸው ፣ ከሰባ ዓመት በላይ የቆየውንና ለኢትዮጵያ መከፋፈልና ብዙ የርስ በርስ ጦርነት ምክንያት የሆነውን ዘመነ መሳፍንትን በማስወገድ ፣ ጠንካራ ማዕከላዊ መንግሥት ለማቆም በመጣጣር በጠቅላላው ለኢትዮጵያ አዲስ የታሪክ ምዕራፍ የከፈቱ ዠግና ናቸው ።

እንደ ኢትዮጵያ ላለ በሥልጣኔ ወደኋላ ለቀረ ፣ ከሃይማኖትና ከልዩ ልዩ ኅብረተሰብ የተወረሰ ባህል ለተጫነው ፣ በራሱ ዲሞክራሲያዊ ምርጫ ለመተዳደር የዕድገቱ ደረጃ ገና ላልፈቀደለት ሕዝብ ጥፋተኛን ከንጹሕ ለይቶ እየቀጣ ፣ ወደ ቀናው የልማት መንገድ የሚመራ ጠንካራ ክንድ ያለው መሪ እንደሚያስፈልገው ግልጽ ነው ።

ነገር ግን ፣ ዐፄ ቴዎድሮስ ዘመነ መሳፍንትን በማስወገድ የባሪያ አገዛዝን ሲሽሩ ፣ የካህናትን ቁጥር ሲወስኑ ፣ «መሬት የመንግሥት ነው» ብለው በዚያ ባለጉልተኛ በሰፈነበት ዘመን ማወጃቸው የሚያስመሰግን ሲሆን ፣ ከእየአካባቢው የተነሣባቸው ተቃውሞ በጎ ሐሳባቸውን ከፍጻሜ ለማድረስ አላስቻላቸውም ። ስለዚህ ሐሳባቸውን አልቀበልም ባለው ወገን ላይ ቁርጠኛ እርምጃ ለመውሰድ አስገድዷቸዋል ።

ቴዎድሮስ ከነገሡ በኋላ ፣ ባጠገባቸው ያሉት እነዦን ቤል በተለይ የእንግሊዝ ቆንሲል የነበረው ሚቹ ወዳጃቸው ፕሎውዴን በመከራቸው መሠረት ለእንግሊዝ ንግሥት ለቪክቶሪያ በ1855 ዓ. ም. በጻፉት ደብዳቤ ፣ አባቶቻቸው ነገሥታቱ ፈጣሪያቸውን ቢበድሉት መንግሥታቸውን ለተቀናቃኞቻቸውና ለቱርክ

ሰጥቶባቸው እንደ ነበረ ከማስታወቃቸውም ሌላ ፣ ስለ ራሳቸው ባሠፈሩት ቃል ፣ «ዛሬ ግን እኔ ከተወለድሁ ፈጣሪዬ ካመድ (ከድህነት) አንሥቶ ፣ ኃይል ሰጥቶ ባባቶቼ መንግሥት አቆመኝ» ሲሉ መጻፋቸውም ይኸንኑ አሳባቸውን ለመግለጽ ነው ። (*) ከሥልጣን አኳያ ተቀናቃኝ የነበሩትን የኦሮሞ ባላባቶች በተለይ ቢመለከቷቸውም ፣ ሰፋ ያለ ያንድነትና የእኩልነት አርአያ የያዘ መንፈስ ነበራቸው ። የገዛ ሚስታቸው እቴጌ ምንትዋብ የራስ ዐሊ ልጅ ባባታቸው ኦሮሞነት እንዳላቸው አይካድም ። የተነሡበት ዋና ዓላማ የኢትዮጵያን አንድነት ለመመሥረት መሆኑን ለመግለጽ ሲፈልጉ ፣ የልዩነት አመለካከትን ወደጐን አድርገው በራሳቸው አነጋገር በፉከራ መልክ እንደዚህ ብለዋል ። «.........ጋላና አማራን ባንድ ሰዲቃ (መሶብ) ያላበላሁ እንደሆነ እኔ የክርስቶስ ባርያ ፣ የቅዱስ ዮሐንስ ዕለት ክርስቲያን አትበሉኝ.........» ያሉትን እናስታውሳለን ። እውነትም በልዩ ልዩ ቅራኔዎች የተነሣ መልሶ ቢበተንም የትግሬን ፣ የአማራን ፣ የወሎንና የሸዋን ሰው አስገብረው ፣ ከየመካከላቸው አስተዳዳሪ ሾመው ያንድነት መሠረት መጣላቸውን ለዘመን መለወጫ (የቅዱስ ዮሐንስ ለት) እና በሌላውም ክብረ በዓል በአዳራሻቸው ግብር አግብተው የነዚህን አገር ሁሉ ተወላጅ የአማራውን ፣ የትግሬውንም ፣ የኦሮሞውንም ወታደሮቻቸውን ግብር ማብላታቸው አይጠረጠርም ። በዚያን ዘመን ባህል ያንድነት ምልክት የሚገለጠው ባንድነት ዘምቶ ባንድነት ግብር ሲበላ ነው ።

ነገር ግን ፣ በጦር ሜዳ ራሳቸው መዋጋትና ሌላውን ማዋጋት ስጦታቸው የሆነው ቴዎድሮስ እንደ ናፖሊዎን ፣ እንደ ታላቁ እስክንድር በድፍረትና በጦር አመራር ዕውቀት በትንሽ ጦር ብዙውን ድል ማድረግ ችለዋል ። ይሁን እንጂ ፣ ተቃዋሚ ኃይሎችን ጨርሶ ለማስወገድ አልሆነላቸውም ። ማፈንገጥ በበዛ ቁጥርም ፣ የሚወስዱት የቅጣት እርምጃም የዚያኑ ያህል የከፋ ሊሆን ችሏል ። ይህም በአንጻሩ የተቃዋሚውን ወገን እየተበራከተና እየተጠናከረ ለመሔድ አስችሎታል ።

* ተቀናቃኞች የተባሉት የውቢት ወገኖችና በተለይ የየጁና የወሎ የኦሮሞ ባላባቶች እነ ራስ ዐሊ ናቸው ። ቱርኮች የሚለው በምዕራብ በመተማና በሰናር ፣ በምሥራቅ በምጥዋ አካባቢ በቱርክ ጠቅላይነት የገቡትን ግብጾች የሚመለከት ነው ።



ዐፄ ቴዎድሮስ በጠላቶቻቸው ላይ ከባድ የቅጣት እርምጃ የመውሰዳቸው ሁኔታ ፣ ከመንገሣቸው በፊትም ይታይ እንደ ነበር ይታወሳል ። ከነገሡም በኋላ እስኪሞቱ ድረስ አድራጐታቸውም ፣ አነጋገራቸውም በጊዜው ካጋጠሟቸው አስቸጋሪ ሁኔታዎች አንጻር ጠንከር ያለ ባሕርይ የሚታይበት ሊሆን ችሏል ። ከዚሁ አኳያ እጅና እግር እስከ መቁረጥ የሚያደርስ ቅጣት እንደፈጸሙ ይታወቃል ።

ከዚሁም በመነሣት ጐንደሬ በነገሩ እየተገረመ ፣ «ምን ያድርግ ፣ በኃጢአታችን ብዛት እግዚአብሔር ሰይፍ ሰጥቶ ቅጣ ብሎ የላከው ነው» እስከ ማለት ደርሷል ። ገጣሚዋ ምንትዋብም ፣

«አንድ እግር በርበሬ መንቀል አቅቷችሁ
እንደዚህ አንድዶ ፣ ለብልቦ ይፍጃችሁ»

ብላለች ። በውነትም ራስ ዐሊ በሥልጣን በቆዩበት የኻያ ሁለት ዓመት ጊዜ (1825—1847) በጐንደርና በደብረ ታቦር ቤተ መንግሥት ተድላ ደስታ ፣ መጠጥና ምንዝር በዝቶ ነበርና በዚህ እምላክ ተቆጥቶ ሕዝቡን ለመቅጣት ቴዎድሮስን አስነሣ የሚል እምነት በመኳንንቱ በካህናቱ በሕዝቡም ላይ እንዲያድር አድርገው ነበር ። ራስ ዐሊ መቶ ሺ ጦር ይዘው ሳለ ፣ ትንሽ ጦር ይዘው ካሣ (ቴዎድሮስ) ቢያሸንፏቸው ፣ «ይህ በትር የአምላክ ነው እንጂ የካሣ አይደለም» ያሉትም በኃጢአታቸው የተነሣ አምላክ ቴዎድሮስን ሊቀጣቸው እንደ ላካቸው አምነዋል ማለት ነው ። ቴዎድሮስም ራሳቸው የባላገሩንም ፣ የወታደሩንም መመረር ተመልክተው ከዕለታት አንድ ቀን በኩታቸው ተጠቅልለው ከሜዳ ላይ ተኝተው ፣ «እንግዲህ ግደሉኝና ዕረፉ» ብለው በመጠበቅ ከቆዩ በኋላ ፣ የሚገድላቸው ቢጠፋ ተገላልጠው ብድግ ብለው ፣ «ታድያ ምን ላድርግ!» አሉ ይባላል ።(1)እንደዚሁም ከዕለታት አንድ ቀን በቤተክርስቲያን ውስጥ እንዳሉ መጽሐፍ አንባቢው ደብተራ በመጽሐፈ ኢዮብ ምዕራፍ 34 ቁጥር30 ላይ ያለውን «ወአነግሥ ሎሙ ብእሴ መደልወ—ክፉ ንጉሥ አነግሥላቸዋለሁ» ብሏል እግዚአብሔር ከሚለው ዐረፍተ ነገር ላይ ሲደርስ ፣ እርሳቸውን «ክፉ ንጉሥ የተባልከው አንተ ነህ» ለማሰኘት ይኸንኑ ቃል ሲደጋግም ሰምተው ፣ «በአንተ እከየ ሕዝቡ—ከሕዝቡ

1 ምንዶን ያላተመው ታሪካቸው ገጽ 36—40
Rassegna di Studi Ethiopici Vol. XII.........

ከፉት የተነሣ' የሚለውን ቃል አከለው» አሉ ይባላል ። በዚህም የራሳቸውን አድራጐት ሳይከዱ ባሕርያቸውን ከሕዝቡ ከፋት ጋር እንዳያያዙት ይታያል ። ከተማረ ደብተራ ጋርም እኩል ወይም የበለጠ ግዕዛዊ የቀለም ችሎታ እንዳላቸው ይታወቃል ።

የሆነ ሆኖ ፣ ከሊቀ መኳስ ዮሐንስና ከእቴጌ ምንትዋብ ሞት ወዲህ በመጨረሻ የግዛታቸው ዘመን አካባቢ (1856—1860) የከዳተኛው ቁጥር በየአውራጃው በበረከተ መጠን ፣ የርሳቸውም ብስጭትና ጭካኔ በዚያው ልክ እየበዛ ሔደ ። በሩቅ ያሉትን የአውራጃ መሳፍንት መሸፈት ሲሰሙ የቀረውም የየአቅራቢያው ለመሸፈት ማቆብቆቡን ሲያውቁ ፣ በዚያው በአቅራቢያ በጐንደርና በዙሪያው ፣ በደብረ ታቦር ፣ በዘጌ ፣ በትውልድ አገራቸው በደምቢያ ፣ በሚጫ ፣ በአገው ምድር ፣ በወገራ ከፍተኛ ቅጣት እንዲፈጸምና ከብቶችም እንዲነዱ አድርገዋል ። ከጐንደርም አብያተ ክርስቲያናት መካከልም የተወሰኑት ተቃጥለዋል ።[1]

በዚሁ ጊዜ ፣ ብዙ ስለት ስለሚገባለት ስለ አዲት መድኃኔ ዓለም መቃጠል ሲነገር እንኳን ፣ ሌላውን ሲያድን ቀርቶ ራሱንም ሊያድን አልቻለም በማለት እንደዚህ ተገጥሟል ።

«እንግዲህ ለታቦት አልሰጥም ስለት
አዲት መድኃኔ ዓለም ነዶ አገኘሁት»[2]

በዚህ ዐይነት ፣ በአገር ላይ ረኃብና ችግር ተፈጥሮ ያንድ እንጀራ ዋጋ አንድ ብር እስከ ማውጣት ደረሰ ፤ ሻል ባለው አውራጃ በብር አራት እንጀራ ተገዛ[3] በዚያን ጊዜ ነው አልቃሾች በዚህ በመጨረሻው ዘመን የጐንደርንና የጐጃምን መፈታት አይተው ፣

«ሞጣ ቀራንዮ ምነው አይታረስ
በሬ ሳላይ (በሬሳ ላይ) መጣሁ ከዚያ እስከዚህ ድረስ ።
በሰንሰለት ታስሮ ዓመት ካራት ወር
ማንን ዋስ አግኝቶ ተፈታ ጐንደር»

---

1 የተረፉት ሬት አቦ ፣ ልደታ ፣ በዓታ ፣ ቁስቋም ፣ አዘዞ ተክለ ሃይማኖት ፣ ምጥማቅ ዮሐንስ ፣ ቀሃ ኢየሱስ ናቸው ። የዋድላው የደብተራ አሥጋኸኝ ደብዳቤ Rassegna di Studi Ethipici Vol. XII ...pp-80-95

2 ያጼ ቴዎድሮስ ታሪክ ሞንዶን ያሳተመው ገጽ 48

3 The History of Debre Tabore - R. Pankhurest p. 252



ብለው ሲገጥሙ ፣ ሌላዋ ደግሞ የረኃቡን ወገን ስታነሣ ፣

«ልብሴንም ገፈፈው ለበሰው እርዘኛ(የተራቆተ)
በሬዬንም ነዳው አረደው ነፍጠኛ (ወታደር)
እህሌንም ዘረፈው በላው ቀለብተኛ(የተራበ ቀለብተኛ)
ንጉሥ የቀረዎት ጥቂት አግርኛ
ምነው ሆድ አይዘርፉ ዐርፌ እንድተኛ(ከምራብ ቢገድሉኝ)»

ብላ የገጠመችው የዘመኑን የከፋ ሁኔታ ይገልጣል ።

ከዕለታት አንድ ቀን ፣ አንድ ወታደር ከባልደረቦቹ ተለይቶ አንድ ፈረስና ሁለት የተጫኑ አህዮች ይዞ እየነዳ በሚሔድበት ጊዜ ፈረሱ ለብቻው ደክሞት እየወደቀ ፣ ከአህዮቹም አንደኛው ጭነቱን እየጣለበት ወታደሩ የሚያደርገው ጠፍቶት ወደ አምላኩ በሐዘን ሲያማርር ቴዎድሮስ ከኋላው ደርሰው ፣ «ለምን ፈጣሪህን ታማርረዋለህ? 'ይህን ንጉሥ ግደልልኝ እንዳርፍ' ብለህ ለምነው እንጂ» ቢሉት ወታደሩ መልሶ ፣ «ጃንሆይ አልሰማኝ አለ እንጂ እኔስ ሁልጊዜ ለመንሁት» አላቸው ። እርሳቸውም «እውነትህን ነው» ብለው ዝም ብለውት ሔዱ ። እዚህ ላይ ደግሞ የርኅራኄያቸውና የመሐሪነታቸው ሁኔታ ይታያል ። ሆኖም በተለያዩ አጋጣሚዎች በሁኔታዎች ተገፋፍተው ብርቱ ቅጣት ከመፈጸም አልተቆጠቡም ። ለምሳሌ ፣ ምኒልክ በ1857 ዓ. ም. ከመቅደላ የግዞት ቤት አምልጠው በወሎ በኩል አድርገው ወደ ሸዋ የገቡ ጊዜ ፣ ለሽሽት የረዱዋቸው ወሎዎች ናቸው የሚለው ወሬ በደረሳቸው ወቅት በመቅደላ በእስር ላይ የሚገኙትን የወሎን 24 መኳንንት እነ ዐሊ ወዳጆን ፣ እነ ፋሪስ ቃሲምን ሌላውንም በመቅደላ አፋፍ ላይ እግርና እጃቸውን እያስቆረጡና እያስገፉ በማስጣል ቀጧቸው ። ሁኔታው ደግሞ መልሶ እየጸጸታቸው «ይኸን ሁሉ ሳደርግ ለምን አልገዘቱኝም» ብለው ራሳቸው ግዞተኛ ከሆኑት ከአቡነ ሰላማ ጋር ተጣልተዋል ። ጳጳሱ ደግሞ ከመገዘት የታገዱት በእስር ቤት ያሉት መኳንንት አሁን ቢገዝቱ ፣ እኛንም ጨምረው ያስፈጁናል ብለው ግዝታቸውን እንዲተዉ ስለ ለመኗቸው መሆኑን አለቃ ወልደማርያም ጽፈውታል ።[1]

---

1 አለቃ ወልደማርያም ገጽ 31—32

ዐፄ ቴዎድሮስ ምንም እንኳን ከሥር ከመሠረቱ አነሣሣቸው በመሳፍንት የተከፋፈለችውን ኢትዮጵያን አንድ አደርጋለሁ በሚል ቅዱስ ዓላማ ቢሆንም ፣ ይኸን የመሰለውን ዓላማ አስቸጋሪ በነበረው ሁኔታ ውስጥ በማለፍ እንደ ምኞታቸው ከዳር ለማድረስ ቀላል አልሆነላቸውም ። በመጀመሪያው የአገዛዝ ዘመናቸው ከተከተሏቸው የጦር መኳንንት ውስጥ በዚህ ጊዜ አንዳንዶቹ ከነጦራቸው እየሸሹ ወዳገራቸው ይገቡ ጀመር ።

በ1859 ዓ. ም. የአማራ ሳይንትና የዋድላ መኳንንት ሊከዱ ነው የሚሉ ወሬ በተሰማባቸውና እነዚህን በወታደር ከበው ያስጠብቁ የነበሩት የብዙ ዘመን አገልጋያቸው ራስ አዲሱ ፣ ይህ ዐይነቱ ዕድል በኔም ላይ አንድ ቀን ሊደርስ ይችላል በሚል ጥርጣሬ ጦራቸውን እንደ ያዙ ወደየጁ ገቡ ። በደህናው ቀን የሚያጫውቷቸው ሁሉ ከፍርሃት የተነሣ ፣ ከፊታቸው መጥፋት ወይም ዝም ማለትን መረጡ ። ብላታ በውቀቱ የሚባሉ ጨዋታ ዐዋቂ ፣ «አጫውተኝ» ብለው ቢጠይቋቸው ከፍርሃት የተነሣ ፣ «በፊት በዋዛው ጊዜ ዐውቅ ነበር ፤ ዛሬስ እረስቸዋለሁ» ብለው አመለጡ ።

ቀድሞ በዙሪያቸው እየተሰበሰበ ለሹመት ለሽልማት ደጅ የሚጠናው ፣ «ምነው ንጉሡ ባዩኝ ፣ ባነጋገሩኝ» የሚለው በዚህ ጊዜ ከፊታቸው መሸሽ ጀመረ ። አንዱ ገጣሚ ፣

«ቴዎድሮስ ቢመጣ ዐይኑን አፍጦ
ወይ መሸሸጊያ ትንሽ ቁጥቋጦ»

አለ ይባላል ። ወደፊት እንደምናነበው ፣ በዚህ ዐይነት በያለበት የሚከዳው ቁጥር እየበረከተ ሔዶ የወታደራቸው ቁጥር ከመቶ ሺ ፣ ወደ አምስት ሺ በወረደበት ጊዜ የእንግሊዝ ጦር መጥቶ በቀላሉ ሊያጠቃቸው ቻለ ።



## ምዕራፍ ሐያ ሦስት

### የመሳፍንቱና የመኳንንቱ የተለያየ አቀዋም

የብሔራዊ አንድነት ዘመቻ ለማድረግ በተነሣሡት ባፄ ቴዎድሮስ ዘመነ መንግሥት የነበሩት የመሳፍንትና የመኳንንት አቅዋም በልዩ ልዩ ሁኔታ የተለያየ ነው ። የሁሉንም አጠቃለን ከሦስት መደብ ላይ ከዚህ እንደሚከተለው ከፍለን ለመመልከት እንችላለን ።

አንደኛው መደብ ፣ ዐፄ ቴዎድሮስ በ1845 ዓ. ም. ዋናውን እንደራሴ ራስ ዐሊን ያሸነፉለት ፣ ከዚያም አከታትለው ደጃዝማች ውቤን አሸንፈው ዘውድ የደፉለት ዘመነ መሳፍንት ቢወድቅም ፣ የነዚያው የመሳፍንት ተወላጆች የዘመነ መሳፍንት የብቸኝነት ሥልጣናቸው እንዲቀጥል በየቤታችን ቋረኛው ካሣን አንቀበልም ብለው ብዙ ዘመን የታገሉት ፤

ሁለተኛው መደብ ፣ በጦር ኃይል መሳፍንቱ ወይም ልጆቻቸው ከተማረኩ በኋላ ፣ እንደ ወገኖቻቸው ይሸፍታሉ እየተባሉ በጥርጣሬ በመቅደላ በእስራት ፣ ወይም በግማሽ ግዞት ተቀምጠው ሲኖሩ የመቅደላው ጦርነት ነጻ ያወጣቸው ፤

ሦስተኛው መደብ ፣ የራሳቸው ያፄ ቴዎድሮስ አብሮ አደጎችና ወይም እርሳቸው በሹመትና በማዕረግ ያሳደጉዋቸው ታማኝ መኳንንቶች ናቸው ።

ስለዚህ ፣ በመጀመሪያ የሁለቱን መደብ የመሳፍንቱን ልጆች ትግልና በጥርጣሬ የታሰሩትን ቀደም አድርገን ከተመለከትን በኋላ ፣ በሚቀጥለው ያለውን የራሳቸውን የመኳንንት ዝርዝር እንመለከታለን ።

# አንደኛ መደብ

## አንደኛ ፣ አቤቶ ሰይፉ (ሰይፈ ሥላሴ)

አቤቶ ሰይፉ ፣ የንጉሥ ሣህለ ሥላሴና የወይዘሮ በዛብሽ ልጅ ፣ የንጉሥ ኃይለ መለኮትና የአቤቶ ዳርጌ ወንድም ናቸው ። በመጀመሪያው ጊዜ ዐፄ ቴዎድሮስ ሸዋን ለማስገበር የመጡ ጊዜ ምኒልክን ማርከው ይዘው ለሸዋ ፣ ወንድማቸውን መርድ አዝማች ኃይሌን ሾመው ሲመለሱ ፣ ግዛቱ ከቤታችን አልወጣም በማለት ነገሩን በቸልታ ተመልክተው ነበር ። በኋላ ግን ፣ መርድ አዝማች ኃይሌ ከቃሉ ባላባት ከዐመዴ በሽር ጋር ተመሳጥረዋል ተብለው ፣ በሥራህ ብዙ ተከሰው በታሠሩና በምክር በርሳቸው እግር ከሣህለ ሥላሴ የማይወለዱት አቶ በዛብህ ለገዥነት ፣ አፈ ንጉሥ አቦዬ ለታዛቢነት የተሾሙ ጊዜ ፣ ከኛ ከመሳፍንቱ መካከል የሚሾም ጠፍቶ ነው የባላገር ቀንደኛ የሚሾም ብለው ተናደው በመነሣት አቶ በዛብህን ካንኮበር በውጊያ አባረሩ ። በዛብህም ወደ ዐፄ ቴዎድሮስ ልከው ሁለተኛ ጊዜ ቴዎድሮስ ወደ ሸዋ ሰይፉን ለመውጋት ዘመቱ ። የጦርነቱንም መበርታት አይተው «እነዚህ በፊተኛው ጊዜ ኖረው ቢሆን ወደ ሸዋ አልገባም ነበር» አሉ ይባላል ። ቢሆንም በመጨረሻ ሰይፉ ተሸንፈው ሸሹ ።

## ሁለተኛ ፣ ደጃች ተድላ ጓሉ ፣

ደጃች ተድላ ጓሉ ፣ ከላይ ከደጃች ዮሴዴቅና ከወይዘሮ ወለተ እሥራኤል ይወለዳሉ ። ወለተ እሥራኤል ፣ እቴጌ ምንትዋብ ከምልምል ኢያሱ የወለዷቸው ናቸው ። ምልምል ኢያሱ ያፄ ኢያሱ አድያም ሰገድ ልጅ ፣ ያፄ በካፋ የእህት ልጅ ናቸው ። ዮሴዴቅ ከላይ ከጉድሩ የኦሮሞ ባላባቶች ይወለዳሉ ። ደጃች ዮሴዴቅ ከወይዘሮ ወለተ እሥራኤል ታላቅ ራስ ኃይሉን ፣ ታላቅ ራስ ኃይሉ ራስ መርድንና ወይዘሮ ድንቅነሽን ፣ ድንቅነሽ ከዳሞቱ ባላባት ከደጃች ዘውዴ ደጃች ጎሹን ፣ ጎሹ ደጃች ብሩንና ደጃች ተሰማን ፣ ተሰማ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን ይወልዳሉ ። ራስ መርድ ደጃች ጓሉን ፣ ጓሉ ደጃች ተድላን ይወልዳሉ ። ስለ ዚህ ደጃች ተድላ ጓሉ ከላይ ከነገሥታት የሚወለዱ የጐጃም መስፍን ናቸው ።

ዐፄ ቴዎድሮስ ፣ የጐጃምን ገዥ ደጃች ጐሹን በ1845 ገድለው ልጃቸውን ብሩን ከማረኩና ከነገሡ ወዲህ ፣ ተድላም በመጀመሪያው ወቅት ከገቡ በኋላ ቴዎድሮስ በጐጃም ሾመዋቸው ነበር ። በኋላ ግን ፣ ንጉሡ ወደ ሸዋ ሲዘምቱ ተድላ ከወሎ ላይ አምልጠው ወደ ጐጃም ገቡ ። ከዚያ ወዲህ ዐፄ ቴዎድሮስ ብዙ ጊዜ ወደ ጐጃም ዘምተው ተድላ ጓሉን ለመደምሰስ ቢሞክሩ አልሆንላቸውም ። ንጉሡ ሲመጡባቸው ተድላ ወደ ሙተራ ጀበላ ተራራ እየወጡ ሲሔዱባቸው ፣ ከተራራ እየወረዱ ጐጃም እየገቡ ሲመለሱባቸው ፣ ወደ ተራራው እየወጡ ብዙ ዘመን አስቸግረው ፣ በዚህ ዐይነት ሲኖሩ በ1860 ዓ. ም. በጥር ወር ሞቱ ። እርሳቸውም በሞቱ ባራተኛው ወር በሚያዝያ ቴዎድሮስ ሞቱ ። ደጃች ተድላ ጓሉ ደግና ሰው አክባሪ ስለ ነበሩ ፣ በሞታቸው ጊዜ መላው የጐጃም ሰው አዝኖ የገጠመላቸውን ባለፈው ምዕራፍ አንብበናል ።

## ሦስተኛ ፣ ዋግ ሹም ገብረ መድኅን አምኃ

ዋግሹም ገብረ መድኅን ፣ ከዋግ ባላባቶች ከላይ ከነዋግ ሹም ርቱዓ አምላክ ይወለዳሉ ። በራስ ይማም ዘመነ ምስፍና የነበሩ የዋግ ሹም ክንፉ የልጅ ልጅ ናቸው ። ዋግ ሹም ክንፉ ዋግ ሹም ወሰንንና አቶ አምኃን ይወልዳሉ ። አቶ አምኃ ከወይዘሮ በተሃ ዋግ ሹም ገብረ መድኅንን ይወልዳሉ ። ዋግ ሹም ገብረ መድኅንም የዋግ ሹም ጉበዜ አባት ናቸው ።

በመጀመሪያ ላይ ለቴዎድሮስ ገብረው ጉብተውላቸው ነበር ፤ ዋግሹም የተባሉት በቴዎድሮስ ይሁን በነራስ አሉላ ጊዜ ይሁን አናረጋግጥም ። የሆነ ሆኖ ፣ ዐፄ ቴዎድሮስ ከሸዋ ሲመለሱ ገብረ መድኅንን በዋግ ላይ ሾመው ከሰደዱዋቸው ወዲህ

ስለሸፈቱ ፣ ቴዎድሮስ በዋግ በዘመቱ ጊዜ ተይዘው ቀርበው በግንቦት ወር በ1848 ገረገራ (ዘቢጥ) በሚባል አገር በግራር ዛፍ ላይ ሰቀሏቸው ።(1)

አራተኛ ፣ ደጃች ብሩ ጐሹ

ብሩ ጐሹ የደጃች ጐሹ ልጅ ፣ የደጃች ተሰማ ወንድም ፣ የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት አጐት ናቸው ። በፊት ራስ ዐሊን ፣ በኋላ የተቻላቸውን ያህል ቴዎድሮስን ተቃውመው በመጨረሻ ዐፄ ቴዎድሮስ አስረዋቸው ሳለ እንግሊዞች ፈቷቸው ። በኋላም ለዋግ ሹም ጐበዜ (ዐፄ ተክለ ጊዮርጊስ) ገብተው ሳለ በንግግር ስለ ዘበቱባቸው ፣ ዋግሹም ጐበዜ በ1860 ዓ. ም. በሰኔ ወር ላይ ሰቀሏቸው ።(2)

አምስተኛ ፣ ዐመዴ በሽር

ዐመዴ በሽር የይማም ሊበን የልጅ ልጅ ፣ የራስ ዐሊ እናት እቴጌ መነን ያባቱ የበሺር እኅት ናቸው ። ከወሎ ባላባቶች ሁሉ ካፄ ቴዎድሮስ ጋር በጣም የተከራከረ ዐመዴ በሽር ነው ። የወይዘሮ መስተዋትና የልጃቸው የይማም ዐመዴ እንደራሴና ራሱ የቃሉ (ወሎ) ባላባት ነው ። ዐፄ ቴዎድሮስ እርሱን ለመውጋት ሰባት ጊዜ ወደ ወሎ ዘምተዋል ። እርሱም እንደ ደጃች ተድላ ጓሉ ቴዎድሮስ በመጡበት ቁጥር ወደ ቆላ ፣ ወደ በረሃ እየገባ እልፍ ሲሉ ወዳገሩ እየተመለሰ አስቸግሯቸው ሲኖር በመጨረሻ ከወይዘሮ መስተዋት ጋር ሆኖ እንግሊዞችን በመቀበል ቴዎድሮስን መቃወም ቀጠለ ። ከርሱም በቀር በአማራ አገር ደጃች ትኩ ፣ በለገጐራ (ወሎ) ዐሊ ደራና እነዚህን የመሳሰሉ ብዙ አሉ ።

ስድስተኛ ፣ በዛብህ (በዙ አባ ድክር) ፣ የክርስትና ስም ወልደ ኪሮስ

ቴዎድሮስ ሸዋ የመጡ ጊዜ ተዋግተው ቆስለው መያዛቸውን እንባቢ ያስታውሰዋል ። ቆስለውም በተያዙና ዐፄ ቴዎድሮስ

1 የቴዎድሮስ ታሪክ — አለቃ ዘነብ ገጽ 33 — 34
2 መጽሐፈ ትዝታ ዘአለቃ ለማ ፣ መንግሥቱ ለማ ገጽ ም. 46 ገጽ 43



ፊት በቀረቡ ጊዜ ፣ «በዘውዴ እንጂ በዦግንነት አልበልጥህም» ሲሉ ንጉሡ አድናቆታቸውን ገልጠውላቸዋል ይባላል ። በኋላ መርድ አዝማች ኃይሌ በጥርጣሬ የታሰሩ ጊዜ ዐፄ ቴዎድሮስ ለሸዋ ጠባቂ አፈንጉሥ አቦዬን ፣ አበጋዝ አቶ በዛብሀን ፣ ታዛቢ አሳላፊ ኪዳኑን ሾመው ሳለ ወደ መጨረሻው ጊዜ በቴዎድሮስ ላይ ሁሉም መሸፈቱን ባዩ ጊዜ ፣ እርሳቸውም ከ1854 ዓ. ም. ዠምሮ የሸዋ ንጉሥ ነኝ ብለው በዚሁ «በዛብህ የሸዋ ንጉሥ» እያሉ መጻጻፍ ስለ ዠመሩ ፣ ቴዎድሮስ ይኸን ሰምተው ሲሔዱባቸው እየሸሹ አልተጠመዱም ። በ1857 ዓ. ም. ምኒልክ ከመቅደላ አምልጠው ሸዋ የገቡ ጊዜ ተዋግተው ፣ ቀጥሎም እጃቸውን ከሰጡ በኋላ አድመሃል ተብለው ተገደሉ ። በዦግንነት የገነኑ ናቸው እንጂ የመስፍንነት ዘር የላቸውም ። ስለዚህ ቴዎድሮስ የሸዋ አበጋዝ ብለው ሥልጣን ወስነው ሾመዋቸው ነበር እንጂ ፣ የመርድ አዝማችነት ማዕርግ እንዳል ሰጡዋቸው ባለፈው አውስተናል ።

## ሁለተኛ መደብ

ሁለተኛው መደብ ባፄ ቴዎድሮስ ላይ ሸፍተው ጉዳት ሳያመጡ ለርሳቸውም ታምነው በብዙ የጦር ግንባር እምብዛም ሳይሳተፉ ሳይሾሙ ፣ አንዳንዶቹም ከተሾሙ በኋላ በጥርጣሬ በእስራት ወይም በግዞት በመቅደላ እንደዚሁ የተቀመጡና እንግሊዞች ሲመጡ የተፈቱትን ቁጥራቸው በርከት ያሉትን እናስታውሳለን ። ከነዚህም ውስጥ ከላይ ከነገሥታት ከነፋሲል ፣ ከነኢያሱ የሚወለዱት ዐፄ ዮሐንስ የእቴጌ መነን ባለቤት ፣ አቤቶ ዳርጌ የንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ልጅ ፣ ባልጋዳ አርአያ ድምፁ ያፄ ዮሐንስ አጐት ፣ ዋግ ሹም ተፈሪ የዋግሹም ወሰን ልጅ ፣ የዋግሹም ከበደ አባት ናቸው ። ተፈሪ የስመ ጥሩው ዦግና የደጃች ኃይሉ እያት መሆናቸው ነው ። ከእነዚህም በቀር ሌሎች እምብዛም ስማቸው የማይታወቅ አሉ ። እነዚህ ሁሉ ወደፊት በየምዕራፉ ስማቸው ተጠቅሶ ስለሚገኝ ፣ መዘርዘር አስፈላጊ መስሎ አይታይም ።

# ሦስተኛ መደብ

በሦስተኛው መደብ የራሳቸው መኳንንትና ሹማምንት ይገኛሉ ። እነዚህ መኳንንትና ሹማምንት ግማሾቹ እንደነራስ እንግዳ ፣ እንደነራስ ውቤ ፣ እንደነፊታውራሪ ገብርዬ አብሮ አደግ ጓደኛ ሆነው የኖሩ ፣ የቀሩትም ከነገሡ በኋላ ገብተውላቸው የማዕረግ ስምና ሹመት እየሰጡ ራስ ፣ ቢቶደድ ፣ ደጃዝማች እያሉ ያሳደጉዋቸው የቅርብ የሥራ ጓደኞቻቸው ናቸው ። አገር በማስተባበር ረገድ ቴዎድሮስ በተያያዙት የአንድነት ግንባር ፣ በውጊያም ፣ በሌላውም የሥራ መስክ የተካፈሉ አሁንም ከጥቂቶቹ በቀር የእንግሊዝ ጦር በመጣበት ጊዜ ሳይከዱ የመከቱ ፣ የሞቱ ፣ የቆሰሉ ፣ የተማረኩ ፣ ወይም ተስፋ ቆርጠው እጃቸውን የሰጡ ይገኙባቸዋል ። ዝርዝራቸው በመጽሐፉ መጨረሻ ላይ ይገኛል ። በነዚህ የጦር አለቆች የሚታዘዝ ያፄ ቴዎድሮስ ነዋሪ የጦር ቁጥር 50,000 ፈረሰኛ ፣ 70,000 የእግረኛ ጦር እንደ ነበር ይገመታል ።([1])

1 Gli Italiani in Africa Orientale - A Del Bocca p. 22



# ምዕራፍ ሐያ አራት

## ከቀብዓተ ንገሥ የሠረፀ የፈላጭ ቆራጭነተ መብተ ፣ የባላገርና የነጋዴ የችግር ደረጃ

በዘመኑ በኢትዮጵያ የቤተ መንግሥቱም ፣ የቤተ ክህነቱም ያስተዳደሩም ፣ የፍልስፍናና የፍርዱም መሠረት መጽሐፍ ቅዱስ ወይም ምንጩ እርሱ ሆኖ ሊቃውንት ከዚያ ላይ የራሳቸውን አሳብ እየጨማመሩ ያቀነባበሩት እንደ ቄርሎስ ፣ እንደ ዮሐንስ አፈወርቅ ያለው መጽሐፍ እንደዚሁም ለፍርድና ለአስተዳደር ፣ ለጋብቻና ለፍቺ የተዘጋጀው ፍትሐ ነገሥት ነው ።

ነገሥታቱ የሚመኩባቸው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከፍተኛ ሥፍራ የያዙት የነገደ ይሁዳ ቅርንጫፎች ዳዊትና ሰሎሞን ናቸው ። የሚቀመጡበትን ዙፋን መንበረ ዳዊት ማለታቸው ፣ ኒሻኑን በሰሎሞን መሠየማቸው ፣ ጸሎቱ ሁሉ የዳዊት መዝሙር መሆኑ ከዚሁ እምነት ጋር የተያያዘ ነው ። በዚህ ምክንያት የቤተ ክህነት መሪዎች በነርሱ መንፈሳዊ መሪነትና ዕውቀት ውስጥ የሚተዳደሩት መሳፍንትና መኳንንት ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጭ ያሉትን የፈረንጆችን ነገሥታት ሁሉ አረመኔዎች ፣ ዕውቀታቸውም የአሕዛብ ዕውቀት እንደሆነ ያምናሉ ። ኢትዮጵያ ከአውሮፓ ዕውቀትና ሥልጣኔ ለብዙ ዘመናት ርቃ የኖረችውም በዚህ ምክንያት ነው ።

ስለዚህ ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በብሉይ ኪዳን በሳሙኤል አንደኛ ፣ «እግዚአብሔር እስከ ምድር ዳርቻ ይፈርዳል ፤ ለንጉሥ ኃይል ይሰጣል» ይላል ።([1]) በሌላ በኩል ደግሞ ፣ መሢሐን (ንጉሤን የቀባሁትን) አትንኩ ። በሐዲስ የሐዋርያት አለቃ

1 - 1ኛ ሳሙኤል 2 ቁጥር 10

ቅዱስ ጴጥሮስ «እግዚአብሔርን ፍሩ ፤ ንጉሥን አክብሩ» (1) በሌላ ቦታ ላይ ደግሞ ፤ «ባለክንፎችም (ወፎች) ቢሆኑ ይናገራሉና በልብህ አሳብ እንኳን ቢሆን ንጉሥን አትሳደብ . . . » (2) የሚለው ቃሉ ሁሉ ለመሳፍንቱና ለመኳንንቱ የመመሪያ ቃላት ናቸው ።

ይኸን የመሳሰለ ጥቅስ በያለበት ስለአለ ፤ ሊቃውንቱ ይኸን አምነው ሌላው እንዲያምን የሚያስተምሩት ፤ የተማረውም ቃሉን አክብሮ የሚጠብቀው ነው ። በዚህ ምክንያት በኢትዮጵያ አንዱ ንጉሥ ሞቶ ሌላው ሲነግሥ ፤ ወይም በጦርነት ሌላውን አሸንፎ ቅብዓ መንግሥት በጳጳስ እጅ ተቀብቶ አዲስ ስመ መንግሥት ተቀብሎ ፤ በቤተ ክርስቲያን ከነገሠበት ቀን ዠምሮ በላዩ ላይ አምላክ እንዳደረበት እንደ ቅዱስ ፍጡር ተቆጥሮ የሚናገረውም ፤ የሚያዘውም እንደ እግዚአብሔር ቃልና ትእዛዝ ይከበራል ።

አለቃ ተክለ ሥላሴ (ጢኖ) የሚባሉት ያፄ ሱስንዮስን ዜና መዋዕል የጻፉት ፤ ራስ የማነ ክርስቶስ በንጉሡ በሱስንዮስ ላይ ስለ ሸፈተ ፤ እርሱን በአነጋገር ሲወቅሱ ፤ «ንጉሥ የፈቀደውን ለማክበር ፤ የጠላውን ለማዋረድና ለማደህየት በዓለም ውስጥ ሥልጣን ያለው የእግዚአብሔር አምሳል ፤ (ምስለኔ ወኪል) መሆኑን አላወቀም ነበር . . .» እያሉ ዘልፈውታል ።(3) ያፄ ኢያሱ አድያም ሰገድ ጸሐፌ ትእዛዝ አዛዥ ሐዋርያ ክርስቶስ ፤ «የንጉሥ ትእዛዝ ፤ የእግዚአብሔር ትእዛዝ ነው ። የንጉሥን ትእዛዝ የሰማ ፤ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ይሰማል» ብለዋል ።(4)በዚህ ዐይነት ንጉሥ እገሌ ይታሰር ወይም ይፈታ ፤ እገሌ ይገደል ወይም ይዳን ፤ የእገሌ አገር ይዘረፍ ወይም ይትረፍ ሲል መሠረታዊው አዛዥ በርሱ ያደረው አምላክ እንጂ ፤ ንጉሡ ራሱ አይደለም ማለት ነው ።

---

1 የጴጥሮስ መልእክት 2—ቁ. 13
2 መጽሐፈ መክብብ 10 ቁ. 20
3 እስመ ኢያእመረ ከመ ንጉሥ አምሳለ እግዚአብሔር በውስተ ዓለሙ ለዘፈቀደ ያከብር ወለዘፀልዓ የሐሥር ወያነዲ..........
4 Annales Johannes Iyasu I - Bakaffa - I Guidi pp. 162



ራሳቸው ዐፄ ቴዎድሮስ ፤ እግዚአብሔር በራሳቸው ውስጥ አድሮ ይኸን ሁሉ የሚያደርጉት በርሱ ፈቃድ መሆኑን ከልብ ያምናሉ ። የጐንደር ቀሳውስት ወደ መቅደስ ሲገቡ ጥምጥማቸውን እያወለቁ በመግባታቸውና እርሳቸው ፊት በቀረቡ ጊዜ ግን ፤ እንደ ጠመጠሙ መቅረባቸው ቅር ብሏቸው ስለ ነበረ በ1849 ዓ. ም. «እኔ ፊትም ስትቀርቡ ጥምጥማችሁን አውልቁ ። ጥምጥሙን ሳያወልቅ የቀረበ ይቀጣል» የሚል ዐዋጅ ዐውጀው ስለ ነበር ፤ ይኸም በካህናት ዘንድ ቅሬታን መፍጠሩ አልቀረም ።

በዚህ ምክንያት ፤ ካህናቱ «ጥምጥም ክብራችን ነውና ይበይኑልን (ይፍቀዱልን)» ብለው ባመለከቱ ጊዜ ፤ «ከታቦት (መቅደስ) በገባችሁ ጊዜ ስለምን ጥምጥማችሁን ታወልቃላችሁ ?» ብለው ጠየቁ ። ካህናቱም ታቦቱ በሚገኝበት በመቅደሱ ውስጥ አምላክ ያድርበታል ለማለት ፤ «እግዚአብሔር አድሮበታል ብለን ነው» ብለው መለሱ ። ለዚህ መልስ ንጉሡ ቀጠል አድርገው ፤ «በኔ እግዚአብሔር አላደረብኝም ? እግዚአብሔር በኔ አድሮ አይደለም የምገዛ ?» ብለው በጠየቁ ጊዜ ፤ ካህናቱም «አወን» ብለው መለሱ ። በዚህ ጊዜ ባቀረቡት ጥያቄ ካህናቱ መረታታቸውን ስለ አመኑላቸው ተደስተው ፤ «እኔ ሥራት ላስተምራችሁ ብዬ ነው እንጂ ጠምጥሙ» ብለው ፈቀዱላቸው ። (1)

ቴዎድሮስ ዙፋኑንም ፤ ዘውዱንም በእግዚአብሔር ፈቃድ ከእግዚአብሔር እንደ ተቀበሉት በማመን ፤ አንድ የሚያበሳጭ ነገር በገጠማቸው ወይም ባላጋራዎቻቸው በርሳቸው ላይ የስድብ ወይም የንቀት ቃል መወርወራቸውን በሰሙ ቁጥር ፤ «እግዚአብሔር አምላክ የሰጠኸኝም አንተ ፤ እኔ በፈቃዴ አላደረግሁት ። አሁንም ይኸን ግፍ ተመልከት» እያሉ ባላጋራዎቻቸውን ከአምላካቸው ፊት ያሳጡ ነበር ። (2)

እላይ እንዳልነው ፤ በዘመናቸው ካባቶቻቸው የወረሱትን መንፈሳዊ ዝንባሌንና እምነትን በማጽናት ፤ እንደ ዘመኑ የአጻጻፍ ባህል እንኳን ላገራቸው ሰው ለውጭ አገር መንግሥታት እንኳ ደብዳቤ በጻፉ ቁጥር ፤ የደብዳቤያቸው መቅድም የሚያደርጉት «በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ ፤ ባንድነት በሦስትነት እግዚአብሔር መርጦ ያነገሠው ንጉሠ ነገሥት

---

1 አለቃ ዘነብ ጽፈውት ኢኖ ሊትማን ያሳተሙት ገጽ 27
2 አለቃ ዘነብ ገጽ 2

ቴዎድሮስ ዘኢትዮጵያ» የሚል ነው ። ለማናቸውም የውጭ አገር ቆንሲሎችም ሚሲዮናውያንም የሚጽፉት ደብዳቤ በዚህ መቅድም መዠመር አለበት ። በደብዳቤያቸው ውስጥ ፣ «በእግዚአብሔር ኃይል ይኸን አደርግልሃለሁ ፤ በእግዚአብሔር ኃይል መልካም አድርጌ አሰናብትሃለሁ ፤ በእግዚአብሔር ኃይል ስንገናኝ እንጫወታለን» የሚሉ ቃላት እንደሚያከሉ ከየደብዳቤዎቻቸው ላይ ይነበባሉ ።

ስለዚህ ፣ በዚህ ዐይነት የነገሠው ንጉሥ በዙፋን ተቀምጦ የፈቀደውን ቢያደርግ ፣ ያለፍርድም ቢገድልና ቢወርስ የሚያደርገው ሁሉ በእግዚአብሔር ፈቃድ ነው ተብሎ ስለሚታመን ፣ በንጉሥ ላይ ተነሥቶ ከሚሸፍተው ይልቅ ከተቀባው ንጉሥ ጋር ተባብሮ ክፉውንም ፣ ደጉንም አብሮ እየታዘዘ የሚፈጽመው ይበልጣል ። ከፍጥረቱ ርኅሩኅነት ፣ ቅንነት ፣ ትክክለኛነት ጠባይ ያለው እንኳን ቢሆን ፣ በተለይ ከድህነት አንሥተው በሹመት ያሳደጉት ወገን ወደዚህ ንጉሣዊ ድርጅት ከገባበት ቀን ዠምሮ ከልቡ ያልፈቀደውን ወንጀል ለመሥራት ይገደዳል ። ምንም ያድርጉ አሳድገው ለማዕረግ አብቅተውኛልና አብሬ እሞታለሁ የሚለው ብዙ ነው ። ሆርሙዝ ራሳም የራስ ኪዳነ ማርያምን ጠባይ ባመሰገነበት ገጽ ላይ ፣ «በንጉሡ ትእዛዝ ካልሆነ በቀር በራሱ ፈቃድ የማንንም ደም ማፍሰስ የማይወድ ደግ ሰው ነው» ይላቸዋል ።(1) በንጉሡ ትእዛዝ ግን ፣ እንደ ሌላው ሁሉ በትእዛዝ ሲዘርፉ ፣ ሲገድሉ ንጉሣቸውን ለምን ብለው ምክንያት የማቅረብ መብት የላቸውም ማለት ነው ።

ከዚህም ከመንፈሳዊው ትእዛዝና እግር ብረት ጋር የማኅበራዊው አቅዋም ፣ የኤኮኖሚው አውታር በግድ በንጉሡ ጥገኝነት መኖርን ፣ የንጉሡን ፈቃድ ለመፈጸም መትጋትንና እርሱን በማናቸውም ረገድ ለማስደሰት መጣጣርን ይጠይቃል ። ከባሻ ዠምሮ እስከ ራስነት ያለውን የማዕረግ ስም የሚሰጥ ፣ ከሱቲ ዠምሮ እስከ ላንቃ ካባ የሚሸልም ፣ ከአንዲት ቁራጭ መሬት ዠምሮ ሰፋፊ መሬት በመትከል ርስት ጉልት የሚሰጥና የሚነሣ እርሱ ነው ። ኃጢአትን አቅልሎ ነጻ ለመልቀቅ ፣ አክብዶ ለመግደል ሙሉ ሥልጣን ያለው እርሱ ነው ።

1 Narrative of the Abys. Exped. pp. 167.239



በንጉሡ እጅ የተጠቀለለው የንብረት ፣ የሹመት ፣ የእስራትና የሞት ሥልጣን ለንጉሡ በሙሉ የመታዘዝን ግዴታ ስለሚያስከትል ፣ ቴዎድሮስ በዘመናቸው የሠሩት ሁሉ ደገኛውም ፣ ክፋውም ከዘመኑ መንፈሳዊ እምነትና ከሹማምንት ፣ ከመኳንንትና ከመሳፍንት ፣ ከካህናት ፣ ከዕጨጌና ከጳጳስ ኅብረት ጋር የተያያዘ ነው ። ንጉሥን ለማስደሰት ሲል ወንድም ከወንድሙ ፣ ልጅ ከአባቱ ይዋጋል ። ዋግሹም ገብረ መድኅንን እጃቸውን ይዘው ለቴዎድሮስ ሰጥተው ያሰቀሉ የገዛ ወንድማቸው ዋግሹም ተፈሪ መሆናቸውን ባለፈው አንብበናል ። የአማራ ሳይንቱ ባላባት ደጃች ትኩ ብርሌ በሸፈቱ ጊዜ ተዋግተው የያዙዋቸው የገዛ ልጆቻቸው ናቸው ።(1)ሆኖም ከዚሁ ከእምነቱ ጐን የመሸለሙ ፣ በሹመት የማደጉ ምኞት ማናቸውንም አስቀያሚ አድራጐት ለመፈጸም እንደሚገፋፋ የታወቀ ነው ።

ይኸ ሁሉ ሲሆን ፣ ያጼ ቴዎድሮስን ማናቸውንም አድራጐታቸውን የቤተ መንግሥቱም ፣ የቤተ ክህነቱም ወገኖች በሙሉ ተቀብለውታል ማለት አይደለም ። ግማሹ በመሸፈት ፣ ግማሹ በሐሜታ ፣ የቀረውም በግጥምና በሮሮ አነጋገር ዐልፎ ዐልፎ መቃወሙ አልቀረም ። ሊቀ መኳስ ኃይሉ የሚባሉ ምክትል የእስር ቤት አለቃ ዐፄ ቴዎድሮስ በመቅደላ የታሰረውን ይገደል ብለው ባዘዙ ጊዜ ፣ « . . . እነዚህን ሁሉ እስረኞች መፍጀት ምንድነው ?» ብለው በድፍረት እንደ ተናገሩ ሬቨራንድ ስቴርን በመጽሐፋቸው አስፍረዋል ።(2) የቀረውም የሕይወት ጉዳይ የቤተሰብ ኃላፊነት እያስገደደው በዝምታ ይኖራል ፤ ወታደሩም የጦር መኰንኑም ፣ ወደደም ጠላም ዝመት በተባለበት ይዘምታል ። ይኸኛውን ወረዳ ምታው ፤ ዝረፈው ፤ ይኸኛውንም ዕለፈው የተባለውን እንደ ታዘዘው ይፈጽማል ። ዘረፋና ግድያ ቅር በሚለው መኰንንና ወታደር ጐን ዘረፋና ሁካታ ደስ የሚለው ፣ በዘረፋ ንብረቱን የሚያደረጀው ወገን የሰላሙን ጊዜ ላይፈልገው ፣ የጦርነቱንና የዘረፋውን ጊዜ በናፍቆት ሊጠብቀው ይችላል ።

1 አለቃ ዘነብ..........ገጽ 44

2 The Captive Missionary. P. 221

በዚህ መካከል የሚያሳዝነው በግብርና የሚኖረው ባላገር ፣ በንግድ የሚዋትተው ነጋዴ ፣ በእጅ ሙያ የተሠማራው የእጅ ጥበበኛ ነው ። አንድ ቀንደኛ በሚኖርበት ወረዳ በሽፈታ ቁጥር የሸፈተው በሞተ ፣ በተማረከ ፣ ወይም ሸሽቶ ባመለጠ ጊዜ በእርሱ ላይ ሊዘምት የመጣው ጦር የንጉሥ ጠላት አሳድረሃል ፣ አብልተሃል ፤ ስንቅ አቀብለሃል ፤ ደብቀኸዋል በሚል ሰበብ አስባብ ሲዘረፍ ፣ ሲበዘበዝ ፣ ሲታመስ ይኖራል ። በዚህም ፣ በሌላውም በሰው ልጅ ማኅበራዊ ኑሮ ውስጥ ያንዱ ሐሣር ላንዱ ክብር ፣ ያንዱ ድህነት ለሌላው ክብረት መሆኑ ያሳዝናል ። ተራ ወታደር ፣ ባላገር ፣ ነጋዴ ፣ አሽከር ባጠፋ ጊዜ መንቆር በሚባል የዕንጨት ግንድ ታስሮ እንደ ቆመ የሚውለው ወይም ከባድ የዕንጨት ሰፌድ ባንገቱ አጥልቆ እንደ ተቀመጠ የሚሠቃየው ለተመልካች ያሠቅቃል ። ባል በሸፈተ ጊዜ ሚስት ፣ አንዱ በሸፈተ ቁጥር የቤተሰብ አባሎች ተይዘው ባልፈጸሙት ጥፋት ይቀጣሉ ። (1)

በሌላውም በሰላሙ ቀን ለመንግሥት አድሮ ትንሽ ሹመት የተሾመው ፣ ባይሾምም ጠበንጃ ይዞ የመንግሥት አሽከር የሆነው ሁሉ በገበሬና በነጋዴ ላይ በብዙ መስክ የበላይነት እያሳየ ፣ ብዙ የዕብሪት ሥራ ሊፈጸምበት ይችላል ። ዓመት እርሶ በጐተራው ያስቀመጠውን ፣ በአጋሰስ ወይም በአህያ ጭኖ ፣ በእግሩ ተጉዞ ፣ ባመት በሁለት ዓመት ነግዶ የቋጠረውን ጥሬ ብር ባንድ የዘመቻና የዘረፋ ወቅት ሊያጣው ይችላል ። አብዛኛውን ጊዜ ለተቀባው ንጉሥ አቤት ብሎ ፍርድ የማግኘቱ ነገር ላንድ ተራ ባላገርና ነጋዴ እንደ ሰማይ ይርቅበታል ። አቅራቢዎቹና አስተናባሪዎቹ በግድ ሹማምንቱ ስለሆኑ ፣ ወታደርን ወይም የጦር መኰንንን ከሶ ፍርድ ባደባባይ ካገኘ በኋላ ቀጥሎ በሌላ ቀን ፣ በሌላ ሰበብ አስባብ የሚደርስበትን አስቀድሞ በማሰብ ዐርፎ እንደበቱን ሰብስቦ ፣ እግዚአብሔር ቢፈርድብኝ ነው የተረፈው ይበቃኛል ብሎ ይቀመጣል ። ጻድቁ ዮሐንስ አቤት ባይ በሹማምንት እንዳይቸገር ደወል ከውጭ አበጅተውለት ነበር ይባላል ። ዘዴያቸውን የቀሩት ነገሥታት የተከተሉት አይመስለኝም ።

1 የእስራት ዘመን በአበሻ አገር..........ገጽ 253



ከዚህም ጋር ነጋዴ ይኸን ሁሉ የዘረፋ ጊዜ ዐልፎ ምንም ነግዶ ቢከብር ፣ ገበሬ ምንም እርሶ ሀብታም ቢሆን ፣ ለመንግሥት አሽከርነት አድሮ በሹመት በሽልማት እንዳደገው ሹም የመከበር መብት የለውም፡፡የፈቀደውን ጌጠኛ ልብስ ለብሶ ፣በቤቱ ጠጅ ጠምቆና ሠንጋ አርዶ ደስታውን ከቤተሰቡ ጋር የመካፈል መብት የለውም ። (1)በዚህ ምክንያት ብዙ ነጋዴ ንግዱን እያቋረጠ፣ብዙ ባላገር ሞፈር ቀንበሩን እየተወ ወደንጉሥ ወይም ንጉሥ ወደ ሾመው ሻለቃ ተጠግቶ ባሽከርነት በማገልገል ሹመትና ሽልማት ለማግኘት ደጅ ሲጠና ይኖራል ። ባላገር በባላገርነቱ ፣ የእጅ ጥበበኛ በእጅ ጥበበኛነቱ ሲሰደብ ፣ «ወታደር» የንጉሥ ሎሌ በመባሉ ይኰራል ፣ ይመካል እንጂ አይሰደብም ። ነገሥታቱም ለክብራቸውና ለዙፋናቸው አጠባበቅ ሲሉ ይኸኛውን የወታደሩን ክፍል በመደጋገፍ ያደረጁታል ። ከግብርና ከንግድ ወጥቶ ለመንግሥት ያደረው ወታደር በዚህ ጊዜ ራሱ በመዘረፍ ፈንታ ዘራፊ ይሆናል ማለት ነው ። በመንግሥት ወይም በንጉሥ ትእዛዝ ሲሆን ዘረፋና ብዝበዛ አያስቀይምም ። በበዓል ቀን ከግብር በኋላ መኳንንቱ በንጉሣቸው ፊት ፣

«ዘራፍ ! ዘራፍ ! ያንተ አሽከር የነፍስ ቢሱ
በደም ይዋኛል ከነአውራሪሱ»

ብለው በመፎከር ለገዳይነት ፣ ለደም አፍሳሽነት ፣ ለዘራፊነት ዋጋ ይሰጡታል ማለት ነው ።

1 ሀብትና ጤንነት — መዓዛ ለማ — ገጽ 9—14

# ምዕራፍ ሐያ አምስት

*ያፄ ቴዎድሮስ የመልክ ቅርፅና ጠባይ ፡ ሰፊ ምኞትና ውሱን ዐቅም*

በኢትዮጵያ የቆየ ያጻጻፍ ልምድ የነገሥታት ፡ የመሳፍንትና የመኳንንት የሕይወት ታሪክ ሲጻፍ ፡ ስለ ጠባዩና ስለ መልኩ ቅርፅ መጻፍ እምብዛም የተለመደ አይደለም ። ምክንያቱም ፡ ከተጻፈ ሁሉንም እንደ መልአክ መልካም ፡ እንደ ሰሎሞን ጠቢብ ፡ እንደ ኢዮብ ታጋሽ ፡ እንደ ኢያሱ ወልደ ነዌ ተዋጊ ዠግና ማለት አለ ። ያለዚያ ግን ፡ አንዱ ጸሐፊ ያንዱን ንጉሥ መልክና ጠባይ በትክክል ለመግለጽ ቢሞክር በጤና ፡ በነጻነት ሊቀመጥ አይችልም ። በዚህም ምክንያት ያፄ ቴዎድሮስን ታሪክ የጻፉት አለቃ ዘነብም ፡ አለቃ ወልደ ማርያምም ስላፄ ቴዎድሮስ መልክና ጠባይ አልጻፉም ።

በዚህ ረገድ ፡ የመሪዎቻችንን መልክና ጠባይ በተቻለ መጠን ልንረዳ የምንችለው ፡ አገር ጐብኚዎችና ቆንሲሎች በጽሑፍ አሥፍረው ካቆዩን መጽሐፍ ውስጥ ነው ። እነርሱም ያገሪቱን ታሪክ ወይም አቀማመጥ ለመጻፍ ወይም ለስብከት ፡ አለዚያም ለንግድ ጉዳይ መጥተው ከንጉሡ ነገሥቱ ጋር በተገናኙበት ቀን እንደ መዠመሪያ ተግባር አድርገው የሚቈጥሩት የንጉሡን መልክ አይተው በጽሑፍ ማሥፈር ፡ ከዚያ በንግግር ጊዜ ውሎ በማደርም ጠባዩን ወደ ማጥናት አዘንብለው ፡ ይኸንኑ ወዳ ገራቸው በሚመለሱበት ጊዜ በመጽሐፍ ቅጽ ያወጡታል ።

ስለዐፄ ቴዎድሮስ መልክና ጠባይ በአጠገባቸው እንደ ቆንሲል ሆነው ፡ በኢትዮጵያ ከቆዩት ውስጥ የእንግሊዙ ተወላጅ ፕሎውዴን ወልተር ሺሲልና የፈረንሣዊው ቆንሲል ጉዮም ለዣን ይገኛሉ ። ፕሎውዴን ስለዐፄ ቴዎድሮስ እንደዚህ ይላል «...ንዴታቸውና ቁጭታቸው በእርግጥ ኃይለኛ ነበር ። ሰዉም ይርበደበድ ነበር ። በጣም ኃይልና ትጋት ያላቸው ቆራጥ ፡ ሃይማኖተኛና ደግ ሰውም ነበሩ ። ከፍተኛ ቁጭት በገ ጠማቸው ጊዜ እንኳን ጨዋነታቸውን አይቀንሱም ነበር ። . . .

የባሪያ ነጻነትን ፣ የቀረጥ መስተካከልን ፣ ወታደር በቀለብ እንዲያድር እንጂ በባላገር ላይ ተጽዕኖ እንዳያደርግ ይመኙ ነበር ። ከዚህም ሁሉ ጋር ፣ የጥንቱን የኢትዮጵያን ገናና መንግሥትነት ለመመለስ ከላይ (ከአምላክ) እንደ ተላኩ ያምኑ ነበር . . . » ([1])

የፈረንሣዩ ወኪል በበኩሉ ፣ « . . . መካከለኛ ቁመት ከአስደሳችና ግልጽ ፊት ጋር ፣ አመለካከታቸው (በዐይናቸው ትኩር ብለው ሲያዩ) ድምቀት ያለውና የሚወጋ ።([2]) በጠቅላላው የመልካቸው ቅርፅ (ሰውነታቸው) ሌሎችን በበታች አድርጎ ለመግዛት ያላቸውን ጽኑ ፈቃድ ያሳያል . . . ኃይለኛና ኩሩ ሆነው የተወለዱ ናቸው . . . » ([3])

በኢትዮጵያ ኅብረተሰብ ባህል ውስጥ የመጠሪያ ስም አወጣጥ በጸሐፊዎች ዘንድ በደንብ ያልተጠና ፣ ነገር ግን ሰፋ ያለ ሚና የተጫወተ መሆኑ አይጠረጠርም ። ንጉሥ የነገሠለትና ጳጳስ ሲጳጳስ የቀድሞ መጠሪያ ስማቸውን እየተዉ አዳዲስ ስመ መንግሥትና ስመ ጵጵስና መውሰዳቸው በስሞች ውስጥ ደረጃና ልዩነት እንዳለ እንረዳለን ። የነዚህም ከመጠሪያና ከክርስትና እንደዚሁም ከቅጽል ስም ጋር ያለው ተደባልቆ ፣ የያንዳንዱ የመጠሪያ ስም ከነምክንያቱ ተዘርዝሮ ቢጻፍ ደንበኛ መጽሐፍ ይወጣዋል ።

መጠሪያ ስም በተለይ የአማራና የትግሬው ቤተሰብ በጣም ተበታትና ለሁሉም ከመሠራጨቱ በፊት በየኅብረተሰቡ ያለው ያንዱ ከሌላው ተለይቶ ይታወቅ ነበር ። የወንዱን ወገን ብቻ ለመመልከት ነጋሥያን ፋሲል ፣ ኢያሱ ፣ ዳዊት ፣ ሰሎሞን ፣ ምኒልክ ፣ . . ጳጳሳት ማቴዎስ ፣ ፊልጶስ ፣ ባስልዮስ ፣ . . . የቀለምና የቤተ ክህነት ሰዎች ጽጌ ፣ አርአያ ፣ ኀሩይ ፣ ጥበቡ ፣ ነቅዓ ጥበብ ፣ ሐረገ ወይን ፣ . . . የጦር አለቆች (በተለይ ሺዎች) ደባልቄ ፣ (ደባልቃቸው) እንዳርጌ ፣ (እንዳርጋቸው) ሺመልስ ፣ ታችበሌ . . . ለብዙዎች መጠሪያ ስም ታደሰ ፣ በቀለ ፣ አበበ ፣ . . . ልጅ የሞተባቸው ቤተሰቦች ካሣ (ካሣዬ) ፋንታ ፣ (ፋንታዬ)

1 The Blue Nile - 14 The Power of Theodore - Alan Moorehead pp. 211-212
2 Regard Vif et Perçant.
3 Theodros II - Le Nouvel Empire d'Abyssinie - Chap. VII p. 181



ዘርይሁን ፣ . . . አገልጋዮች ሰጠኝ ፣ አረሩ ፣ ቢከፋ ፣ መቻል . . . እየተባሉ ሲጠሩ ባኗኗር ደረጃ ብቻ ሳይሆን ፣ የስም ደረጃው እነሆ እስከ ጊዜያችን ደርሷል ።

ከቤተ ክህነት በኩል ፣ «ስሙ ይመርሆ ኀበ ግብሩ — ስሙ ተግባሩን ይቀይሰዋል» ወይም «የሰውዬው መጭው ዕድል እንደ መጠሪያ ስሙ ነው» የሚል ዘይቤ ስለ ተወረወረ ፣ አንዳንድ አባትና እናት ወንድ ወይም ሴት ልጅ ወልደው መጠሪያ ስም በፈቃዳቸው ለልጃቸው ከመስጠታቸው በፊት ወደ ጠንቋይ ፣ ወደ አስማተኛ ፣ ወደ ባሕታዊ በመሔድ በንጉሥ ፊት ሞገስ የሚያሰጥ የሚያሾም ፣ የሚያስከብር ፣ በሰው ዘንድ የሚያስወድድ ስም እንደሚፈልጉ ሁሉ ፣ ሌሎች ደግሞ በዚህ የማያምኑ ግድየለሾች ፣ «አዬ ወዲያ ! መጠሪያ ስም ያው እገሌ ብሎ ለመጥሪያ ወይም አቤት ብሎ ለመመለሻ ነው» ብለው አንዱን ስም እንዳገኙ የሚያወጡ ሞልተዋል ።

ነገር ግን ፣ ካህናት ስመ መንግሥት ለንጉሥ ፣ የፈረስ ስም ለመሳፍንትና ለመኳንንት ሲያወጡ ፣ ስሙ በሕይወቱ ላይ እንዲያንጸባርቅ ወይም ሥያሜውና ተግባሩ በመጠኑ ተመሳሳይ እንዲሆኑ ከፍተኛ ጥንቃቄ እንደሚደረግበት ይታወቃል ። አንበሳ ሰገድ ተብሎ የተሠየመ ንጉሥ ፈሪ የሆነ እንደሆነ ፣ አፅራር ሰገድ (ጠላቶቹን የሚያሰግድ) ተብሎ ቁጥራቸውም ቢያንስና ዐይነታቸውም ባይታወቅ ጠላቶቹን ካላምበረከከ . . . በፈረስ ስም ረገድ አባ ዳኘው ተብሎ ፍርደ ገምድል ፣ አባ መቻል ተብሎ ፣ ግልፍተኛ ፣ አባ ሰይጣን ፣ አባ ቀማው ተብሎ ፈሪ ፣ ልስልስ ገራም ከሆነ ሥያሜውን የተሸከመው ንጉሥ ወይም መኰንን የሥያሜ ስሙና ተግባሩ አልተገናኘምና ለማንም መዘበቻና መሣለቂያ ይሆናል ።

ዐፄ ቴዎድሮስ ፣ አባትና እናታቸው ያወጡላቸውና 35 ዓመት ሙሉ ሲጠሩበት የነበረውን ካሣ የሚባለውን መጠሪያ ስማቸውን ለውጠው ሲነግሡ ፣ የቴዎድሮስን ሥያሜ የተቀበሉት በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ከዚህ በፊት በንግሣቸው ምዕራፍ ላይ እንደ ጠቀስነው ፣ አስተዳደሩ በተበላሸውና አገር በተከፋፈለበት በመሳፍንት ዘመን «'ቴዎድሮስ የሚባል ንጉሥ ከወደ ምሥራቅ መጥቶ ፣ የተበላሸውን አስተዳደር አስወግዶ ፣

የኢትዮጵያን ግዛት ያሰፋል . . .’ ተብሎ ትንቢት የተነገረው ላንተ ነው» በማለት ከካህናቱ ተነግሯቸው ፤ እርሳቸውም አምነው በመቀበል በዚሁ ሥያሜ ዘውድ ደፍተው ሲነግሡ ፤ በትንቢት የተነገረውን በተግባር ለማሳየት ወዳንድ የሞራል ግዴታና ኃላፊነት ገብተዋል ማለት ነው ።

እንኳን የራሱ ምኞት ተጨምሮ ለዚህ ተገቢ ሆኖ ሲገኝ ይቅርና አንዱን ሰው እንደዚህ ነህ ካሉት ፤ ባይሆንም ለመሆን ይጣጣራል ። ከመልኩ የበለጠ የሰው የሞራሉ አቅዋም በየሰበቡ ይለዋወጣል ። በአጋጣሚ ከሹመት የወደቀው ሞራሉ ሲወድቅ ዕውቀቱና አስተያየቱ ሁሉ እንደሚበላሽ ፤ አንዳንዱ ደግሞ ሹመት ሲጨብጥና ወደሚ ኘው ዕድገት ደረጃ ከፍ ባለ ቁጥር ዕውቀቱ ፤ አስተያየቱ ከሥራው ልምድ ጋር እያደገ ይሔዳል ።

ባገራችን ባህል ብዙ አስመኪና አኩሪ የፈረስ ስም ያላቸው መኳንንት በሕዝብና በወታደራቸው አንደበት ደምቆ የሚጠራው የፈረስ ስማቸው እንዳይጐድፍ በጦርነትም ፤ ባስተዳደርም ጊዜ መልካም አርአያ ለማሳየት እንደሚሞክሩ በሚታዩበት ጐን እንደዚሁም ‘መልከ ጥፉ ፤ በስም ይደግፉ’ እንደሚባለው ፤ ብዙ ሰው የተሠየመበትን ሥያሜ በሥራ ለሙግለጥ ምንም ቢጣጣር የማይሆንለት እንዳለ አይዘነጋም ።

በዚህ ምክንያት ፤ ባፄ ቴዎድሮስ ላይ ያለው ችግር ከካህናቱ ወገን የኢትዮጵያን ግዛት ያሰፋል ፤ መጥፎውንም አስተዳደር ያቃናል የተባልከው አንተ ነህ ተብለው ይኸን ዓላማ ወደግብ ለማድረስ እርሳቸውም ሲጣጣሩ ፤ እነሱም ሲገፋፉዋቸው ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ፤ በተዋሕዶ ሃይማኖት የማያምን የፈረንጅ ሥልጣኔ ወዳገር እንዳይገባ ሥልጣኔውን ጠልተው በመኳንንትና በሕዝብ ዘንድ ያስጠሉታል ። ባንድ ወገን ደግሞ ፤ የመሬት ሥሪት ለማሻሻል የተጨበጠ የሥራ ፍሬ የማያሳየው ፤ በየመንደሩ በመዞር በቤተ ክርስቲያን ወገቡን እየሰበቀ ፤ ራሱን እየታጠቀ የሚያውደለድለው ደብተራ እንደ ሌላው ይገብር ወይም ላገሩ ደህንነት ለሚዋጋው ወታደር ይልቀቅ ፤ ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የተወሰኑ ቀሳውስትና ዲያቆናት ይበቃሉ ሲሉ ‘ባይናችን መጣህ’ ብለው ይጣሉዋቸዋል ። በባሪያም የአገዛዝ ሽረት ተጽፎ ባናገኘውም ፤ ከብዙው መሳፍንትና መኳንንት ጋር እንደሚጣሉ የታወቀ ነው ።



ቢሆንም ፤ ከካህናቱ መካከል በጥቅማቸውና በክብራቸው መነካት የተነሣ ግማሾቹ ሲጣሉዋቸውም ፤ ብዙዎቹ ደግሞ በዘመነ መሳፍንት የነበረውን የርስ በርስ ጦርነት ፤ የየአውራጃውን መከፋፈል ፤ በጐንደርና በደብረ ታቦር ከተማዎች የነበረውን ድልወትና ቅንጦት መበርከት በመመልከት ፤ ጠንከር ያለ ፤ ሁሉን ተቆጣጥሮ የኢትዮጵያን ስም የሚያስጠራ የማዕከላዊ መንግሥት መሪ በመጥፋቱ ፤ ይናደዱ የነበሩት የሊቃውንት ወገኖች በትንቢት የተነሡት ቴዎድሮስ የሚያደርጉትን ጥረት ከዘመናዊ ግንባታቸው ጋር በማያያዝ የሚገባ አድርገው ድጋፋቸውን እየሰጡ በወረብ ዜማ ፤ በቅኔ ድርደራ የሚያበረታቷቸው ሞልተዋል ።

ከነዚህም መካከል ቴዎድሮስ ራሳቸው ፤ «ይማሩዋል እንደ አካልዬ ፤ ይዋጉዋል እንደ ገብርዬ» ብለው ትምህርታቸውን ያደነቁላቸው መምህር አካለ ወልድ ይገኛሉ ። እርሳቸውም ቴዎድሮስ የመግደልም ፤ የማዳንም ሥልጣን ከአምላክ እንደ ተሰጣቸው ፤ ለርሳቸው አልገዛም ያሉት የሞት ሞት (ኩነኔ) እንዳገኛቸው ፤ የተገዙላቸው ግን መንግሥተ ሰማያትን እንደ ወረሱ ለማመልከት ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ሥላሴ ቅኔ ተቀኝተውላቸዋል ።

«ለሞት ወለሕይወት  
ሥልጣን ብከ ቴዎድሮስ  
እለ ኢተቀንዩ ለከ እስመ ልቃሐ ሞት ተፈድዩ  
ወወረሱ ሀገረ ሕይወት ዘለከ ተቀንዩ  
አመኒ ተሰምዓ በዜና ነገረ ብሉይ አብድዩ  
ተረፈ ኢዮስያስ ጸራልዩ  
እምጠለ ቤትከ ፍትሕ እስከ ይረውዩ  
አሰምዕ ሰብአ መሃይማነ እርአያሃ ወዘካርያስሃ ወልደ  
በራክዩ ።»

የቅኔው ፍሬ ሐሳብ ፦ ንጉሡ ቴዎድሮስ በሕይወትም ፤ በሞትም ላይ ሥልጣን ስላላቸው ‘አሜን’ ብለው የተገዙት ሕይወትን ሲወርሱ ፤ እምቢተኞች የሞት ፍዳ መቀበላቸውን ከዘካርያስ ልጅ ከበራክዩና ከአብድዩ ታሪክ ጋር እያመሳሰሉ አቅርበውታል ። ([1])

1 መጽሐፈ ቅኔ ፤ ብላታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ 1918 ፤ ገጽ 272 ፤ የማቴዎስ ወንጌል ምዕ. 23 ቁ.35

ይኸን ከመሳሰለው ከካህናቱ መንፈሳዊ ግፊት ጐን ከመኳንንት ፣ ከወታደርና ከሕዝብ የሚመነጨው ሥጋዊ ግፊት ብዙ ነው ። ከሁለቱም ወገን የሚመጣው ግፊት ቴዎድሮስ ከሚጠሩበት ሥያሜ ጋር እርሳቸውም ካላቸው የመስፋፋት ፣ የማደግ ፣ ኢትዮጵያን ለማሳደግ ካላቸው ፍላጐት ጋር ሁኔታውን ሲያሟሙቀው ፣ ሁሉም ወገኖች ራሳቸውም ቢሆኑ በመዠመሪያው ወቅት በትክክል ያላጤኑት የቴዎድሮስን አጭር ዕቅም ፣ የኢትዮጵያን ጠረፍና የወደብ ግዛት የወረሩትን የግብጾቹንና የዋናውን የቱርክን ኃይል ነው ።

ከዚህም ጋር ፣ በዚህ ዘመን ያለውን የእንግሊዝንና የቱርክን ወዳጅነት በትክክል ሳይገነዘቡት የእንግሊዝን ሕዝብ ክርስቲያንነት ከነፕሎውዴንና ከነሊቀ መኳስ ዮሐንስ (ዦን ቤል) የፈረንሣይን ሕዝብ ክርስቲያንነት ከነጉዮም ለዣን ፣ ከነአጉስት ባርደል እንደበት በመስማታቸው ፣ እነዚያም ከዚህ በፊት እንዳልነው ሐቁን እየደበቁ ለጊዜው የርሳቸውን ሞገስና ጊዜያዊ ጥቅማቸውን ለማግኘት ብቻ ፣ የቱርክን ግዛት ከኢትዮጵያ ዙሪያ ለማስወጣት ፣ ብሎም ኢየሩሳሌምን ከቱርክ እጅ ለማስለቀቅ ላቀዱት ሰፊ ዓላማ የእነዚህን መንግሥታት ትብብር እንደሚያገኙ ፣ የጦር መሣሪያም አሠልጣኝም ከነዚህ መንግሥታት እንደሚሰጣቸው ስለ ተነገራቸው ፣ ከሁለቱም የበለጠ በእንግሊዝ መንግሥት ላይ ከፍ ያለ ተስፋ ነበራቸው ።

ስለዚህ ነው — ለእንግሊዝ ንግሥት ለቪክቶሪያ ደብዳቤ በጻፉ ቁጥር ፣ «እርስዎም የክርስቶስ ልጅ ነዎት ፤ እኔም የክርስቶስ ልጅ ነኝ ፤ ስለ ክርስቶስ ፍቅር ወዳጅነት ፈልጌአለሁ . . . ደፍሬ የላክሁብዎን ከፍቶብኝ ቢገኝ ይምከሩኝ እንጂ አይከፋብኝ . . .» ያሉት ። ለነራሳም በጻፉት ደብዳቤ ላይ ፣ «. . . ለንግሥቲቱ ለወዳጄ ዕድሜና ጤና ስጥልኝ . . . እኔን የሚወዱበት ልቦና ስጥልኝ እያልሁ እለምናለሁ ፣ ፈጣሪያችንን . . .» እያሉ በጽሑፍ ደጋግመው የገለጹት ።[1] በነዚያ በኩል ግን ፣ ጉዳዩን ቀለል እያደረጉ በመመልከት ደብዳቤዎቹ ራሳቸው በውጭ ጉዳይ ቢሮ ጠረጴዛና መዝገብ ቤት ተጉላልተው እንደዚሁ ለማስታወሻ ብቻ ተመዝግበው በከንቱ የሚቀሩበት ጊዜ ሞልቷል ።

1 Oriental Documents - The Amharic Letters ....1a, 50, 80



በዚህ ምክንያት ፣ ዐፄ ቴዎድሮስና መኳንንቶቻቸው በግልጽ ያልተረዱት ፣ ከእንግሊዝ መንግሥት ጋር ወዳጅነት እንዲያደርጉ የሚገፋፉዋቸው እንግሊዞችና የውጭ አገር ሰዎች በትክክል ከወደ መዠመሪያው ላይ ያልገለጹላቸው ምናልባትም ሆን ብለው የደበቋቸው የአውሮፓ መንግሥታት ለየግል ጥቅማቸው ሲሉ ከዚሁ ለውጊያ ከሚፈልጉት ከቱርክ ጋር ያላቸውን የንግድና የወዳጅነት ስምምነት ነው ። ከነርሱ ወደኋላ በሀብትም በሥልጣኔም ከቀረው አፍሪካዊ መንግሥት ጋር ተባብረው ከቱርክ ጋር ለመጣላት እንደማይቃጡ በፍጹም አላስረዱዋቸውም ።

የመስኮብ መንግሥት ባንድ ወገን ከአውሮፓ ጉዳይ ከእንግሊዝና ከፈረንሣይ ፣ ከጀርመንና ከአውስትሪያ ጋር ሲጣላ ፣ በሌላው ወገን ወደ ጥቁር ባሕርና ወደ መካከለኛው ምሥራቅ ለመግባት ባለው ምኞት የባልካን ክርስቲያኖችን በመደገፍ እንደ አው.አቆ. 1855—1856 ዓ. ም. በክሬሚያ የተዋጋ ጊዜ የፈረንሣይና የእንግሊዝ መንግሥት ከእስላሙ መንግሥት ከቱርክ ጋር ቆመዋል ። የእንግሊዝ መንግሥት የቱርክ ጠቅላላ ግዛቱ እንዲከበር እንደ አው.አቆ. በ1854—55 ዓ. ም. ላይ ደንበኛ ውል ተዋውለዋል ። ይኸም ዘመን ፣ ዐፄ ቴዎድሮስ የነገሡበት ዘመን ነው ።

ዐፄ ቴዎድሮስ ፣ በአውሮፓ መንግሥታት ላይ ተስፋ በማድረግና የራሳቸውን ኃይል ባለመገምገም ፣ በመርከብና በምድር ጦርም ለደረጁት ለመስኮብና ለፈረንሣይ እንኳን ያልተበገረውን የቱርክን ኃይል ተዋግቼ ኢየሩሳሌምን ነጻ አወጣለሁ የሚለው ምኞታቸውን ለማጉልመስ ገጣሚው ፣

«አንተም ጌታ አይደለህ እኔም ያንተ ሎሌ
የኢየሩሳሌም ሰው ካልሜኒ በርሞሌ
ታጠቅ ብሎ ፈረስ ካሣ ብሎ ስም
ዐርብ ፣ ዐርብ ይሸበራል ኢየሩሳሌም» (*)

* ዐርብ ፣ ዐርብ በያመቱ የስቅለት በዓል በሚከበርበት ጊዜ ለማለት ይሆን?

እያለ ምኞታቸውን ያጋግለዋል ። የመርከቡም ጉዳይ በኢትዮጵያ ገና የሥራው አሳብ ሳይወጠን ፈረሰኛ ጦራቸውን ይዘው ባሕር ተሻግረው እንደሚዘምቱ ሁሉ ፣

«የታጠቅ ፈረሶች እንዴት ያሸካካሉ
ባሕር ማዶ ጨፌ መልቀም ያስባሉ
አበሻ በመላው ምን ያጉመተምታል
በመርከብ ተሻግሮ ገና ባሕር ይዘምታል»

እየተባለ ተገጥሟል ።

የግጥሙ ድርደራ ለአንባቢና ለሰሚ ቢያስደስትም ፣ በጠቅላላው ከእውነተኛ መንገድ ጋር ያልተያያዘ መሆኑ ግልጽ ነው ።

ወደ መጨረሻ ዘመናቸው በመንግሥታቱ ተስፋ በከንቱ መታለላቸው ፣ የነጋሪዎቹንም አስተኝነት የርሳቸውም ዐቅም በጣም ያነሰ መሆኑን በሙሉ ተረድተውታል ።



ዐፄ ቴዎድሮስ
(ከሪቻርድ ፓንክረስት መጽሐፍ )



ዐፄ ቴዎድሮስ
(ከወልደማዬር ቲዎፊል መጽሐፍ)

# ምዕራፍ ሐያ ስድስት

## ዐፄ ቴዎድሮስ የውጭ ጉዳይ ግንኙነታቸውና አገራቸውን ለማሠልጠን ያላቸው ጽኑ ፍላጎት

ዐፄ ቴዎድሮስ፣ በጠቅላላው የንጉሥነት ሕይወታቸው ሲገመገም ስፊ ምኞት ያላቸው ሆነው ይገኛሉ ። በንጉሠ ነገሥት አቅዋማቸው ራሳቸውን የሚገምቱት ከማንም የዓለም መሪ እንደማያንሱ አድርገው ነው ። እንደ ቀደምት ነጋሥያን አባቶ ቻቸው በሥልጣኔ ወደኋላ ቢቀሩም፣ አድር ባይ ካህናት ከየትም ቆጣጥረው ከእሥራኤላውያን ነገሥታት ከዳዊት፣ ከሰሎሞን ሳያዛምዷቸውና ከዚያም መወለዱ ብቻ እንደሚያስከብር ሳያሳ ምኗቸው አልቀሩም ። ይኸም፣ እላይ እንዳልነው፣ የርሳቸው ብቻ ሳይሆን ከዛጉዬዎች በቀር የቀደሙት ነገሥታት ሁሉ ጽኑ እምነት ነው ። እርሳቸውም ለንግሥት ቪክቶሪያ በጻፉዋ ቸው ደብዳቤዎች ባንደኛው፣ «...... እኔ ከተወለድሁ ፈጣሪዬ ከዐመድ አንሥቶ ኃይል ሰጥቶ ባባቶቼ መንግሥት አቆመኝ» ካሉ በኋላ፣ በሌሎቹ ደብዳቤዎቻቸው መቅድም፣ «የእግዚአብሔር ፍጡር ባርያው፣ የዳዊት የሰሎሞን ልጅ» ማለት ያዘወትሩ ነበር ።

የዘሩ ጉዳይ በዚህ እንዳለ፣ በነርሱ ጒን ያሉት የቤተ ክህነት ባለሥልጣኖች በበኩላቸው ዕውቀት ማለት ከእሥራኤሎች የመ ነጨው ብሉይና ሐዲስ ነው ። ከዚያም ከክርስቲያን አበው ከነ ዮሐንስ አፈወርቅ ተቀነባብሮ የመጣው የሊቃውንት መጽሐፍ፣ ከነያሬድ የፈለቀው ዜማ፣ ከነተዋነይ የመነጨው ቅኔ ነው ። ከዚህ ውጭ ያለው ከፈረንጆች አዕምሮ የተገኘው ማናቸውም ትምህርት የአሕዛብ ዕውቀት ስለሆነ ሊማሩትም፣ ሊያውቁ ትም አይገባም በሚል እምነት ከሥልጣኑ ከአክሱም ውድ ቀት ጀምሮ በነገሥታቱ፣ በዕጨጌዎቹ፣ በመሳፍንቱ፣ በሊቃ ውንቱ ስትመራ የሺ ዓመት የነጻነት ጊዜ ያሳለፈችው ኢትዮጵያ ለማናቸውም የውጭ ሥልጣኔ፣ በተለይ የሥልጣኔን ቁልፍ

ጪብጦ ለሚገኘው ለአውሮፓ መምህር ፣ በሯን በጥብቅ ዘግታ ኖረች ። አውሮፓዊው መምህርም ከኋላው የቅኝ ግዛትንና የሃይማኖትን የለውጥ መዘዝ ሳያስከትል ፣ በተለይ በዚያ የቅኝ አገዛዝ በሰፈነበት ዘመን ፣ በቅንነት ላስተምር ላሠልጥን ማለት አይችልም ። የዕውቀት መተካከል የኑሮ መተካከልን ፣ የነጻ ነትን መብት ጥያቄን ስለሚያስከትል ፣ አፍሪካዊውን አስተምሮ በዕውቀት ፣ በመብት መተካከሉን አይፈልገውም ።

አንዱ ሌላውን በዕውቀትም ፣ በሀብትም ጨቁኖ ራሱ ብቻ ገዥ ፣ ራሱ ሀብታምና ዐዋቂ ሆኖ መኖርን ይፈልጋል ። ይኸም ፍላጐት በየዘመኑ እያንጸባረቀ ፣ የጦርነት መነሻ እየሆነ ሕዝብን ሲያፋጅ መኖሩ ግልጽ ነው ። ኢትዮጵያም የሥልጣኔውን ትም ሀርት መሸሿ ለፈረንጆቹም ፣ ለቱርኮቹም ሳያስደስታቸው አይ ቀርም ።

የተናቀው የዚህ የሥልጣኔ ጉድለት ዐልፎ ፣ ዐልፎ በየምክን ያቱ ብልጭ በአለባቸው ቁጥር ወይም ከቱርክና ከግብጽ አጥቂነት የሚከላከሉበት ጠበንጃና ጥይት ባጡ ቁጥር ፣ የኢትዮጵያ ነገሥ ታት ለአውሮፓ ነገሥታት በሚጽፉት ደብዳቤ ላይ አሠልጣኝና የእጅ ጥበበኛ መጠየቃቸው ከየደብዳቤያቸው ላይ ይነበባል ።[1] ነገር ግን ፣ እስከ 19ነኛው መቶ ዓመት ድረስ አንድም የኢትዮጵያ ንጉሥ የቆየውን የተዘጋ ልማድ ከፍቶ ፣ የቤተ ክህነቱን ተጽዕኖ ሽሮ ፣ ባገሪቱ የአውሮፓን የአዕምሮና የእጅ ጥበብ ፣ የሕክምና ፣ የእርሻንና የመሐንዲስነትን ትምህርት ለማስገባት አልተጣጣ ረም ። ይኸን የመሰለውን አዳዲስና አስፈላጊ ትምህርት ለማስ ገባት ራሱ ፈቃዱ ምኞቱ በኅብረት አገሪቱን በሚመሩት የቤተ መንግሥትና የቤተ ክህነት መሪዎች አዕምሮ ውስጥ ለመፀነስ ቦታ የለውም ። የተማሪው አለመፈለግ ፣ 'ተዋቸው እንደ ተኙ ይኑሩ' የሚለው ያስተማሪው መለገም ፣ በትክክል ተገናኝተው አገሪቱን በሚያሳዝን አኳኋን በኋላ ቀርነት ያለ ሐኪም ፣ ያለ መድኃኒት ፣ ያለ መንገድ ፣ ያለ መጓጓዣ በድህነትና በሥቃይ ለረዥም ዘመን እንድትኖር አድርጓታል ።

---

1 Dernier Partie du Second Tome de L'Afrique.-Jean Temporal-pp. 130-263.



በተባራሪ ፣ በስደት አንድ ወይም ሁለት ኢትዮጵያውያን መጠነኛ ዕውቀትና ቋንቋ ከፈረንጅ አገር በችግር ተምረው ይዘው ፣ በብርቅ ወደ አገር ገብተው እንደሆነ ወይም ካንድ ሚሲ ዮን ተጠግተው ትንሽ ትምህርት ቀስመው እንደሆነ ከፈረንጅ ጋር አብሮ እየበላ ፣ እየጠጣ የኖረ ወይም በሚሲዮን ቤት ያደገ በተዋሕዶ ሃይማኖት መጽናቱ ፣ በዓል ማክበሩ ፣ ጾም መጾሙ አጠራጣሪ ስለሆነ ፣ በምንም ዐይነት በመንግሥቱ ሥልጣን ውስጥ ከፍተኛ ደረጃ ሊሰጠው ፣ ምክሩና አስተያየቱ በቁም ነገር ሊደ መጥ ወይም ተደምጦ በሥራ ላይ ሊውል አይችልም ። ሲበዛ ቢውል ፣ ለንጉሡ ወይም ለባለሥልጣኑ የግዴታ ሆኖ የአስተር ጓሚነት ወይም የተላላኪነት ደረጃ ይሰጠዋል እንጂ የራስነትን ፣ የደጃዝማችነትን ማዕረግ አግኝቶ በትምህርት የቀሰመውን የሥራ ፍሬ በባለ ሥልጣንነት ደረጃ ለማሳየት አይችልም ።

በዚሀ ምክንያት ፣ የኢትዮጵያ ነገሥታት ይኸን ላገር ልማ ትና ዕድገት ፣ ለውጭ አገር ግንኙነትም አስፈላጊ የሆነውን ትምህርት ኢንዱስትሪውንም ባገራቸው ውስጥ ስለ አላስገቡ ዐይነትና ጥራት ያለው ሸቀጥ የሚያመርት መሣሪያ ስለሌለ ፣ በማ ናቸው ም አንጻር ከውጭ መንግሥታት ጋር የሚያደርጉት የንግድ ልውውጥ ደካማ ነው ። አስፈላጊያቸው የሆነውን ሸቀጣሸቀጥ ከውጭ በምጥዋ ፣ ወይም በመተማ በኩል የሚያገኙት አገር በተፈጥሮዋ ያፈራቻቸውን ወርቅና ቡና ፣ የከብት ቆዳና የዝሆን ጥርስ ፣ ጥራጥሬና ይኸን የመሰለውን በመስጠት ብቻ ነው ። ይኸም በመንግሥት ደረጃ ሲታይ የልውውጡ ደንብ ፣ የቀረጡ መጠን ከሠልጡኑ ዓለም ሕግና ሥርዓት ጋር በትክክል ተመሳ ሳይ አይደለም ። ባገርም ውስጥ የንግድ ልውውጥ በከፍተኛ ደረጃ ከወርቁና ከብሩ በቀር አብዛኛው ዝቅተኛውና ሕዝባዊው ንግድ የሚከናወነው ዕቃ በዕቃ እየሆነ የሕዝቡም የኑሮ ደረጃ ዝቅ ያለ ፣ የመኖሪያ ቤቱም የመገልገያውም መሣሪያ ሁሉ ዐይ ነት ከጥንት ሲያያዝ የመጣ እንጂ ዘመንን ተከትሎ የተሻሻለ አይደለም ። የአብዛኛው ባላገር ነጋዴና ወታደር ልብስ ካንድ ነጠላና ካጭር ሱሪ አያልፍም ።

እንደዚሁም ፣ በዓለም ዐቀፍ ደረጃ በውጭ ጉዳይ ግንኙነት የተማረ የሰው ኃይል ከመጥፋቱ የተነሣ ፣ የቱርኮችና የዐረቦች ወረራ ባሠጋ ቁጥር የኢትዮጵያ መላክተኛ ሆኖ ወደ ውጭ አገር

የሚላከው ሰው ሁል ጊዜ ያው የውጭ አገር ሰው ነው ። ከርሱ ጋር ተደራቢ ወይም ታዛቢ ሆኖ የሚሔደው የውጭ አገር ቋንቋውንም ፣ አበላሉንም ፣ አኗኗሩንም የማያውቀው በቤተ መንግሥቱና በቤተ ክህነቱ በኩል የሚከበረው አንዱ ሊቅ ነው ። ለምሳሌ ፣ ባዬ ልብነ ድንግል የልጅነት ዘመን ኢትዮጵያን ያስተዳድሩ የነበሩት ታላቂቱ ንግሥት ዕሌኒ በ1510 ዓ. ም. ወደ ፖርቱጋል ንጉሥ ወደ አማኑኤል የላኩት ማቴዎስ የሚባለውን የአርመን ተወላጅ ነው ። ልብነ ድንግል በነገሡ ጊዜ በ1526 ዓ. ም. ወደ አማኑኤል ልጅ ወደ ዮሐንስ የላኩት የራሱን የፖርቱጋሉን ንጉሥ መላክተኛ አልቫሬዝንና በተጨማሪ አባ ጸጋ ዘአብ የሚባሉትን መነኩሴ ሲሆኑ ፣ ከዚያ ወዲህ የዐፄ ኢያሱ አድያም ሰገድ (1682 — 1706 ዓ. ም.) መላክተኛ ሙራድ የሚባል አርመናዊ ነው ። በቅርቡ ዐፄ ቴዎድሮስ በሽፍትነት ባሉበት ጊዜ የደጃች ውቤ የፈረንጅ አገር መላክተኛ ካህኑ አለቃ ሀብተ ሥላሴ ሲሆኑ ፣ የነራስ ዐሊ መልክተኞች ፈረንሣዮቹ እነ አንቷን ዳባዲ ናቸው ።(1)

አሁንም ፣ ዐፄ ቴዎድሮስ ያገሪቱን አንድነት ሰብስበው ሳይጨርሱ ፣ ሕዝቡን በተለይ በወታደራዊ ትጥቅ ለማሠልጠን ከልባቸው ሲነሡ ፣ ባገራቸው የመዠመሪያ ደረጃ እንኳን ተማሪ ቤት የለም ። ስለዚህ የርሳቸው መልክተኞችና ጉዳይ ፈጻሚዎች እንደዚያው እንደ ተለመደው ፣ የርሳቸው ዜጋ ያልሆኑት እንግሊዞቹ እነ ወልተር ፣ ፕሎውዴን ፣ ጀርመኖቹ እነ ማርቲን ፍላድ ፣ ፈረንሣዮቹ እነ ባርዴል ናቸው ። ከፓትርያርኩ ከአቡነ ቄርሎስ ጋር ወደ ግብጽ መሪ ወደ ሰይድ ባሻም የተላኩት አለቃ ገብረየስ የሚባሉት የብሉይና የሐዲስ ፣ የፍትሐ ነገሥት ሊቅ ናቸው ። እኝሁ ምሁር በአለቃ ዘነብ ብርዕ ሊቀ ማዕምራን ተብለው የተጠቀሱት በውነትም ባገራቸው መንፈሳዊ ዕውቀት የተራቀቁ ሲሆኑ የውጭውን አገር ቋንቋውንም ፣ የፖለቲካውንም ዘዴ አያውቁትም ማለት ነው ። ከልጅነት ዠምሮ ቢማሩት ግን ፣ እንደ አውሮፓዊ ሊቅ ለመሆን ምንም የሚያግዳቸው ነገር ባልተገኘ ነበር ።

እንደነዚህም ያሉት ካገራቸው ወጥተው የማያውቁት የቤተ ክህነት ሰዎች ለመዠመሪያ ጊዜ ፣ በውጭ አገር ሲገኙ ምን ዐይነት

1. የግራኝ አህመድ ወረራ — ተ.ጸ.መ. — ገጽ 63—79
Histoire de L'Abyssinie - Jones et Monroe pp. 147-154



መደናገርና ባይተዋርነት እንደሚገጥማቸውና በነርሱም አማካይነት ቁም ነገር ያለው የፖለቲካ ፣ የኢኮኖሚ ወይም የወታደርነት ጉዳይ ተነጋግሮ ፣ ተከራክሮ ወደ ፍጻሜ ለማድረስ ያላቸውን የችሎታ አቅዋም ለመገመት ቀላል ነው ። የውጭ አገር ሰዎቹም ከባዕዱ አገርና ከኢትዮጵያ ንጉሥ ወደ ራሳቸው አገር መሪ ተልከው ሲሔዱ ለማን ምን እንደሚሠሩ ግልጽ ነው ። ቀድሞውኑ ወደ ኢትዮጵያ ሲመጡ ላገር ምርመራና ለስለላ ስለሆነ ፣ ያገራቸው ጥቅም በማይነካበት መንገድ ካልሆነ በቀር ለላካቸው የባዕድ ንጉሥ ፣ በተለይ ሥልጣኔ ላልቀመሰ አፍሪካዊ መሪ ፣ ከልብ ይሠራሉ ተብሎ አይጠረጠርም ።

ስለዚህ «አስቀድመህ ዛፉን ትከል ፤ ፍሬው ዐውቆ ይመጣልሃል» እንደሚባለው ፣ አሁንም ዐፄ ቴዎድሮስ አስቀድመው የመዠመሪያውን ደረጃ ትምህርት ቤት በጐንደር ከተማ በማቋቋም ሳይወጥኑ ፣ የፈረንሣይና የእንግሊዝ መንግሥታት በአስቸኳይ የእጅ ጥበበኞች ልከው ያገራቸውን ሕዝብ የመድፍ ሥራና የወታደርነት ሙያ እንዲያስተምሩላቸው በደብዳቤ ይጐተጉታሉ ። ያሰሩትን የእንግሊዝ ቆንሲል ካሜሮንን ለማስፈታት ለመጣው ለምስተር ሆርሙዝ ራሳም በ1858 ዓ. ም. በጻፉለት ደብዳቤ ላይ ፍላጐታቸውን እንደዚህ ሲሉ ገልጸውለታል ። «በስመ አብ...... ከእንግሊዝ ንግሥት ሎሌ ከወዳጄ ካማካሪዬ ካቶ ሀርሞዝ ረስአም ፤ የምፈልገው የምትልክልኝ መድፍ ሠሪ ፣ ነፍጥ ሠሪ ፣ ብረት አቅላጭ ፣ ቦምብ ተኳሽ ፣ መድፍ ተኳሽ ፣ እኒሁ ሁሉ ሠራተኞች አሳይተውኝ እንዲመለሱ ከነመሣሪያቸው ይምጡልኝ......» ፍላድን ወደ አውሮፓ በላኩ ጊዜም ፣ «ብልህ ሠራተኛ ፈልጌአለሁ ። ከኔ የሚመጣን ሠራተኛ ሁሉ በደስታ እቀበለዋለሁ ። ብልሃቱንም አስተምሮ ወደ አገሬ እመለሳለሁ ቢል ደመወዙን ሰጥቼ ፣ ደስ አሰኝቼ እሰደዋለሁ» የሚል ቃል ይገኝበታል ።

ዐፄ ቴዎድሮስ ከንግሣቸው በፊት ፣ 'ቴዎድሮስ የሚባል ንጉሥ ይነግሣል ፣ ኢትዮጵያን አንድ አድርጎ ይገዛል ፣ ግዛቷን ያሰፋል' እንደ ተባለው ፣ ካገሪቱ አንድነት በኋላ ከፊታቸው የተደቀነው የቱርክን ኃይል ከኢትዮጵያ ዙሪያ ለማባረር ስለሆነ ፣ በጥያቄያቸው ውስጥ የዘረዘሩዋቸው የጦር መሣሪያዎች ናቸው ። የውጭ አገር መምህራኑም በቶሎ መጥተው ለኢትዮጵያውያኑ አስተምረው እንዲመለሱ ምኞታቸው ሲሆን ፣ ይኸንኑ ከፈረንጅ

አገር በፈረንጅ ቋንቋ የተሠራውን መማሪያ ኢትዮጵያውያኑ በቅድሚያ የመምህራኑን ቋንቋና በመማሪያው ላይ ያለውን ጽሑፍ ለመረዳት የሚያስችላቸውን ትምህርት የማቋቋሙን ጉዳይ በቅድሚያ እንዳላሰቡበት ይታያል ። የሆነ ሆኖ ፣ ይኸው የጦር መማሪያ ፋብሪካው ባገራቸው ተቋቁሞ ፣ ባገራቸው ሰው ወይም በተቀጠረው የውጭ አገር ሰው እጅ ተሠርቶ ምርቱ ከመታየቱ በፊት እነዚህኑ የኢትዮጵያን ዳርቻ ወረዳዎች እነ በጎስን እነ ሐባብን ፣ ወደቦቹን እነ ምጥዋንና እነዙላን በጦር ኃይል ከቱርኮች የማስለቀቁ ፣ ወደ ኢየሩሳሌም የመዝመቱ ምኞታቸው ቀደም ብሎ ታይቷል ። ከእንግሊዞች ጋር ዋናው የጠቡ መሠረት በዚህ ዘመቻ ያለመተባበራቸው መሆኑ በየሠነዱ ላይ በግልጽ ይነበባል ።

የፈረንጆቹ መሪዎች ካገራቸው የመስፋፋት ፣ ወይም የንግድ ጥቅም ጋር ካልተያያዘ በቀር ስለ ሃይማኖት ምንም ያህል ጉዳይ እንደሌላቸው ባለመረዳት ፣ አጠገባቸው ባሉት አድርባይ የውጭ አገር ሰዎች በመታለል የፈረንሣይ ንጉሠ ነገሥት ናፖሊዮንም ፣ የእንግሊዝ ንግሥት ቪክቶሪያም ፣ ሁለቱም ክርስቲያን በመሆናቸው ብቻ ፣ ከቱርኮች ጋር ወደፊት ለሚያደርጉት ጦርነት የቃል ኪዳን ጓደኛ ሆነው እንዲተባበሩዋቸው ይጠብቃሉ ። በዚህ ምክንያት ፣ በ1850 ዓ. ም. ለንግሥት ቪክቶሪያ በጻፉት ደብዳቤ ላይ «......አሁንም እርስዎ የክርስቶስ ልጅ ነዎ ፤ እኔም የክርስቶስ ልጅ ነኝ ። ስለ ክርስቶስ ፍቅር ወዳጅነት ፈልጌያለሁ» የሚል ይገኝበታል ። በ1855 ዓ. ም. በጻፉት ረዘም ካለው ደብዳቤ ላይ በመጨረሻው መሥመር ፣ «.....እናንተም ተጋፉልኝ ክርስቲያኑን (እኔን) እስላም (ቱርክ) አጠቃህ (ላጥቃህ) ሲለኝ» ያሉት በዚሁ ሳቢያ ነው ።

በእነዚህም በሌላዎቹ ደብዳቤዎች ላይ በሃይማኖት አንድነት ላይ የጠበቀ እምነት እንዳላቸው ሲገልጡ ፣ በሌላው ለንግሥት ቪክቶሪያ አሁንም በ1858 ዓ.ም. በጻፉላቸው ደብዳቤ ላይ ፣ «......ያባቴን መንግሥት ኃይል ሰጥቶኝ መለሰልኝ ።(*) የኢትዮጵያን ሰዎች ድንቁርናታችንን ፣ ዕውርነታችንን ሳይሰሙት አይቀርም ። ያማረ መስሎኝ ደፍሬ የላክሁብዎን ከፍቶብኝ (አጥፍቼ እንደሆነ) ቢገኝ ይምከሩኝ እንጂ አይከፋብኝ ፤ እግዚአብሔር የመረጠዎ

* እግዚአብሔርን ነው ።



ንግሥት ዐይንዎ የበራ ነውና» የሚል ቃል ይገኝበታል ። በሌላው ለራሳም በሚያዝያ ወር 1859 ዓ. ም. በጻፉት ላይ ፣ «......ከንግሥቲቱ ከወዳጄ ፣ ካንቱ ከወንድሜ የምፈልገው ፍቅራችሁን ነው እንጂ ካብት (ሀብት) አልፈልግም ። ካብት አለመፈለጌ ክብር (ባለጠጋ ሀብታም) ሆኜ አይደለም ።...... በጥበብ ዐይኔን ትከፍቱልኝ ብዬ ነው እንጂ» ብለዋል ።[1]

ዐፄ ቴዎድሮስ በየደብዳቤያቸው ላይ እርሳቸውም ፣ ሕዝባቸውም በድንቁርና ውስጥ መገኘታቸው እየነደዳቸው መልሰው ደግሞ ከውጭ አገር ኃያላን ለፖለቲካም ፣ ለንግድም ተልከው የመጡት መልክተኞች በፊታቸው በቀረቡበት ሰዓት ያሠለጥኑኛል ብለው የሚገምቷቸውን የኃያላኑን መልእክተኞች እግር ተወርች እያሰሩ ሲያጉላሉ ፣ ለሥልጣኔ ባላቸው የመጓጓት መንፈስ ውስጥ የክብራቸውና የመዋረዳቸው ሁከት እየተሰማቸው የኃይል እርምጃ ሲወስዱ ይታያል ።

በመዠመሪያው የልጅነታቸውንና የወጣትነት ጊዜያቸውን ያሳለፉት በጦርነትና በሁካታ መካከል እንደ ነበረ ባለፉት ምዕራፎች በሰፊው አንብበናል ። በሰባት ዓመት ዕድሜያቸው የሚማሩበት የቸንከር ተክለ ሃይማኖት ገዳም የተበዘበዘ ጊዜ ብዙ ጓደኞቻቸው በፊታቸው ከተገደሉ ዠምሮ በደጃች ክንፉም ፣ በደጃች ጐሹም ቤት ባሽከርነት ፣ ቀጥሎም በሽፍትነት ያሳለፉት ዘመን የጦርነት ፣ የዘረፋ ፣ የቅሚያ ፣ የግድያ ፣ የለቅሶና የዋይታ ነው ። ወደ ዙፋን ለመውጣት ከደጃዝማች ወንድይራድ እስከ ደጃች ውቤ ድረስ ራሳቸው ያደረጉዋቸው የጦርነት ዘመናት ከጦርነቱ በፊት ፣ «ታጠቅ ፣ ተደራጅ » በጦርነቱ ሰዓትና ከጦርነቱ በኋላ ፣ «ያዘው ፣ በለው ፣ እሰረው ፣ ጣለው ፣ ግረፈው ፣ እጅና እግሩን ቁረጠው» የሚለው ወታደራዊ አባባል ልማዱ እንደ ባሕርይ ከሰውነታቸው ጋር ተዋሕዶ የዕድሜያቸውን ዘመን የመረዘው ይመስላል ።

1 Oriental Documents II. The Amharic Letters of Emperor Theodore ... to the Queen Victoria — Girma Selasse Asfaw and David L. Apple yard in Collaboration with E. Ullendorff - Eo. 1/26, Fol. 210, 5 — Fol. Mss Eur. Fol. 103, Fol. 23 EO, 95/7 2 5. F O L. 226.

ስለሰው ባሕርይ ተመራማሪ የሆኑ ሊቃውንት አንዳንዶቹ
የሰውን ጠባይ የሚቀርፀው የኑሮው አካባቢ ነው እንጂ ፥ ከልጅ
ነት እስከ ዕውቀት በፍጥረቱ ክፉም ፥ ደግም ሰው የለም ሲሉ ፥
ሌሎቹ አንዱ ሰው ከባሕርዩ (ከፍጥረቱ) ደግነትና ርኅራኄ ያለው
በሁካታም ፥ በጦርነትም መካከል ቢያድግ ከባሕርዩ ጋር የተያያ
ዘውን ደግነት አይተውም ይላሉ ። ከባሕርይ የመጣውም ፥ ካካ
ባቢ የተወረሰውም ፥ ሁለቱም በሰው ላይ ይጫናል የሚሉ አሉ ።([1])

የሆነ ሆኖ ፥ ዐፄ ቴዎድሮስ የቁጡነትን ጠባይ ከሌላው
በውርስም ያግኙት የራሳቸው ባሕርይም ይሁን ፥ ከነገሡም በኋላ
የዕረፍት ጊዜ ሳይታደሉ አሸነፍሁት ፥ ገዛሁት ያሉት አውራጃ ፥
ገባልኝ ተገዛልኝ ያሉት መስፍን ፥ እንደገና በመሸፈት መላ ዕድ
ሜያቸውን የጦርነት ዘመን ስለ ከበበው ፥ መንፈሳቸውን ጠር
ጣሪና ኃይለኛ አድርጎ አገዛዛቸውን ብቻ ሳይሆን ከውጭ አገር
እርዳታ አጠያየቃቸውን ሳይቀር ፥ ከደብዳቤያቸው ላይ የሰፈረ
ውን ለስላሳ አቀራረብ በመጨረሻ ወደ ኃይል እንዲለውጡት
አስገድዷቸው ይታያል ። ራሳቸውን ዝቅ አድርገው በደብዳቤ ፥
«አስተምራችሁኝ ዐይኔን ከፈቱልኝ» ካሉበት ወቅት ቀጥሎ
የእንግሊዙን ቆንሲል ካሜሮንን ፥ «የጻፍሁትን ደብዳቤ ለምን
ራስህ ወስደህ ለንግሥት ቪክቶርያ አቅርበህ መልስ አላመጣ
ህም?» ብለው ሲያስሩት ፥ በምኞታቸው ስፋትና በማስፈጸሚያው
ሁኔታ መካከል ያጋጠማቸው የተራራቀ ሁኔታ የቱን ያህል አስ
ቸጋሪ እንደ ሆነባቸው ያሳያል ።

የንግሥት ቪክቶሪያን ቆንሲል ፥ ቴዎድሮስ የሚባል አፍ
ሪካዊ ንጉሥ አሰረው የሚለው ወሬ በሎንዶን ሲሰማ ትልቅና
አስገራሚ ጉዳይ ሆነ ። የእንግሊዝ መንግሥትም ጉዳዩን በውጭ
ጉዳይ ቢሮ ካስጠና በኋላ ፥ የኃይል እርምጃ በመውሰድ ፈንታ
ራሳም የንግሥቲቱን ደብዳቤ ይዞ ይሒድና በሰላምና በስምምነት
ያስፈታ ተብሎ ስለ ተወሰነ ፥ ራሳም ወደ ርሳቸው ሲመጣ በክ
ብር ከተቀበሉት በኋላ የጠበቁትን ውጤት ይዞ ባለመምጣቱ
የርሱም ፍጻሜ እንደ ቀሩት ሁሉ እስራት ሆነ ።

---

1 Le Temperament Nerveux — Dr. **Alfred Adler** — **pp. 69, 106, 120, 257, 314**



ደግሞ ባንድ ወገን አሠልጥኑን እያሉ የአውሮፓ ኃያላንን
በደብዳቤ ሲጠይቁ ፥ በሌላ ወገን በባዶ እግር በመራመድና ተራ
ያገራቸውን ልብስ በመልበስ ከፈረንጆች ከእጅ ጥበባቸው
በቀር የፈረንጆቹን መልካቸውንም ፥ ልብሳቸውንም ፥ ባህላቸ
ውንም እንደ ናቁት በብዙ ረገድ ይታያል ። በዚሁ ጐን ፥ ያገ
ራቸውን ጠላቶች ቱርኮችን ከኢትዮጵያ ዙሪያ ለማባረር ከኢየ
ሩሳሌም ለማስወጣት የሚያስችል የጦር መሣሪያና መርከብ ራሳ
ቸው ከነሕዝባቸው ለመሥራት ባለመቻላቸው ፥ ንዴትና ጸጸት
ላይ እንዳደረሳቸው በግልጽ ደብዳቤ ለመናዘዝና ራሳቸውን
ሥልሰው ለመስደብ ግዴታ ሆኖባቸው ሳለ ፥ የፈረንጅ ተማሪ
መሆኑንም የጠሉት መስለው ይታያሉ ።

የግሪኩ ፈላስፋ ዴዎጋን ፥ እንደ ቴዎድሮስ ብስጩ ፍጡር
ስለ ነበር ዐልፎ ፥ ዐልፎ ፕላቶንን ሲያስተምረው ይመታው
ነበር ። ፕላቶን ደግሞ የዴዎጋን ትምህርት ስለ ጣፈጠው በብ
ትሩ ሳይመረር ፥ «ግደለም ምታኝ ፤ ነገር ግን አስተምረኝ»
ይለው ነበር ይባላል ። የኢትዮጵያን አንድነት ለመገንባትና ግዛ
ቷን ለማስፋፋት ትንቢት የተነገረላቸው ዐፄ ቴዎድሮስ ግን ፥
ንጉሠ ነገሥት እንደ መሆናቸው መጠን ፥ የተማሪነት አቅዋማ
ቸው ከፍልስፍና ስሜት በቀር የግዛት ሥልጣን ከሌለው ከፕላ
ቶን ለየት ስለሚል ፥ «አስተምሩኝ ፥ ነገር ግን ተጠንቀቃችሁ
አክብሩኝ» የሚል ነው ። ይህ ደግሞ አለመግባባትንና የእስራት
ውጣ ውረድን ባሕርይ ፈጥሮ በመጨረሻ ወደ መቅደላው ጦር
ነት እንደ መራቸው ዝርዝሩን ወደፊት እናነባለን ።